**ዋና አዘጋጅ:-**
ይገዛል አረጋ

**ሪፖርተር:-**
ይገዛል አረጋ
መሰረት አለማየሁ
ጌትነት መላኩ
አስቻለው ይርሰማ
መክሊት ይልማ
ሄኖክ ከድር
አቡበከር አሰፋ
ታደሰ አለማየሁ
ሰላማዊት እሸቴ

**ኤዲተር:-**
ይገዛል አረጋ

**ፎቶግራፈር:-**
ብሩክ ተክሉ
ድረስ ወርቁ
ነፃነት ንጉሴ
አስተባባሪ
ሲፈን ባዩ

**ፀሀፊ:-**
ሰላማዊት ተመልሶ

**ሹፌር:-**
ዳንኤል ባይሳ

**ፅዳት:-**
ንጋት ታደገ

**ዲዛይንና ህትመት:-**
ኤልያና ማተሚያ ቤት
0911 079663
0930 878787

# ማውጫ

1. የአዘጋጁ መልዕክት ............................................................
2. የኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ሃላፊ መልዕክት .................................
3. የዋና ስራ አስፈፃሚ መልዕክት ............................................
4. የብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ሃላፊ መልዕክት .............................
5. አንድ ሙያ ለአንድ ዜጋ..........................................................
6. የእንደራሲዎች ሚና.............................................................
7. ለማህበረሰቡ ፈጣኝ ምላሽ እየሰጠ ያለ ተቋም..................................
8. ተግባር በውጤት ..............................................................
9. የትውልድ ግንባታ ለሀገር እድገት................................................
10. አቅም የገነባ ተቋም...........................................................
11. ምቹ የስራ አካባቢ ለውጤታማ አገልግሎት.........................
12. የገፅታ ግንባታ ስራ በልደታ .................................................
13. ፈጣን አገልግሎት በቴክኖሎጂ...............................................
14. ፅዳትን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ............................................
15. ሪፎርም ለውጤታማ አገልግሎት..............................................
16. የአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጤታማነት ...............................
17. ህብረት ስራ ማህበራት ለውጤታማነት.............................
18. የሌማት ትሩፋ ለዜጎች ተጠቃሚነት ...................................
19. የፕሮጀክቶች አፈፃፀም በልደታ............................................
20. መስሪያ ቦታዎች ለፍታሃዊ ተጠቃሚነት...............................
21. ሰላም ለሀገር ልማት.............................................................
22. እንግልትን የቀነሰ ተቋም.....................................................
23. ትውልድን በስነ-ምግባር ተቀቋምን በአሰራር..........................
24. የዘርፈ ብሩ ተልዕኮ ባለቤት..................................................
25. ጤናው የተጠበቀ ትውልድ......................................................
26. ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም..................................................
27. ውብ አዲስ አበባን የመፍጠር ጉዞ...........................................
28. ማዘጋጃቤታ አገልግሎት ለህብረተሰባችን .........................
29. ጥራቱን የጠበቀ ምግብና መድሃኒት...................................
30. ይቻላል በተግባር.............................................................
31. የወጣቶች ሚና ለሀገር ብልፅግና...........................................
32. የመንግስት ንብረት የጋራ ሀብት.........................................
33. ንፁህ አካባቢ ለጤናማ ህይወት............................................
34. የሴቶች ተሳትፎ ለዘላቂ ልማት............................................
35. የህግ ተፈፃሚነትን ያረጋገጠ ተቋም.....................................
36.፲ ላን ለከተማ ገፅታ ...................................................

# የአዘጋጁ መልዕክት

ከተማችን አዲስ አበባ የሀገራችን ዋና ከተማ የአፍሪካ ህብረትና የአለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ፣የዲፕሎማቶች መኖርያና የሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች መቀመጫ ፣የሀገሪቱ ከፍተኛ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚደረግባት፣ በርካታ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማት የሚገኙባት፣በአንፃሩ ደግሞ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥርና ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ የሚከተል ማህበረሰብ ከተማ በመሆኗ ለነዋሪዎቿ ምቹ ውብና ፅዱ በማድረግ በተለያዩ ዘርፎች የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከመቼው ጊዜ በላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል። የተጀመሩትን ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ወደ ከተማችን በማምጣት በርካታ ሰው ተኮር የሆኑ ፕሮጀክቶችን በ24/7 ማሳካት ተችሏል።

በመሆኑም በመከናወን ላይ የሚገኙ የልማት ስራዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸው በማድረግ የዜጎችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የሀገራችንን ብልፅግና ማረጋገጥ ይኖርብናል።

የልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር የነዋሪዎችን ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ ሰው ተኮር የሆኑ ፕሮጀክቶችን በማከናወን የኑሮ ውድነትን በማረጋጋት፣ የዜጎችን ሰላም በማረጋገጥና ፈጣንና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት በመስጠት በህብረተሰቡ የሚነሱ የመልካም አሰተዳደርና የልማት ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ በመስጠት ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል።የዜጎችን ተጠቃሚነት በተሻለ መልኩ ለማስቀጠል ሁሉም የክ/ከተማው ነዋሪዎችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ከአስተዳደሩ ጎን በመሆን ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል የሚል መልዕክታችንን በዝግጅት ክፍሉ ስም እናስተላልፋለን።



## ወ/ሮ ሲፈን ባዩ
## የኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ

### ገቺ ትርክትን እየገነባ ያለ ተቋም

የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ጠንካራ የኮሙኒኬሽን ስርዓት በመዘርጋት በቂና የተሟላ መረጃ ያለው፤ በሁለንተናዊ እድገት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግ ህብረተሰብ በመፍጠር ከተማችን አዲስ አበባ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት እንድትሆን ለማስቻል የበኩሉን ራዕይ ሰንቆ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።

ጽ/ቤቱ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት የተለያዩ የኮሙኒኬሽን አግባቦችን በመጠቀም ዘመናዊ፣ ግልጽ እና ፈጣን ምላሽ መስጠትን ባህሉ ያደረገ የኮሙኒኬሽን ስርዓት በመዘርጋት ላይ ይገኛል።

የኮሙኒኬሽን ዘርፉን በማጠናከር በመንግስትና በህዝብ መካከል ጥራት ያለውና እና ለሁሉም ነዋሪ ተደራሽ የሆነ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የማድረግ ተግባር ተከናውኗል። የማህበረሰቡን ትክክለኛ የመረጃ ፍላጎት በማርካት ተሳትፎና ተጠቃሚነቱን ማሳደግ፣ የሀገራችንና የከተማዋን መልካም ገጽታ መገንባት እንዲሁም በዋና ዋና ሀገራዊና ከተማ አቀፋዊ አጀንዳዎች ላይ የጋራ መግባበትን መፍጠር የሚያስችል ተልዕኮ ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።

ጽ/ቤቱ በ2018 በጀት ዓመት በህዝብና ሚዲያ ግንኙነት ተግባራት ተግባቦት በመፍጠር የመረጃ ተደራሽነትን ማሳደግ፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ የዲጅታል ሚዲያ፣ ሞኒተሪንግ እና የከሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መረጃ አገልግሎት ስርዓትን ማሳደግ እና ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀምና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማሻሻል ማዕከል ያደረጉ ስትረቴጂክ ግቦች ቀርፆ ወደ ተግባር ገብቷል።

በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያው 6 ወር በዕቅድ ያስቀመጣቸውን ተግባራት ለማከናወን ያለሰለሰ ጥረት አድርጓል። በዕቅድ ይዞ ያከናወናቸውን ተግባራት አፈፃፀም በየጊዜው በመገምገም የታዩ ጥንካሬዎችን ማስቀጠልና ክፍተቶችን በማረም ውጤታማ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል።



## ወ/ሮ ልዕልቲ ግደይ
## የልደታ ክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ
## የዋና ስራ አስፈፃሚ መልዕክት

የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸምን በመገምገም እና በየደረጃው ካለው የማህበረሰብ ክፍል ጋር ውይይት በማድረግ በተገኘው ግብዓት መሰረት የ2018 በጀት ዓመት የልማት እና መልካም አስተዳዳር ዕቅድ ከተዘጋጀ በኋላ በሁሉም አካላት ተሳትፎ እንዲዳብር ተደርጎ በሙሉ አቅም ወደ ተግባር በመግባት በግማሽ ዓመቱ ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችሏል፡፡

ባለፉት 6 ወራት በተለይም የህብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ቁልፍ የልማት እና መልካም አስተዳዳር ተግባራትን ውጤታማነት እያረጋገጡ ከመሄድ እና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ተቀብሎ ተገቢ ምላሽ በመስጠት በኩል አበረታች ውጤቶች ታይተዋል፡፡
በአስተዳደሩ ባለፉት 6 ወራት ከተመዘገቡ ጉዳዮች ውስጥም ለአብነት የሚከተሉትን ማየት ይቻላል፡፡

በአገልግሎት አሰጣጣችን የግልጸኝነት እና ተጠያቂነት አሰራር ስርዓትን በማስፈን ለነዋሪዎቻችን ምቹ እና ቀልጣፋ አገልግሎት የመስጠት ግብ ተቀምጦ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ በዚህም ተቋማትን በሰው ሃይል፣በአሰራር እና በቴክኖሎጅ ሪፎርም በማድረግ እና ምቹ የስራ አካባቢን በመፍጠር አገልግሎት አሰጣጣችን ፈጣን፣ ቀልጣፋና ምልልስን የሚቀንስ እንዲሆን ተደርጓል በዚህም የበርካታ ተገልጋዮች ያደረ ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ማድረግ ተችሏል፡፡

ጽ/ቤቱ በህትመትና ዲጅታል ሚዲያዎች ገዥ ትርክቶችን በማስረጽ ረገድ ውጤታማ ስራዎችን እየሰራ ነው፡፡በለሀገር ማንሰራራት የሚተጋ ማህበረሰብ ለመገንባትም ከምንጊዜውም በላይ በትጋት እየሰራ ይገኛል፡፡

ተቋሙ በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያው 6 ወር ውጤታማ ስራ እንዲሰራ ስትሰሩ ለነበራቹህ ሁሉ ምስጋናየ የላቀ ነው በቀጣይም ድጋፋቹህ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አደራ እላለሁ፡፡



**አገልግሎት አሰጣጥ**

የኑሮ ውድነት እና የገበያ አለመረጋጋት ዓለም-አቀፋዊ፤ አህጉራዊ እና አገር አቀፋዊ ገጽታዎች ያሉት ቢሆንም ችግሩ እየተባባሰ በመሄድ ነዋሪው ላይ ጫና እንዳይፈጥር  በክፍለ ከተማ ደረጃ የሸማች ህ/ስራ ማህበራትን እና አምራቹን በማሳተፍ እና ማንቀሳቀስ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎችን የማስፋፋት ስራዎች ተጠናክረው ቀጥለዋል ፡፡ በድጐማ የሚቀርቡ  መሠረታዊ  ሸቀጦች ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ  እንዲቻል  ለሸማች  ማህበራቱ  የብድር  አቅርቦት በማመቻቸት ሰፋፊ ስራዎችን ለመስራርት ጥረት ተደርጓል፡፡ ሰው ሰራሽ የገበያ ጉድለት በሚፈጥሩ እና ህገ ወጥ እንቅስቃሴ በሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይ የቁጥጥር ስርዓቱን የማጠናከር መጋዘናትን የመፈተሽ፣ የበር ለበር ቁጥጥር የማድረግ ሥራዎችን ተሰርቷል፡፡ በአጠቃላይ የምርት አቅርቦትን በማስፋት እና ምርቶች ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ በማድረግ ስኬታማ ስራ ተከናውኗል፡፡



**የኑሮ ውድነትና ገበያ ማረጋጋት**

የህብረተሰቡ መሰረታዊ ጥያቄ የሆነውን የኑሮ ውድነቱን ጫና ለመቀነስ የከተማ አስተዳደሩ ባስቀመጠው አቅጣጫ  ከስራ ዕድል ፈጠራ ስራችን  ጎን ለጎን የከተማ ግብርና ስራችንን በማስፋፋት የቤተሰብ ፍጆታን ማሟላት እና በሌማት ትሩፋት ከቤተሰብ ፍጆታ ባለፈ ለገበያ በማቅረብ የኑሮ  ውድነቱን የማረጋጋት ስራችን  በልዩ ትኩረት  የተሰራ ሲሆን በተለይም  በዶሮ እርባታ ፤ የወተት ላም እርባታ እና በጎሮ አትክልት አዎንታዊ ስራዎች ማከናወን የተቻለ ሲሆን ተግባሩም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡



**የከተማ ግብርና ስራዎች**

ከሁሉ በላይ የክፍለ ከተማችን ብሎም የከተማችን ሰላም እና ጸጥታ እንዲከበር ህብረተሰቡ በየግዜው የሚያነሳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ህብረተሰቡን የሰላም ባለቤት በማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት በመፍጠር ከጸጥታ በጥምር ሃይሉ (ፖሊስ ፣ከደንብ እና ከሰላም ሰራዊት) ጋር በመሆን  ቀድሞ የመከላከል ስራ በልዩ ትኩረት በማከናወን የጎላ ችግር ሳያጋጥም የተለያዩ ሃይማኖታዊ በዓላት እና ኩነቶች በስኬት የማጠናቀቅ እና የአካባቢውን ሰላም እና ጸጥታ በማስጠበቅ በኩል ህብረተሰቡ እና ጥምር ሃይሉ የበኩሉን ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡



**የሰላምና ፀጥታ ስራዎች**

በተለመደው አካሄድ የማህበረሰቡን የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግር ለመፍታት አስቸጋሪ በመሆኑ አስተዳደሩ የኢንሼቲቭና ሰው ተኮር ተግባራትን አቅዶ በመስራት ባለፉት 6 ወራት ውጤታማ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ባለፉት 6 ወራት የመንግስት ሰራተኛውን፣

የአመራሩንና የማህበረሰቡን ተደማሪ አቅም በመጠቀም የማህበረሰቡን የበርካታ አመታት ጥያቄ በአጠረ ጊዜ የመለሱ የኢኒሼቲቭ ስራዎች ተከናውነዋል።

የዜጎችን የመኖሪ ቤት ችግር ለማቃለል የሚያስችሉ የጂ+4 መኖሪያ ቤቶች ግንባታ እተከናወኑ ይገኛሉ።



**የኢንሽቲቪ ስራዎች ቤቶች ግንባታ**

አስተዳደሩ ለትውልድ ግንባታ ትኩረት በመስጠት ፕሌይ ግራውንዶችንና የህጻናት ማቆያዎችን በሰፊው በማከናወን የታዳጊዎች፣ የወጣቶችን እና የእናቶችን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ስራ ሰርቷል።



**ፕላይ ግራውንድና የህፃናት ማቆያ**

በክፍለ ከተማው ምቹ የስራ አካባቢን በመፍጠር ረገድ ሰፋፊ ስራወች የተከናወኑ ሲሆን ለአብነትም ብቁ ንቁና አምራች የሆኑ አመራርና ሰራተኞች ለመፍጠር የሚስችል ደረጃውን የጠበቀ ጅምናዚየም ቤት እንዲሁም የሰራተኛውን የኑሮ ጫና ለማቃለል የሚያግዝ ካፌዎችና ሱፐር ማርኬቶችን ስራ አስጀምሯል።



**የሰራተኞች ክበብና ሱፐርማርኬት**

አሁን ያለውን ሰላም የበለጠ ለማጽናት እንዲቻል ፖሊስ ጣቢያዎችን የመገንባት እና ሲሲ ቲቪ ካሜራዎችን በመግጠም የወንጀል ምጣኔ በእጅጉ እንዲቀንስ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል።



**የደህንነት ካሜራ**

በአጠቃላይ የክፍለ ከተማውን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ስራዎች በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ ሁሉንም ባሳተፈ መልኩ ሲከናወኑ ነበረ በዚህም በርካታው የማህበረሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ ችለናል።

በሁሉም ዘርፍ የልደታን ከፍታ ለማረጋገጥ ተደማሪ አቅምን ተጠቅመን እየሰራን የላቀ ተጠቃሚነትን እናረጋግጣለን። ይህ እንዲሳካ ሁሉም ከጎናችን ሆኖ አቅሙ የሚፈቅደውን አስተዋጾ እንዲያደርግ ጥሪየን አቀርባሉ።

**በአዲስ ዕይታ የልደታን ከፍታ እናረጋግጣለን!**



## አቶ ፍታለው ከፌያለው
## የልደታ ክ/ከተማ ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ

ከተማችን አዲስ አበባ ስሟን የሚመጥን፣ ዉብ፣ ፅዱ፣ ለመኖርያ የተመቸች እንድትሆን ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ። ክፍለ ከተማችን ልደታም የከተማዋን እድገትና ብልፅግና የሚመጥን የልማት ስራዎችን በማከናወን የነዋሪዎቿን የልማት ጥያቄ ለመመለስ ሰፋፊ ስራዎች በማከናወን ላይ ናት። የከተማችንን ሰላምና ፀጥታ አስተማማኝ ከማድረግ አኳያ ህዝባዊ ተሳትፎ ለማጎልበት እና በማጠናከር በፀጥታ ስራ ህዝቡ በበላይነት ተዋናይ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር በርካታ ስራዎችን መስራት ተችሏል።

በሰው ተኮር በሆኑ ስራዎቻችን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ወገኖቻችንን መርዳትና መደገፍ ባህል ያደረገች ከተማ መፍጠር ችለናል፤ የበጎ ፈቃድ ስራዎች የህሊና እርካታ የምናገኝበት ከመሆኑ በተጨማሪ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ወገኖቻችን ችግራቸው የሚፈታበት ተግባር በመሆኑ የመተባበርና መደጋገፍ ባህልን በማጎልበት በርካታ የበጎ ፈቃድ ስራዎች እየሰራን እንገኛለን።

ነዋሪዎቻችንን የሚመጥን ቀልጣፋ እና ዘመናዊ አገልግሎት ለመስጠት የጀመርናቸውን ስራዎች አጠናክረን እንቀጥላለን። የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች ከሌብነት የጸዳ፤ ፈጣን፤ ቀልጣፋና ብቃት ያለው አገልግሎት በመስጠት ሀገራዊ ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባል። የአገልግሎት ቅልጥፍናን ለመጨመር በሲቪል ሰርቪስ ተቋማት በቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራር ለመዘርጋት የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በብልፅግና ፓርቲ የሚመራው የመደመር መንግሥት “የጉባ ብስራቶች የመደመር መንግሥት ትሩፋቶች” በሚል መሪ ቃል በከተማችን እና ክ/ከተማችን ህዝባዊ የውይይት መድረኮች ማካሄዱ የሚታወስ ነው። ለተከታታይ ሁለት ሳምንት በመዲናችን አዲስ አበባ አስራ አንዱም ክ/ከተሞች እና በሁሉም የክልል ዋና ዋና ከተሞች የውይይት መድረኮች ከፍ ያለ የህዝብ ተሳትፎ የታየባቸው ሆነው ተካሂደዋል።

ህዝባዊ የውይይት መድረኮቹ መንትያ ግቦች ያነገቡ ናቸው፤ አንደኛው ግብ ብልፅግና ለህዝብ የገባውን ቃል ህዝብ አስተባብሮና ተጠቃሚ አድርጎ በተግባር የገለጠበትን እውነታ ከህዝቡ ከራሱ አብሮ ለመገምገም ሲሆን፤ ሁለተኛው ግብ በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች የሚሰተዋሉ ችግሮችን ከህዝቡ ከራሱ በማዳመጥ መፍትሄ መስጠት ነው።

የህዝባዊ ውይይት መድረኩ መሪ ቃል አካል የሆነው አንደኛው ነጥብ 7ቱ የጉባ ብስራቶች ሲሆኑ እነዚህም ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክታችን በድምር በ6 እጥፍ ሚተልቁ የ30 ቢልየን ዶላር ፕሮጀክቶች ናቸው። እነዚህ የማዳበሪያ፣ የነዳጅ ማጣሪያ፣ የጋዝ ኃይል፣ የኒኩሌር ኃይል፣ የቤት ልማት እና የግዙፍ አየር ማረፍያ ግንባታ ፕሮጀክቶች ኢትዮጵያን በቀጣይ 5 ዓመታት ወደ የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት የሚያደርሱ እና የሀገረ-መንግስት ግንባታ አካል የሆኑ ስትራቴጂክ ፕሮጀክቶች ናቸው።

መንግሥት በነዚህና ሌሎች አያሌ ድሎች ሳይዘናጋና ሳይኩራራ በህዝብ ዘንድ የሚነሱ ችግሮችና ቅሬታዎች በመድረኩ እንዲነሱ አድርጓል። መንግሥት በህዝብ ዘንድ የሚነሱ የተለያዩ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ከህዝቡ አንደበት ለማዳመጥ የሄደበት ርቀት የህዝባዊነቱ እና የአገልጋይነቱ ጥግ ማሳያ መሆናቸው በተሳታፊዎች በደስታ-እምባ ጭምር የታጀበ እውቅናና ምስክርነት ተሰጥቶታል።

ይህ ነባራዊ ሁኔታ በአንዳንድ ባዳዎችና ባንዳዎች በማህበራዊ ሚዲያ ከሚነዙ የሀሰት ወሬዎችና አሉባልታዎች በተቃራኒ ህዝብ ከመንግሥት ጎን ያለ መሆኑ እና የሚያጋጥሙ ችግሮችም ከመንግሥትና ህዝብ የመፍታት አቅም በላይ አለመሆናቸው ከፍተኛ እምነትና ተስፋ እንዳለ ታይቷል።

የመንግሥት ህዝባዊነትና ህዝብን የማዳመጥ ተግባር በተከታታይ ዓመታት የተስተዋለ ቢሆንም በዚህ ጊዜ እየተካሄደ ያለው ህዝባዊ ውይይት ላይ የተለየ ትርጉም ተገኝቶበታል። ይህ የተለየ ትርጉም በዚህ ዓመት ነፃ፣ ፍትሀዊ፣ ተዓማኒና አሳታፊ ሆኖ ለሚካሄደው ሀገራዊ ምርጫ እና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እንዲሁም ለቀጣይ 5 ዓመታት የብልፅግና የመሪነት ያለው ህዝባዊ ድጋፍና ዝግጁነት ነው።

በከተማችን አዲስ አበባ እና በክ/ከተማችን የተከናወኑ የልማት ስራዎች ወጣቶችን በዘላቂነት ተጠቃሚ የሚያደርጉ ናቸው። ወጣቶችና ሴቶች በሰው ተኮር፣ በበጎ ፈቃድ፣ ሰላምና ጸጥታ፣ በኮሪደር ልማትና ሌሎች ፕሮጀክቶች ጉልህ ሚና በመጫወት የስራ እድል ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ። ወጣቶችን በፖለቲካ፣ በማህበራዊና ምጣኔ ሃብት ዘርፎች ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ አካታች እድገት ለማምጣት የተጀመረው ተግባር የሚበረታታና ተጠናክሮ የሚቀጥል ነው።

## አንድ ሙያ ለአንድ ዜጋ

በክፍለ ከተማ ደረጃ ጽ/ቤቱ በተደራጀበት አግባብ የስራና ክህሎት ጽ/ቤት በሚል በሁለት ዘርፎችና በ8 ቡድኖችና በማደራጀት የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት ማጠንጠኛ የሆነውን የስራ እድል መፍጠርንና የስራ ስምሪትን በማሳለጥ፣ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነትንና የሙያ ደህንነትን ጤናማ በማድረግ፣ የኢንዱስትሪ ሰላምን ለማረጋገጥ እና ለኢንዱስትሪው እድገት መሰረት የሚጥሉ ኢንተርፕራይዞችን የማልማትና የኢንተርፕራይዞች ሽግግር ስራን በማፋጠን በምርትና ምርታማነት ላይ እምርታዊ ለውጥ የማምጣት ተልዕኮን ለማሳካት እንዲያስችለው በባለፉት ዓመታት ትግበራ የተመዘገቡ ውጤቶችን እንዲሁም የታዩ ክፍተቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ የስራ ገበያውን መሰረት በማድረግ የሰው ኃይል የማሰልጠንና የማዘጋጀት፣ የከተማዋን ነዋሪ የስራ አጥነት ችግር የሚቀርፍ ዘላቂና አስተማማኝ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የስራ ስምሪትን በማሳለጥና የአሰሪ ሰራተኛ ግንኙነትን መልካም በማድረግ የኢንዱስትሪ ሰላም ማስፈን፣ የኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችል ቅንጅታዊ ስራዎች አተገባበርን እንዲሁም ለዘርፉ የተሰጠውን ተልእኮ እና በልደታ ክ/ከተማ ስራና ክህሎት ጽ/ቤት በ2018 በጀት ዓመት ባለፉት ወራት የተከናወኑ ተግባራትን መነሻ አድርገን ከልደታ ክ/ከተማ ምክትል ስራ አስፈጻሚ እና የስራና ክህሎት ጽ/ቤት ኃላፊ ከአቶ አራርሳ ድሪባ ጋር የዝግጅት ክፍሉ ቆይታ አድርጓል፡-



### አቶ አራርሳ ድሪባ
### የክ/ከተማው ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚና የስራና ክህሎት ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** የጽ/ቤቱን ራእይና ተልእኮ ቢገልጹልን?

**አቶ አራርሳ፡-** የጽ/ቤቱ ራእይ የከተማችንን ራእይ በመጋራት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2022 ዓ.ም ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል በማፍራት ምቹ የስራ ሁኔታ የተረጋገጠበት ዘላቂ የስራ ዕድል ተፈጥሮ ማየት ሲሆን፡-

**ተልዕኮው ፡-** ደግሞ ክህሎት መር የውጤት ተኮር የስልጠና ስርዓት በመዘርጋት ብቁ ተወዳዳሪና ስራ ፈጣሪ የሰው ኃይል በማፍራት፣ ለኢንተርፕራይዞች ድጋፍ በማድረግ ማልማት እንዲሁም ውጤታማ የሆነ የስራ ስምሪት አገልግሎት በመስጠትና የኢንዱስትሪውን ሰላም በማረጋገጥ፣በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ነዋሪዎችን ኑሮ በማሻሻል፣ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነትን ጤናማ በማድረግ፣ የስራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ የሚያስችል ተቋም በመገንባት፣ ዘላቂ የስራ እድል እንዲፈጠር ማድረግ ነው።

**ልደታ ፋና፡-** ጽ/ቤቱ የትኛውን ማህበረሰብ ክፍል ነው የሚያገለግለው?

**አቶ አራርሳ፡-** በልደታ ክ/ከተማ ስራና ክህሎት ጽ/ቤት የአስር ዓመት ፍኖተ ብልፅግና /ከ2013 – 2022 በጀት ዓመት/ የልማት ዕቅድ በማቀድ በየደረጃው ያሉ ጽ/ቤቶች በ4ቱ የዘርፉ እሳቤዎች ማለትም የክህሎት ልማት፣ የስራ እድል ፈጠራ፣ አሰሪ ሰራተኛ ጉዳዮችና ተቋም ግንበታ በተጨማሪ ከኢንተርፕራይዝ ልማት ጋር ተያያዥ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚፈልጉ ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍሎች፣ተቋማት እና ድርጅቶች አገልግሎት የሚያገኙበት ሲሆን ከደንበኞቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ ዝቅተኛ ነዋሪዎች፣ ስራ ፈላጊ ወጣቶች እና ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ከስደት ተመላሽ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የኢንተርፕራዝና የኢንዱስትሪ አንቀሳቃሾች፣ የከፍተኛ ኢንዱስትሪ ባለቤቶች፣ የአሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች፣ የግል ድርጅቶች ሰራተኞች፣ የሰራተኛ ማህበር አመራሮች እና መሰል የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው።

**ልደታ ፋና፡-** የጽ/ቤቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ምንድን ነው ?

**አቶ አራርሳ ፡-** የስራና ክህሎት ጽ/ቤት የሃብት ክፍፍል ፍትሃዊነት የሚረጋገጥበት፣ የኑሮ ውድነት እና የዋጋ ንረት የሚረጋጋበት፣ የአሰሪ እና ሰራተኛ ግንኙነት ጤናማ የሚሆንበትና የኢንዱስትሪ ሰላምና የሰራተኞች የሙያ ደህንነት የሚረጋገጥበት እንዲሁም የኢንተርፕራይዞችን የማምረት አቅም እና የምርትና አገልግሎት ጥራት በማሳደግ በብቃት፣ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የተለያዩ መንግስታዊ ድጋፎችን በማድረግ ዜጎች በገቢ ራሳቸውን እንዲችሉ የሚደረግበት ከመሆኑም ባሻገር ምርታቸውን ለሀገር ውስጥና የውጪ ገበያ በማቅረብ የገበያን ጅፍተት በመሙላትና የውጭ ምንዛሬን በማስገኘት እንዲሁም የሚጠበቅባቸውን ግብር በመክፈል ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖያዊ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። በማህበራዊ ዘርፉም ስንመለከት ከራሳቸው አልፈው ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር፣ የአቅመ ደካማ ቤቶችን በማደስ፣ ማእድ በማጋራት እና እርስ በርስ በሚያደርጉት ማህበራዊ መስተጋበር ሰፊ ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸውን ተግባራት እያከናወኑ ከመሆኑም ባሻገር በክ/ከተማ፣ በከተማ ብሎም በሀገር ደረጃ እየተከሰቱ ያሉ መነሻቸው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮች የሆኑ ፖለቲካዊ ስብራቶችን የምንጠግንበት ዘርፍ በመሆኑ እነዚህንና ሌሎች ያልተጠቀሱ ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች እያበረከተ ይገኛል።

**ልደታ ፋና ፡-** በበጀት ዓመቱ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት የምትከተሉት መርህ ምንድን ነው ?

**አቶ አራርሳ ፡-** የስራ እድል ፈጣራ ስራ በርካታ ባለድርርሻ አካላትና አስተግባሪ ተቋማት የሚሳተፉበትና በቅደም ተከተል የሚከናወኑ ተግባራትን ያካተተ ሰፊ ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም የ2018 በጀት ዓመት እቅድን ለማሳካት የምንከተለው መርህ ከስልጠና አኪያ አንድ ሙያ ለአንድ ዜጋ የሚል ሲሆን ከስራ እድል ፈጠራ አንጻር ደግሞ ክህሎት መር የስራ እድል ፈጠራ ነው፡፡ ይህ ማለት ከስልጠና አኪያ አንድ ስራ ፈላጊ ቢያንስ አንድ ሙያ መያዝ ያለበት ሲሆን ከስራ እድል ፈጠራ አንጻር ደግሞ በመደበኛ ወይም በቅጥር ወደ ስራ ገበያው የሚቀላቀል ስራ ፈላጊ ወደ ስራው ከመግባቱ በፊት መሰልጠን ይኖርበታል ማለት ነው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ተቋሙ በዋናነት ሊያሳካቸው የያዛቸው ግቦች ምን ምን ናቸው ?

**አቶ አራርሳ ፡-** የስራና ክህሎት ጽ/ቤት ሁለት ስትራቴጂክ ግቦችን ለማሳካት ታስቦ በሁለት ዋና ዘርፎች ማለትም በስራ ስምሪትና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስራዎች ዘርፍ እና በኢንተርፕራይዝ እና ቴክኖሎጂ ድጋፍ ዘርፍ ሲደራጅ በአንድ በኩል ለዜጎች ህሎት መር ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ማሳደግና ድህነትን መቀነስ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለኢንተርፕራይዞች መንግስታዊ ድጋፎችን በማድረግ ለኢንዱስትሪ ሽግግሩ መሰረት የሚጥሉ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማፍራትና ማበራከትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በክ/ከተማችን በዘርፉ ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል ዋነኛው የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ድህነትን መቀነስ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለወጣቶችንና ሴቶች ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር የክፍለ ከተማችንን ነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሚደረገው ርብርብ የተለያዩ የቅድመ ስራ እድል ፈጠራ ስራዎችን በማከናወን ለስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር የመንግስት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶችና ነባር ኢንተርፕራይዞች ሊፈጥሩ የሚችሉ ጸጋዎችንና ክፍት የስራ መደቦችን በጥናት በመለየት ለክ/ከተማው ነዋሪዎች እና ስራ ፈላጊዎች በዘርፉ ተግባራት ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ወጣቶችንና ሴቶችን በስራ ፈላጊነት እንዲመዘገቡ በማድረግ ስራ ፈላጊዎች ያላቸውን እውቀት እና ትኩስ ጉልበት ተጠቅመው እንዲሁም እንደ ከተማ ያሉንን ውሱን ሃብቶች በፍትሃዊነት በመደገፍና የስራ እድል በመፍጠር አመርቂ ውጤት ማስመዘገብ ሌላኛው ግባችን ነው፡፡ ከቅድመ ስራ እድል ፈጠራ እና ስራ እድል ፈጠራ አኪያ ባለፉት 6 ወራት ከተከናወኑ ተግባራት መካከል የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም 17,471 ስራ ፈላጊዎችን በመመዝገብ እና በተለያዩ የግል እና የመንግስት ተቋማት እንዲሁም የተለያዩ ኢንተርፕራዞችና ኢንዱስትሪዎች ከ18,000 በላይ ክፍት መደቦችንና ጸጋዎችን በመለየት በከተማ ግብርና፣ ኢንዱስትሪ እና ንግድና አገልግሎት ዘርፎች ለ11,769 የክ/ከተማችን ነዋሪ ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ 6,485 ሴቶች ሲሆኑ 5,226 ወጣቶች ከመሆናቸውም ባሻገር የተፈጠረው የስራ እድል ቋሚ የስራ እድል ነው፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ከ458 በላይ ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተዋል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በከተማ ምግብ ዋስትና እና ስራ ፕሮጀክት እና በወጣቶች ስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክት እየተሰራ ያለውን ስራ ቢገልጹልን?

**አቶ አራርሳ፡-** በከተማ ምግብ ዋስትና እና ስራ ፕሮጀክት በክ/ከታማችን ዝቅተኛ ነዋሪዎችን የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ በተጨማሪ ፋይናንስ ተጠቃሚ የነበሩ የ607 አባወራ እማወራ ተወካዮች 1,807 የቤተሰብ አባላት በአንድ በኩል በአካባቢ ልማት ስራ አካባቢያቸውን እያጸዱ እና እያለሙ በሌላ በኩል ደግሞ ገቢ እያገኙ ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን በ2 ዓመት ቆይታቸው የተፈቀደላቸው ግራንት ተለቆላቸው ቁጠባቸውን በመጨመር 100% በመረጡትና በሰለጠኑበት ዘርፍ ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ በሌላ በኩል በመንግስት ማችንግ ፈንድ በተመደበ በጀት በ3,382 አባወራ እማወራዎች ስር 10,931 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከወጣቶች ስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክት ስራ አንጻር በ3ኛ ዙር ብቃት የወጣቶች ስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክት ተጠቃሚ በሆኑ 4 ወረዳዎች ልምምዳቸውን ያጠናቀቁ 775 ወጣቶችን ሙሉ በሙሉ ተቀጣሪ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በመንግስት በጀት በሚካሄድ የወጣቶች ስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክት በሁለት ወረዳዎች 300 ወጣቶችን በማለማመድ ለማስተሳሰር በተያዘው እቅድ መሰረት ምዝገባና ምልመላ ተጠናቆ 375 ወጣቶች የህይወት ክህሎት ስልጠና ወስደዋል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለኢንተርፕራይዞች ወይም ለአምራቾች በጽ/ቤታችሁ የሚደረጉ ድጋፎች ምን ምን ናቸው?

**አቶ አራርሳ ፡-** ለኢንተርፕራዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች ከሚሰጡ ድጋፎች መካከል የቁጠባ፣ ብድርና የመሳሪያ ሊዝ ብድር ማመቻቸት፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት፣ የንግድ ልማት አገልግሎት፣ የገበያ ትስስር ድጋፍ፣ የእድገት ደረጃ ሽግግር ድጋፍ፣ የመስሪያ ቦታ አቅርቦት፣ የምርት እና ምርታማነት ልኬት እና መሰል ድጋፎች ይገኙበታል፡፡ ከዚህ አኪያ ለኢንቨስትመንት መሰረት የሆነው ቁጠባ በመሆኑ የዘርፉ አንቀሳቃሾች በቁጠባ ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ ጨብጠው ወደ ቁጠባ እንዲገቡ ሰፊ ስራ ተሰርቷል፡፡ ብድር ከማመቻቸት እና ማስመለስ አንጻር በከተማ ግብርና፣ በንግድ፣ በአገልግሎትና በኮንስትራክሽን ለተደራጁ ኢን/ዞች ብድር የተመቻቸ ሲሆን በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተደራጁ ኢንዱስትሪዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየተሰራ ነው፡፡ በተጨማሪም ለኢንተርፕራይዞች የኦዲት አገልግሎት ድጋፍ፣ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት እና በየደረጃው የእድገት ደረጃ ሽግግር ድጋፍ ማድረግ ተችላል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በግማሽ አመቱ ከተከናወኑ ተግባራት በጥንካሬ የሚገለጹና ተሞክሮ ሊሆኑ የሚችሉ ስራዎች ካሉ?

**አቶ አራርሳ፡-** በጽ/ቤቱ በጅምር ደረጃም ቢሆን በ2018 በጀት አመት ባለፉ 5 ወራት የተመዘገቡ አበረታች ውጤቶች ያሉ ቢሆንም አሁንም ያልተቀረፉ ማነቆዎች አሉ፡፡ እነዚህን ማነቆዎች በመፍታት ተቋማዊ አቅም በመገንባት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ነዋሪዎች በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በማሳተፍ፣ የስራ ስምሪት አገልግሎትን በማስፋፋት እንዲሁም የኢንተርፕራይዞችና የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ ክትትልና ድጋፍ በማጠናከር የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም፣ የምርት ጥራት፣ በሀገር ውስጥ መመረት የሚችሉ ምርቶችን በስፋት በማምረት የሀገር ውስጥ ገበያን ማረጋገጥ፣

የኢንዱስትሪ ሰላምን በማረጋገጥና ምቹ የስራ ሁኔታ በመፍጠር አሠሪና ሠራተኛን የሚመለከቱ የህግ ማዕቀፍች ተፈጻሚነት በማረጋገጥ የአሠሪና ሠራተኛ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎትን በማጠናከርና በማጎልበት ከአደጋ ስጋት ነጻ የሆነ ምቹና ጤናማ የሥራ አካባቢ በመፍጠር ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ በጥንካሬ የሚገለጽ የዘርፉ ዋናው የትኩረት መስክ ነው፡፡

**ልደታ ፋና፡-**በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ?
**አቶ አራርሳ ፡-** የስራና ክህሎት ጽ/ቤት የክህሎት ልማትን፣ የስራ እድል ፈጠራ ስራንና ተጠቃሚነት ማረጋገጥን፣ የኢንስትሪ ሰላም ማስፈንን እንዲሁም የተቋም ግንባታ እሳቤዎችን ለማሳካት ሰፊ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተልኮዎችን ወስዶ እየሰራ ያለና የሃብት ክፍፍል ፍትሃዊትና የህብረተሰበብ ተጠቃሚነት የሚረጋገጥበት ዘርፍ እንደመሆኑ መጠን ለስኬቱ የበርካታ ተቋማትንና ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎና ርብርብ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ለክ/ከተማችን ነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንዲሁም የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመቅረፍና የዘርፉን ተግባራት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈጸም ውስጣዊ አሰራርን በማጠናከርና ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ትስስር በመፍጠር በተለይም የወጣቶችን እና የምሩቃንን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል እያልኩ ሚዲያውም የዘርፉን ስኬቶችና ጉድለቶች በመፈተሽ ስኬቶችን እያሰፋ ጉድለቶቹ የሚታረሙበትን መንገድ በማመለከት በኩል የተጀማመሩ ስራዎችን በማጠናከር ሚናውን ይወጣ የሚል መልእክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ስለ ቃለ መጠይቁ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ እናመሰግናለን፡፡
**አቶ አራርሳ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

## የእንደራሲዎች ሚና

ምክር ቤቱ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 ዓ/ም የተቋቋመ ሲሆን የተቋቋመበት ዋናዋና ዓላማዎች የአስፈጻሚውን አካል አሰራር መመርመር ፤መደገፍ፤አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም እርምጃ መውሰድ ፤የተለያዩ ሹመቶችን ማፅደቅ ወይም እንዳግባብነቱ መስጠት ወይም መሻር የከተማውን የአጭር እና የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት እቅድና ዓመታዊ በጀት መርምሮ ማፅደቅ እና አፈፃጸሙን መከታተል ነው፡፡ናቸው፡፡ እኛም የህዝብ ምክር ቤቶች በአስፈጻሚ አካላት ላይ የሚያካሂዱትን የክትትልና የቁጥጥር ሥራ በምክር ቤቱ የአሠራር ደንብና የክትትል ቁጥጥር መመሪያ መሰረት ምን ይመስላል የሚለውን አስመልክቶ ከልደታ ክፍለ ከተማ ምክር ቤት ዋና አፈ-ጉባኤ የተከበሩ አቶ ዘሪሁን ሽፈርዳ ጋር ቆይታ አድርገናል መልካም ንባብ፡፡



### አቶ ዘሪሁን ሽፈርዳ
### የልደታ ክ/ከተማ ምክር ቤት አፈ- ጉባኤ

**ልደታ ፋና፡-** ለአስፈጻሚ አካላት በምን ዓይነት መንገድ ክትትልና ቁጥጥር ታደርጋላችሁ?
**አቶ ዘሪሁን፡-** ምክር ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት አስፈጻሚ አካላት እቅዳቸውን ለምክር ቤት እንዲልኩ በማድረግ እቅዳቸውን መርምሮ ክፍተትና ጥንካሬያቸውን በግብረመልስ ያሳውቃል፡፡ በእቅዳቸው መሰረትም አፈጻጸማቸውን በየጊዜው በሪፖርት ከመከታተል ባሻገር በአካል ወርዶ በሱፐርቪዥንና በመስክ የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፡፡ የታዩ ክፍተቶችም እንዲታረሙ ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡ በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት በወቅቱ የማይስተካከሉ ከሆነ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በአስፈጻሚ አካላት ላይ የሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር በአገልግሎት አሰጣጥ ላይና በመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች እያስገኘ ያለውን ውጤት ቢገልጹልን
**አቶ ዘሪሁን፡-** እንደ ምክር ቤት ለአስፈጻሚ አካላት ድጋፍና ክትትል

ከማድረግ ባሻገር በተገልጋይ ቀን አገልግሎት አሰጣጡ ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ ድንገተኛ ምልከታ ያደርጋል፣ መጠይቅ አዘጋጅቶ ከተገልጋዮች ሀሳብና አስተያየት ይቀበላል፤ ጥናት አድርጎ ግኝቱን በየጊዜው ከአስፈጻሚ አካላት ጋር ይገመግማል፣በጥናት የተደገፈ መረጃ ያቀርባል፤ ክፍተቶች እንዲስተካከሉ በየጊዜው በሚደረጉ ክትትሎች በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ አዳጊ ለውጦችን ማየት ችለናል፡፡ በየተቋማት የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን እየለየን ጥብቅ ክትትል በማድረጋችን ህዝባችን የሚመሰክራቸው በርካታ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ተፈተዋል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የህዝብ ጥያቄ ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ እንዲያገኝ እየተሰራ ያለው ስራ ምን ይመስላል?

**አቶ ዘሪሁን፡-** ምክር ቤታችን በጉባዔና በልዩ ልዩ መድረኮች የሚነሱ የህዝብ ጥያቄዎችን በመለየት ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ በመጠመር በየደረጃው ላሉ አስፈጻሚ አካላት አስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጥባቸው ይልካል፡፡ ከላከም በኋላ ተፈጻሚነታቸውን በሱፐርቪዥንና በአካል መስክ ወርዶ ያረጋግጣል ተደጋጋሚ ክትትል ያደርጋል፡፡ አስፈጻሚ አካላትም ህዝባችን የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች በፍጥነት እየፈቱ ለምክር ቤታችን በግብረ መልስ እንዲያሳውቁ የምናደርግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግተን እየሰራን ነው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የምክር ቤት አባላት ከመረጣቸው ህዝብ ጋር በሚያደርጉት ውይይት የመጣው ውጤት ምንድን ነው?

**አቶ ዘሪሁን፡-** በየጊዜው በምናደርገው የመራጭ ተመራጭ መድረክ ቀደም ብለው ተነስተው የነበሩ ጥያቄዎች መፈታታቸውን በተጨባጭ ጥያቄዎችን ካነሳቸው ህዝብ ጋር በውይይት ወቅት የማረጋገጥ ስራ እንሰራለን፡፡ የመድረኩ ተሳታፊዎችም ከዚህ ቀደም እንደነበረው ማማረር ብቻ ሳይሆን ለበርካታ ጥያቄዎች መፈታት አመስጋኝ መሆናቸው ለመጣው ለውጥ ትልቅ ማሳያ ነው፡፡ ምክር ቤታችንም የሚነሱ የህዝብ ጥያቄዎች ምላሽ እስኪያገኙ ድረስ በተደጋጋሚም ቢሆን ይዞ ትግል ስለሚያደርግ በርካታ ለውጦች መመዝገባቸውን በተጨባጭ አረጋግጠናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ ቢገልጹልን?

**አቶ ዘሪሁን፡-** በ2018 ዓ/ም በክ/ከተማው ነዋሪ የሚነሱ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ እንዲያገኙ ባደረግነው ከክትትልና ቁጥጥር በየደረጃው የሚገኙ የክ/ከተማችን አስተዳደር ጥያቄዎቹን በቅንነት ወስዶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመፍታት ባደረገው ቅንጅታዊ ርብርብ ውጤታማ ስራ መኖሩን በመስክ ምልከታ እና በሱፐርቪዥን ስናረጋግጥ ቆይተናል፡፡ መላው የም/ቤታችን አባላትም ደከመን ሰለቸን ሳንል በክ/ከተማችን ነዋሪ በየጊዜው የሚነሱ አዳጊ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ እንዲያገኙ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን እንዲፈቱ የክትትልና የቁጥጥር ስራችን ውጤታማ በማድረግ እጅ ለእጅ ተያይዘን ለላቀ ውጤት መትጋት እንዳለብን ላስገነዝባችሁ እወዳለሁ፡፡

## ለማህበረሰቡ ፈጣን ምላሽ እየሰጠ ያለ ተቋም

ቤት ለሰዉ ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ተብሎ ከተቀመጡ ጉዳዮች መካከል ዋነኛ ተጠቃሽ ነዉ፡፡ በየጊዜዉ እየጨመረ የመጣዉ የሰዉ ልጅ ቁጥርና የቤት ፍላጎት አለመጣጣም ደግሞ መጠለያ አልባ በመሆን ለተለያዩ ችግሮች ሲጋለጥ ይታያል፡፡ በተሻለ ኢኮኖሚ የሚገኝ የራሱ ቤት ባይኖረዉም ተከራይቶ መኖር የሚያስችል አቅም ካለዉ እየተከራየ ኑሮዎን ሲገፋ አቅም የሌለዉ ግን የማያዛልቅ ግን ጊዜያዊ መጠለያ በየጫካዉ፣በየስርቻዉና ሌሎች አማራጮች በመጠቀም ይኖራል ይሄ ግን እስከመቼ በማለት መንግስት በቤት ጉዳይ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት ይገኛል፡፡ የልደታ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤትም በመንግስት የወረደለትን የትኩረት አቅጣጫ በመተግበር ለነዋሪዎቹ የቤት ጥያቄ ምላሽ መስጠትና ፍላጎት ማጣጣም ላይ ትኩረት አድርጎ ዉጤት ተኮር ስራን እየሰራ ይገኛል፡፡ ማህበረሰቡም የራሱ ቤት እንዲኖረዉ ለማስቻል አግባብነት ባለዉ መንገድ ለሚያቀርበዉ አቤቱታና ቅሬታ ምላሽ ለመስጠት ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ከክፍለ ከተማዉ አስተዳደር ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑ ይታወቃ፡፡ ከእዚሁ ጉዳይ ጋር ልደታ ፋና ከልደታ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ገመቹ ጌታቸዉ ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርጓል በንባብ ተከታተሉን!

**ልደታ ፋና፡-**ጽ/ቤቱ የነዋሪዉን የቤት ፍላጎት ለማሟላት ያከናወነዉ ተግባር ምንድነዉ?

**አቶ ገመቹ፡-** ልደታ ክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት የነዋሪዎች የቤት ፍላጎትን በተግባር ለማሟላት በተለያዩ እቅዶችና አቅጣጫዎች ላይ ተግባራዊ ስራዎችን እየፈጸመ ይገኛል፡፡ ይህም ሲባል የነዋሪዎችን የቤት ፍላጎት ለማሟላት ያከናወነው ተግባር ሰፊ ነዉ ማለት ይቻላል፡ ኮሚቴ በማቋቋም ህገ-ወጥ ቤቶችን በመለየትና በመከታተል እያስለቀቅን እንገኛለን፡፡ ቤቶችን ተረክበን ከጨረስን በኋላ ለተቸገሩ ነዋሪዎቻችን በግልፅኝነት እና በፍትሀዊነት የምናስተላልፍ ይሆናል፡፡ የነዋሪዎቻችን የቤት ተጠቃሚነት ችግሮችን ለመፍታትና ለመቅረፍ በአስተዳደሩ አቅም የተለያዩ ፕሮጀክትን በመንደፍ የቤት ግንባታን እያከናወን እንገኛለን፡፡



## አቶ ገመቹ ጌታቸው
## የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-**በቤት ዙሪያ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመቀነስ ምን ተሰራ?
**አቶ ገመቹ፡-** በነዋሪዎች በኩል የሚነሱ በርካታ ቅሬታዎች ነበሩ አሁን ላይ ግን እነዚህን ቅሬታዎች እንዲቀንሱ ስልት በመንደፍና ወደ ተግባር በመቀየር ከበፊቱ በተሻለ መልኩ ቅሬታዎችን መቀነስ ተችሏል፡፡ ነዋሪዎች በተሻለ አካባቢ እንዲኖሩ እና በቤቶች መካከል የሚታዩ ቅሬታዎች እንዲቀንሱም ጽ/ቤቱ በርካታ ስራዎችን ሰርቷል፡፡

- >የቅሬታ መቀበያና መመርመሪያ ሂደትን ማዘመን፣
- >ቅሬታ በፍጥነት እንዲመለስ የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት መጠቀም፣
- >ከነዋሪዎች ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ ኮሚቴዎችን መቋቋም፣
- >የማህበራዊ ውይይትን በመደበኛ መንገድ ማካሄድ በመንደሮች የሚፈጠር ግጭቶችን በአካል በየወረዳ በመውረድና ነዋሪዎችን በማወያየት ችግሮችን እየፈታን እንገኛለን፡፡
- >ነዋሪዎቻችንን በመድረክ በማወያየት ግልፅኝነትን እየፈጠርን እንገኛለን፡፡

**ልደታ ፋና፡-**የተገልጋዩን እንግልት ለመቀነስ የተሰሩ ስራዎች ካሉ?
**አቶ ገመቹ፡-** በነዋሪ አገልግሎት ላይ የሚኖረውን የጊዜና የሂደት እንግልት ለመቀነስ፣ ጽ/ቤቱ ተግባራዊ ስራዎችን እየካሄደ ይገኛል፡፡ ነዋሪዎቻችን የውል እድሳታቸውን በቴሌ ብር ከፍለው ውላቸውን እንዲያድሱ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህ ማለት እንደ ከዚህ ቀደሙ ገቢዎች ሄደው የሚከፍሉት ክፍያ አይኖርም ማለት ነው፡፡

የሰራተኞችን ብቃት ለማሻሻል የተለያዩ ስልጠናዎችን እየሰጠን የአገልግሎት አሰጣጥን እያሳለጥን እንገኛለን፡፡ የተገልጋዮችን አስተያየት በተደጋጋሚ መሰብሰብና መተግበር ላይ እንገኛለን፡፡ የማህበረሰቡን እንግልት ለመቀነስ አሁንም በጥናት የተደገፈ ማሻሻያ እያደረግን ሲሆን እስካሁን ባለዉ ግን አገልግሎት ፈልገዉ ለሚመጡ አካላት ያልገባቸዉን ጥያቄ ምላሽ የሚሰጡና ወረፋን የሚያስተባብሩ ባለሙያዎችን በሟማለት የቤት እድሳት ሆነ የቤት ይሰጠኝ ጥያቄያቸዉን በአግባቡ እንዲፈታላቸዉ እያደረግን እንገኛለን፡፡

በተጨማሪም የቤት ፍላጎትን ለሟሟላት ከአንድ ቤት በላይ የያዙ ህገ ወጥ አካላትን በማስለቀቅ ቤት ለሌላቸዉ ለመስጠት ጥረት እያደረግን ነዉ እስካሁን በቁጥር ብዙ ቤቶች ማስለቀቅ ችለናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ?
**አቶ ገመቹ፡-** ከምንም በላይ ለሰዉ ልጅ መጠለያ ያስፈልገዋል፡፡ ይህንን ለማሳካትና ነዋሪዉን ከቤት ችግር ለማላቀቅ ቀጣይ ሰፊ ስራዎችን እንሰራለን፡፡ መንግስትም በቤት ጉዳይ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዋናነትም በአከራይና ተከራይ ዙሪያ አዋጅና ደንብ እንዲወጣ በማድረግና ተግባራዊ በማድረግ አከራይ በየጊዜዉ የቤት ኪራይ እንዳይጨምር ማድረግ መቻሉ ራሱ ሌላኛዉ የቤት ችግር መፍትሄ ተደርጎ መዉሰድ ይቻላል፡፡ ከአንድ ቤት በላይ የያዙ ግለሰቦችን በማጣራትና በማስለቀቅ ቤት እየሰጠ መሆኑ ደግሞ ተጨማሪ ስራ ነዉ ቀጣይም ከእዚህ በተሻለ መንገድ ለመስራት አጀንዳ ቀርጾ እየሰራበት መሆኑን ነዋሪዉ መረዳት ይኖርበታል፡፡ ባለድርሻ አካላትም በእዚህ ሰዉ ተኮር ተግባር ላይ የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርበታል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ስም እናመሰግናለን
**አቶ ገመቹ፡-**እኔም አመሰግናለሁ

## ተግባር በውጤት

የልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር የነዋሪዎችን የገበያ አለመረጋጋት እና ኑሮ ውድነትን ጥያቄዎችን ለመመለስ ጽ/ቤቱ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ እነዚህም የፍጆታ ምርቶች ከደላላ ንክኪ ነፃ እንዲሆኑ በማድረግ ምክንያታዊ የዋጋ ትመና በመስራት የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት የቅዳሜና እሁድ ገበያዎችን በማስፋት፤በማዘመንና የአቅራቢዎችን አቅም በማጠናከር የትኩረት ማዕከል ተደርጎ ተሰርቷል፡፡የንግድ ቁጥጥርና ክትትል ስርዓቱን ከተለምዶዓዊ አሰራር ወደ ቴክኖሎጂ በማሸጋገር የተግባር ምዕራፍ ላይ ሲሆን በዚህም በክትትልና ቁጥጥር አተገባበር ላይ የሚነሳውን የፍትሃዊነት ችግር ደረጃ በደረጃ የመፍታት ሂደት ውስጥ ተቋሙ ገብቷል፡፡ የልደታ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽ/ቤት የገበያ አለመረጋጋትና የኑሮ ውድነትን ለመከላከል የኢንዱስትሪና የከተማ ግብርና ምርቶችን በስፋት፤በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብና የድጎማ ምርቶችን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ በማሰራጨት ውጤታማ ስራ ተሰርቷል፡፡የኑሮ ጫናን ለማቃለል ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የእሁድ ገበያዎችን በማስፋትና ህገ ወጥ ነጋዴዎችን በመቆጣጠር የገበያ ማረጋጋት ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የገበያ ማረጋጋትና የኑሮ ውድነትን ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰሩ ያሉ ስራዎች በምን አግባብ እየተከናወኑ እንደሆነ ከንግድ ጽ/ቤት ሃላፊ ወ/ሮ ተስፋነሽ ጋሻው ጋር ቆይታ አድርገናል መልካም ቆይታ፡፡





**የእሁድ ገበያን የሚያሳይ**

## ወ/ሮ ተስፋነሽ ጋሻው
## የንግድ ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** ህገ-ወጥ ንግድን ከመከላከል አንጻር ምን ስራ ተሰርቷል?

**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** በ2018 በጀት ዓመት የኮንትሮባንድና ህገወጥ ንግድ ለመከላከል የወረዳና የክፍለ ከተማ የቁጥጥር ባለሙያዎችን በማጣመር የቀጠና ስምሪት በመስጠት ከህገወጥ ንግድ ነፃ የሆነ ቀጠና የመመስረትና የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ኮንትሮባንድ ንግድ መከላከል ከሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት፤ከደንብ ማስከበር ጽ/ቤትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ስምሪት እንዲያዝ ተደርጓል፡፡ 22,250 የበርለበር ክትትልና ቁጥጥር የተደረገ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 554 ነጋዴዎች የንግድ ህጉን ጥሰው በመገኘታቸው አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ ታርመው በስራ ገበታቸው እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡ ፡ በተደረገው ክትትልና ቁጥጥር 39 ነጋዴዎች ሀሰተኛና አሳሳች የንግድ ማስታወቂያ ለጥፈው በመገኘታቸው፤61 የንግድ ድርጅቶች የጥራት ደረጃቸውን ያጓሉ የፍጆታ ምርቶች ይዘው በመገኘታቸው ምርቱን የማስወገድና ድርጅቶች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ተችሏል፡፡

የምሽት ንግድ የማለማመድ፤ወደ ስራ የማስገባት እና ወደ ተግባር አጠናክሮ የማስቀጠል ስራ ላይ በትኩረት መስራት የተቻለ ሲሆን 2,634 ነጋዴዎች አምሽተው በመስራት የነበረውን ኃላቀር የስራ ባህል በመቅረፍ የከተማችንን የስራ ባህል ገፅታ መቀየር ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የእሁድ ገበያን ከማስፋትና ተደራሽ ከማድረግ አንጻር የተሰሩ ስራዎች ካሉ ቢጠቅሱልን?

**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር የሸማቹን ህብረተሰብ መብት ለማስከበር የምርት አቅርቦት በከፍተኛ መጠን በማሳደግ የተረጋጋ የግብይት ስርዓት መፍጠር ተችሏል፡፡

የእሁድ ገበያ ተደራሽነት ማስፋት፤ያሉትን የእሁድ ገበያዎች የማዘመንና የምርት የአቅራቢዎችን አቅም በማሳደግ ባሉት 12 የእሁድ ገበያዎች የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርት በስፋት ማቅረብ ተችሏል፡፡በሁሉም የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች አቅራቢዎችን ከቸርቻሪ ወደ አምራችና ጅምላ አከፋፋይ የመቀየር ስራ የተሰራ ሲሆን ቸርቻሪዎች ያሳዩት የነበረው ከተመን በላይ ዋጋ በመጨመር መሸጥ፤የጥራት ደረጃው የተጓደለ ምርት ማቅረብና የመሳሰሉ ችግሮችን መቅረፍ ተችሏል፡፡

አምራችና አከፋፋይ አቅራቢዎችን ከአጎራባች ክፍለ ከተሞችና ከትርፍ አምራች ክልሎች በማፈላለግ ትስስር የተፈጠረ ሲሆን እነዚህ ትስስር የተፈጠረላቸው አምራቾች የግብርና ምርቶችን በስፋትና በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ችለዋል፡፡ በዚህም ያሳለፍናቸው 3 ተከታታይ ህዝባዊ በዓላት በደመቀና በተረጋጋ ሁኔታ ማክበር ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የኑሮ ውድነትን ለመከላከል የምርት አቅርቦትን ለማስተካከል ምን እየተሰራ ነው?

የምርት አቅርቦት በስፋት በማቅረብ ለሸማቹ ህብረተሰብ ተደራሽ በማድረግ በእኩል ባዛሮችን እንደመፍትሄ መጠቀም የተቻለ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ካለፉት ዓመታት ለየት ባለ መልኩ ለ2018 ዘመን መለወጫ፤ለመስቀልና ለኢሬቻ ለተከታታይ ሳምንታት በምርት አቅርቦት፤በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪነታቸው ውጤታም የነበሩ ባዛሮችን ማዘጋጀት ተችሏል፡፡የቅዳሜና እሁድ ገበያ የኑሮ ዉድነትን በማረጋጋት ትልቅ አስተዋጽዎ እያደረገ ሲሆን የተለያዩ ጥራት ያላቸዉ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ እንዲቀርቡ በማድረግ አምራችና ሸማቹን በቀጥታ እንዲገናኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

የሰብል ምርት 53,627.25 ኩ/ል ማቅረብ የተቻለ ሲሆን ከ2017 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 49,092.93 ኩ/ል ብልጫ ያለው ምርት ማቅረብ ተችሏል፡፡ 722,950 ኩ/ል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በእሁድ ገበያና ባዛሮች ማቅረብ የተቻለ ሲሆን ከ2017 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 699,849.77 ኩ/ል ምርት በአብላጫ ማቅረብ ተችሏል፡፡ ከፍተኛ የምርት አቅርቦት እጥረት የነበረበት የእንቁላል አቅርቦት ሲሆን ችግሩን ለመቅረፍ 2,178,639 ኩ/ል ማቅረብ ተችሏል፡፡

**የእሁድ ገበያ ተደራሽትን በማስፋ፤የምርት አቅርቦትን በማሳደግ እና የአቅራቢ መጠንን በማሳደግ የተገኙ ውጤቶች፤**

በከፍተኛ መጠን እየናረ የነበረውን የኑሮ ውድነት በመግታት የህብረተሰቡ የእለት ከዕለት ፍላጎት የሆኑትን የፍጆታ ምርቶችን በመጠን፤በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ተችሏል፤የቅዳሜና እሁድ ገበያ የኑሮ ውድነቱን በከፍተኛ ደረጃ እንዲረጋጋ ማደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ የገበያ ቦታው በመኖሪያ አከባቢዎችና በአቅራቢያቸው የተመቻቸ በመሆኑ ሸማቹ ህብረተሰብ ካለምንም እንግልት ምክንያታዊ በሆነ ዋጋ በአንድ ማዕከል እንዲሸምት አስችሎታል፤ለአምራቾችና እና ጅምላ አከፋፋዮች ካለምንም የደላላ ጣልቃ ገብነት እንደ አንድ የገበያ አማራጭ እንዲጠቀሙት አስችሏል፤(አምራችና ሸማችን በቀጥታ በማገናኘት ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የንግድ ፍቃድ ቁጥጥርን በተመለከተ የተሰሩ ስራዎች ቢጠቀሱልን?

**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** በክትትልና ቁጥጥር ተግባር የመጡ ለውጦችን ስናይ፡-ምንም አይነት የንግድ ፍቃድ ሳይዙ የሚነግዱ፤የንግድ ፍቃድ ሳያሳድሱ የሚነግዱ፤ዘርፍ የሚቀላቅሉና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ምርቶች በማስወገድና አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ የተጀመረውን ፍትሃዊ የንግድ ስርዓት የመገንባት ሂደት በማጠናከር ገቢ አቅምን ማሳደግ ማቻሉ፤አዳዲስ ነጋዴዎችን ወደ ንግድ ስርዓቱ መቀላቀል መቻሉ፤የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ምርቶች ጥቅም ላይ እንዳውሉ ተከታትሎ በማስወገድ የህብረተሰቡን ጤንነት መጠበቅ ተችሏል፤ ሰው ሰራሽ የምርት ክምችትና የዋጋ ንረት መከላከል ተችሏል፤ልኬትን የሚያዛቡ የመለኪያ መሳሪያዎች ስርዓት የማስያዝ ስራ መሰራቱ ህብረተሰቡን ከአጭበርባሪዎች መጠበቅ ተችሏል፤

**መደበኛ ያልሆነ ንግድ ስርዓት ማስያዝ**

መደበኛ ያልሆነ የንግድ ስርዓትን ወደ መደበኛ የንግድ ስርዓት በማሸጋገር ሂደት የነጋዴ ልየታ፤የቦታ ልየታና ለተለዩ ቦታዎች እውቅና የመፍጠር ተግባር ተከናውኗል፤መደበኛ ያልሆኑ ነጋዴዎች ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ በየጎዳናው የሚነግዱ በመሆናቸው ለፍትሃዊ የንግድ ስርዓት ፀር ሆነው፤የከተማውን ገፅታ በማጓደል ትልቅ ችግር ሲፈጥሩ ነበሩ፡፡ ይህንን ለማስተካከል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የንግድ ተግባርን ስርዓት ለማስያዝ በዘጋጀው ደንብ ቁጥር 184/2017 መሰረት የነጋዴ ልየታና የቦታ ልየታ በማድረግ የክፍለ ከተማና የወረዳ ግብረሃይል እንዲያረጋግጠው በማድረግ በ10ሩም ወረዳዎች የቦታ ዝግጅት ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የከተማውን ስታንዳርድ በጠበቀ መልኩ በመመሪያው መሰረት መስፈርቱን ያሟሉ 5 ገበያዎችን ወደ ስራ ማስገባት የተቻለ ሲሆን ለ355 መደበኛ ያልሆኑ ነጋዴዎች የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ሌሎች ቦታዎች መመሪውን መሰረት በማድረግ ግንባታውን አጠናቆ ወደ ስራ ለማስገባት በክትትል ላይ የሚገኙ ሲሆን ከ2 ዓመት በኃላ ለሚደረገው ወደ መደበኛ የንግድ ስርዓት የማሸጋገር ተግባራት ከአሁኑ ነጋዴዎችን የመደገፍና የማዘጋጀት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** አገልግሎቶችን በኦንላይን ከመስጠት አንፃር የተገኙ ጠቀሜታዎች

**ወ/ሮ ተስፋነሽ፡-** የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በኦንላየን እንዲሰጥ የተደረገ ሲሆን ይህም ነጋዴዎች የግል ስልካቸውን በመጠቀም ራሳቸው አገልግሎቱን ማግኘት የሚችሉበት ደረጃ ተደርሷል፡፡ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ካለምንም መጉላላት ስራቸውን እየሰሩ የንግድ ፍቃድ ማውጣትና ማደስ የሚችሉ ሲሆን አስቸጋሪ ነገር ከገጠማቸው ባለሙያዎች እገዛ እንዲያደሩ ተደርጓል፡፡ ጊዜ ከመቆጠብ አንፃር፡- ቀደም ሲል የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በማኑዋል በሚሰራበት ጊዜ ተገልጋይ በአካል ቢሮ መምጣት ስለሚያስፈልገው ሱቁን ሳይከፍት ጊዜውን በመንገድ ያጠፋ የነበረውን አሁን ቢሮው ቁጭ ብሎ ስራውን እየሰራ በኦንላን ብቻ የሚፈልገውን አገልግሎአት ስለሚያገኝ ጊዜውን ይቆጥባል፤ ወጪ ከመቆጠብ አንፃር፡- ለተገልጋዩ የትራንስፖርት ወጪ እና የስራ ጊዜን ቆጥቧል፤ ለመንግስት ተቋም/ለንግድ ቢሮ ቀደም ሲል ለካርድ ህትመት የሚያወጣው ወጪ ለቀለም፣ ለወረቀት፣ ለደረሰኝ ህትመት፣ የሰራተኛ ደሞዝ በትንሽ የሰው ኃይል ስለሚሰራ የመሳሰሉትን ወጪ ይቀንሳል፡፡ ሌብነትና ብልሹ አሰራርን ከማስቀረት አንፃር፡- ስራው በቴክኖሎጂ/በኦንላይን ስለሆነ ያለ አግባብ የሚሰሩ ስራዎችንና በድግግሞሽ የሚጠየቁ የድርጅት ስሞችን እንዳይሰጡ ማድረግ መቻሉ እንዲሁም ያለ አግባብ የተሰሩ ስራዎችን ማን መቼ እንደተሰራና እንደሰራ በግልፅ ማወቅ መቻሉና የተጠያቂነት ስርአት ለማስፈን ማስቻሉ የተገልጋይ እርካታ ከመጨመር አንፃር፡- በተለይ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶች በኦን ላይን መሆናቸው የተገልጋዩን ጊዜና ወጪ በመቆጠቡ እንዲሁም ባሉበት ሆነው ፈጣን አገልግሎት በማግኘታቸው በተጨማሪም ከቦታ ርቀት የተነሳ ቅጣት ከመግባት በመዳናቸው የተገልጋዩ እርካታ በጣም ከፍተኛ መሆኑ፡ ፡ በአጠቃላይ አገልግሎት አሰጣጣችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻልንና እያዘመንን በመምጣታችን የተገልጋዩን እርካታ እያሻሻልን እንገኛለን በመሆኑም በቀጣይም ሁሉንም አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ለመስጠት መስራት ይጠበቅብናል፡፡

## የትዉልድ ግንባታ ለሃገር እድገት

ትምህርት የእውቀት ምንጭ ነው፤ እውቀት ደግሞ ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ዕድገትና ውስብስብ ችግሮች መፍቻ መሳሪያ መሆኑ በፍልስፍና፣ በሳይንስና በተግባር ተሞክሮ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡ ፡ በነዚህ ዕውነታዎች መነሻነት በዓለማችን ለተከሰቱ ህብረተሰባዊ ለውጦች /Societal Transformation/ ትምህርት የማይተካ ሚና አለው፡፡የልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት የተሰጠውን ተግባርና ሀላፊነት መሰረት የሀገሪቱን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም ጥራት ያለው አጠቃላይ ጥራት ያለው ትምህርት ለክ/ከተማው ነዋሪዎች በፍትሃዊነት ተደራሽ ለማድረግ እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በማስፋፋትና የመማርና ማስተማር ሂደት በበላይነት በመምራት ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

የትምህርት ሽፋን ተደራሽነትና ጥራትን ለማረጋገጥ የለውጡን ኃይል በመጠቀም ዜጎችን በእውቀት፣ በአመለካከትና በክህሎት በማነጽ ለሀገር ምጣኔ- ሀብታዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እሴቶችን የሚያስተገብር ብቃት እንዲኖር የሚያስችል አደረጃጀት ተፈጥሮ ለዘላቂ ልማትና እድገት ትምህርት ወሳኝ ሚና እንዲኖረው ሰፊ ሥራ ተከናውኗል። በተለይም በትምህርት ዘርፉ በተደረገው በሃገራዊ ሪፎርም የ6ኛ እና 8ኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተናዎች እና የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተናዎች የተማሪዎችን ውጤት ማላቅ ከተማ አቀፍ ስትራቴጂ በጥብቅ ዲሲፕሊን እንደ ክ/ከተማ የማጠናከሪያ ትምህርቶችና የመማማሪያ መድረኮች እንዲካሄዱ ተደርጓል።

በሁሉም የትምህርት እርከኖች የመማሪያ ቁሳቁስ ግብአት አቅርቦት ስርጭት እና የተማሪዎች ምገባ አገልግሎት በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ከፍተኛ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጓል። በ2018 የመጀመሪያው የትምህርት ዘመን የተመዘገበዉን አበረታች ውጤት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀምና አጠናክሮ በማስቀጠል የታዩ ጉድለቶችንና ችግሮችን ለይቶ በማስተካከል በቀጣይ በተለይም የተማሪዎችን ውጤትና ስነ-ምግባር ለማሻሻል በታቀደዉ ዕቅድ መሰረት ስትራቴጂክ ግቦች የትምህርት ማህበረሰቡ ትኩረት ሰቶ ከሰራ ከዚህ የበለጠ ዉጤት ሊመዘገብ እነደሚችል ያለዉ ተስፋ ሰጭ እንቅስቃሴ በደንብ ያሳያል።

በ2018 ዓ.ም የት/ት ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ እያከናወኛቸዉ የሚገኙ ስራዎችን በምን አግባብ እየተከናወኑ እንደሆነ የዝግጅት ክፍላችን ከጽ/ቤቱ ሃላፊ ወ/ሮ በላይነሽ ሞሲሳ ጋር ጥያቄዎችን በማቅረብ የሰጡንን ማብራሪያ እንዲህ አቅርበነዋል መልካም ንባብ ።



ወ/ሮ በላይነሽ ሞሲሳ
የትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና ፡-** የተማሪ ቅበላ መጠን ለማሳደግ፣ ፍትሃዊ የትምህርት ሽፋንና ተደራሽነት ለማሳደግ ተከናወኑ ተግባራት

**ወ/ሮ በላይነሽ ፡-** በክ/ከተማ ደረጃ የተማሪዎች ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሁሉም ት/ቤቶች ተማሪዎቻቸውን በአግባቡ እንዲቀበሉ የህዝብ ንቅናቄ ስራዎች በማካሄድ እድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ተደርጓል።

ቴክኖሎጂን በመጠቀም ተማሪዎች እና ወላጆች ባሉበት ሆነው **በe-school system (online)** በመጠቀም ተማሪዎች እንዲመዘገቡ በማድረግ ተገልጋዮች ያለምንም መንገላታት አገልግሎት እንዲያገኑ ተደርጓል። በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከቅድመ አንደኛ እስከ 2ኛ ደረጃ በእድሜአቸው የተመዘገቡ ተማሪዎች መረጃ የማጥራት ሥራ ተሰርቷል። ከዚህ በተጨማሪ በሁሉም የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የክፍል ድልድል በሲስተም መሆኑን የማረጋገጥ ሥራዎች ተሰርቷል።

በ57 የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ቅበላ **13,950** ሲሆን በአፋን ኦሮሞ ትምህርት **388** ተማሪዎች ተመዝግበው እንዲማሩ ተደርጓል።

በ44 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቤቶች የተማሪ 31,712 ሲሆን በአፋን ኦሮሞ ትምህርት **912** ተማሪዎች ተመዝግበው እንዲማሩ ተደርጓል።

በ11 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ቅበላ **13,224** ሲሆን በአፋን ኦሮሞ ትምህርት 472 ተማሪዎች ተመዝግበው እንዲማሩ ተደርጓል

በክ/ከተማ ደረጃ ባሉን **112** የትምህርት ተቋማት በ2018 ዓ/ም **60,658** ተማሪዎች ተመዝግበው እንዲማሩ ተደርጓል።



**የትምህርት ቤት መክፈቻ**

**ልደታ ፋና ፡-** በትምህርት ለትውልድ ስራዎች የመጣ ውጤትና ትምህርት ቤቶችን ለማሻሻል፣ ደረጃቸውን እንዲያድግ ከማድረግ አንጻር ያላቸው አስተዋጽኦ

**ወ/ሮ በላይነሽ ፡-** የተማሪ ዉጤትና የትምህርት ቤቶችን ደረጃቸውን ለማሻሻል ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችን በማከናወን ከግል ባለሃብቶች፣ ከግብረ-ሰናይ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት ጋር በማቆራኘት በገንዘብ **1,159,325** በጉልበት **17,039,913** በቁሳቁስ 96,452,644 እና በእውቀት **14,935,684** በአጠቃላይ **129,587,566** ሃብት በማሰባሰብ በየትምህርት ተቋማቱ የመማሪያ ክፍል ግንባታ ተከናወኗል። የትምህርት ተቋማትን ምቹና ማራኪ ለማድረግ የቴራዞን ንጣፍ መስራት ተችሏል። በሁሉም ት/ቤቶች የትምህርት ግብዓት ማሟላት ተችሏል።ትምህርት ቤቶች የግቢ ማስዋብና የልዩ ፍላጎት የራምፕ ስራ ተሰርቷል።

በሁሉም ት/ቤቶች የትምህርት አጋዥ ማጣቀሻ መጽሃፍት እንዲሟላ ተደርጓል ።የተማሪ መማሪያ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች ማሟላት ተችሏል። በአብዛኛው ት/ቤቶች የላብራቶሪ ግብዓቶች ማሟላት ተችሏል።የትምህርት ግብዓቶችን በማሟላት ተቋማት ደረጃቸው እንዲሻሻሉ ተደርጓል። የትምህርት ለትውልድ ስራዎች በመከናወናቸው የተማሪዎች ውጤት ማሻሻል ተችሏል።



**በትምህርት ለትዉልድ የተሰሩ ስራዎች**

**ልደታ ፋና ፡-** የአካቶ ትግበራ ስራዎች ከትምህርት ፍታሃዊ ተደራሽነት አንጻር ያለው ፋይዳ እና ትግበራው ያለበት ደረጃ

**ወ/ሮ በላይነሽ ፡-** የልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ በህብረተሰቡ መካከል ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ ስራ መስራት ተችሏል፤የልዩ ፍላጎት እና የአካቶ ትምህርት **11** ድጋፍ መስጫ ማዕከላትን ማስፋፋት እና ለማዕከላት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በማሟላት **1,600** የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለደረጃው ብቁ የሆኑ እና በዘርፉ የሰለጠኑ መምህራን መመደብ ተችሏል። በሌላ በኩል ሁሉም ትምህርት ቤቶች በልዩ ፍላጎት ተማሪዎች አመቺ እንዲሆኑ የትምህርት ቤት የመሰረተ-ልማት ማስፋፋት ስራዎች ተከናውነዋል።



**ተማሪዎች ሲማሩ የሚያሳይ**

**ልደታ ፋና ፡-** የጎልማሶች ትምህርት ያለበት ሁኔታ ቢገለጽ

**ወ/ሮ በላይነሽ ፡-** የትምህርት ዕድል ያላገኙ ጎልማሶች በቤት ለቤት በቆጠራ በመለየት **16** በአማርኛ **6** በአፋን ኦሮሞ በድምሩ **22** የመማሪያ ጣቢያዎች ተለይተው በቂ ግብዓትና አሰራር ስርዓት ተዘርግቶ **278** ተማሪዎች በተቀናጀ የጎልማሶች ትምህርት በመሰጠት ላይ ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪ በብርሃን ምዘና ተመዝነው **50** እና በላይ ውጤት ያመጡ ጎልማሶች ከልደታ ማኒፋክቸሪንግ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በተለያ የሙያ ዘርፎች የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል።

**ልደታ ፋና ፡-** መጠነ ማቋረጥና መጠነ መድገም ችግሮችን ለመቅረፍ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች

**ወ/ሮ በላይነሽ ፡-** በክ/ከተማ ደረጃ በ**19** ቅድመ አንደኛ ደረጃ እና በ20 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች **22,337** ተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም **(School feeding Program)** የምገባ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል። በሌላ በኩል የትምህርት ቁሳቁሶች እና የደንብ ልብሶች እንዲያገኙ ተደርጓል። ይህም በመሆኑ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር **0.05%** እንዲዲቀንስ ተደርጓል። ከዚህም ባሻገር ትምህርት ቤቶች ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ወላጆች ለሚመጡ ተማሪዎች በመምህራንና በበጎ አድራጎት ክበብ የሚደረገውን ድጋፍ አጠናክሮ ማቀጠል ተችሏል። መምህራን ተማሪዎቻቸዉን እንደ ትምህርት አቀባበላቸው በመለየት የማብቃት ስራ እንዲሰሩ የተደረገ ሲሆን የተማሪዎችን ክፍተት በመለየ አሳታፊ የማስተማር ስነ-ዘዴን በመጠቀም፣ የተከታታይ ምዘናዎችን እና የማጠናከሪያ ትምህርቶች ተጨባጭ ውጤት ስለመምጣቱ መከታተል ተሰርቷል።

**ልደታ ፋና ፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ በላይነሽ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# አቅም የገነባ ተቋም

የልደታ ክፍለ ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት የህዝብና የመንግስት ጥቅም ተጠበቆ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን በትጋት እየሰራ ይገኛል።ተቋማት እና ግለሰቦች በህግ አግባብ ተደግፈው ስራዎችን እንዲከውኑ ለማስቻል የንቃተ ህግ እና የህግ- ስርጸት ስራዎችን በስፋት በመስራት ውጤታማ ሆኗል። ተቋሙ የማስፈጸም አቅሙን በየጊዜው እየገነባ መንግስት ጥቅሙን እንዳያጣ በማድረግ ላይ ነው። ጽ/ቤቱ የማስፈጸም አቅሙን በመገንባት የመንግስትን ጥቅም ለማስጠበቅ እየሰራቸው ያሉ ስራዎችንና ሌሎች ስራዎችን አስመልክቶ ከጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ ወርቁ ከተማ ጋር ቆይታ አድርጋለች በጥሞና ተከታተሉን መልካም ንባብ።



## አቶ ወርቁ ከተማ
## የፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** የመንግስትን ጥቅምን ከማስከበር አንጻር ምን ያህል መዝገቦች ላይ ክትትል አደረጋቹህ?

**አቶ ወርቁ፡-** የከተማ የአስተዳደሩን መብትና ጥቅም ከማስጠበቅ አንፃር የፍ/ብሔር መዝገቦች አፈፃፀምን ስንመለከት ካለፈው የዞሩ **101** መዝገቦችንና አዲስ የመጡ **63** መዝገብ ላይ በአጠቃላይ **164** ያህል መዝገቦች ላይ ክትትል ተደርጓል።

**ልደታ ፋና፡-** ክትትል ከተደረገባቸው መዝገቦች ውስጥ ምን ያህሉ ውሳኔ አገኙ ?

**አቶ ወርቁ፡-** ክትትል ከተደረገባቸው መዝገቦች ውስጥ 65 መዝገቦች ላይ በፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን ውሳኔ ካገኙት መዝገቦች ውስጥ **6** ለመንግስት ሲወሰን **5** መዝገቦች በመንግስት ላይ ተወስኗል። **3** መዝገቦች ላይ ይግባኝ ተጠይቆባቸዋል በሂደት ላይ ያሉ መዝገቦች ብዛት **102** ናቸው።

**ልደታ ፋና፡-** በፍትሐብሔር ክርክር ከተወሰኑት መዝገቦች መንግስት ሊያጣው ይችል የነበረ ምን ያህል ገንዘብ አዳናቹህ ?

**አቶ ወርቁ፡-** በፍትሐብሔር ክርክር ከተወሰኑት መዝገቦች መንግስት ሊያጣው ይችል የነበረ ብር **218,742,200 /አስራ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ብር**/ ግምት ያለው የመንግስት ጥቅም እና በአይነት **358** ካሬ ሜትር በታ ላይ ያረፈ **03** ክፍል የመንግስት ቤት ጥቅም ተከብሯል።

**ልደታ ፋና፡-**የማስወሰን አቅማቹህን ምን ያህል ይገልጹታል?

**አቶ ወርቁ፡-** የማስወሰን አቅማችንን በፐርሰንት ስናሰለው **93%** ማድረስ ተችሏል። ይህ የሚያሳየው ሙሉ አቅማችንን ተጠቅም መንግስት ጥቅሙን እንዳያጣ እየሰራን መሆኑን ነው።

**ልደታ ፋና፡-** የወንጀል ጉዳዮች ክርክር ክስ ከቀረበባቸው ውስጥ ምን ያህሉን ተጠያቂ አድርጋቹህ

**አቶ ወርቁ፡-** የወንጀል ጉዳዮች ክርክር ክስ ከቀረበባቸው **526** መዝገቦች ውስጥ **522** መዝገቦች በመርታት ወንጀሉን የፈፀሙ አካላት ተጠያቂ ማድረግ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** የዐቃቢያን ህጎችን አቅም በየጊዜው የመገንባት ስራ ትሰራላቹህ?

**አቶ ወርቁ፡-** የዐቃቢያን- ህጎችን የማስፈጸም አቅም ለማሻሻል በየጊዜው የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችን እየሰጠን እንገኛለን በዚህም ውጤታማ መሆን ችለናል።

**ልደታ ፋና፡-** በየጊዜው የሚወጡ ህጎችን በተቋማትና በማህበረሰቡ ዘንድ ለማስረጽ ምን እየሰራቹህ ነው?

**አቶ ወርቁ፡-** የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል እና የኑሮ ውድነትን መቀነስ ላይ ግብ ባደረጉ የሕግ ርዕስ ጉዳዩች ላይ በመድረክ ለ**2000** በላይ ተሳታፊዎች የንቃተ ሕግ ማሳደግ ስልጠና ተሰጥቷል፤እንዲሁም በተለያዩ የሕግ ርዕስ ጉዳዩች ላይ ከ**3500** በላይ በራሪ ጽሁፎችን በማዘጋጀት ከማህበረሰቡ እንዲደርሱ እና ግንዛቤ እንዲፈጠር ተደርጓል። በከተማችን አዲስ አበባ ሙሉ ተደማጭ በሆነው በ96.3 ሬድዮ ጣቢያ ሁለት ጊዜ የንቃተ ህግ ትምህርት ተሰጥቷል።

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን ።

**አቶ ወርቁ፡-** እኔም መረጃ እንዳካፍል ስለጋበዛችሁኝ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።

# ምቹ የስራ አካባቢ ለውጤታማ አገልግሎት

የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል በትኩረት እሰራ ይገኛል:: አስተዳደሩ አገልግሎት አሰጣጡን ፈጣን ቀልጣፋና ምልልስን የሚቀንስ እንዲሆን ለማስቻል የተለያዩ ስልቶችን ቀይሶ እየሰራ ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ አሰራርን በቴክኖሎጅ ማስደገፍ፣ ምሬት ሲበዛባቸው ነበሩ ተቋማትን ሪፎርም ማድረግ እና ለሰራተኛውና ለተገልጋይ ምቹ የስራ አካባቢን መፍጠር የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በዚህ ጽሁፍ ምቹ የአገልግሎት ስፍራ መፍጠርን አስመልክቶ ከልደታ ክፍለ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ወ/ሮ መቅደስ ያደታ ጋር ቆይታ አድረገናል ተከታተሉን፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅ ክፍሉ ስም እናመሰግናለን

**ወ/ሮ መቅደስ፡-** እኔም እንግዳ አድርጋቹህ ስለጋበዛቹህኝ አመሰግናለው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በአስተዳደሩ ለሰራተኛ እና ለተገልጋይ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የተሰራ ስራ ካለ ቢያብራሩልን?

**ወ/ሮ መቅደስ፡-** አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል እንዲቻል በተለይ ለሰራተኛውና ለተገልጋዩ ምቹ ሁኔታን እየፈጠርን ነው፡፡ ለአብነትም በአስተዳደሩ ደረጃቸውን የጠበቁ ካፌ፣ሱፐር ማርኬት፣የህጻናት ማቆያ፣ ፕሌይ ግራውንድ፣ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ፣ ቤተ-መጽሀፍት፣ የስልጠና ማዕከላት እና አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ እንዲደገፉ የማድረግ ስራ ሰርተናል፡፡



## ወ/ሮ መቅደስ ያደታ
## የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ



### የሰራተኞች ሱፐርማርኬት

**ልደታ ፋና፡-**የህጻናት ማቆያው ለሰራተኞች ምን ፋይዳ አለው?

**ወ/ሮ መቅደስ፡-** የህጻናት ማቆያው እናት የሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ልጆቻቸውን በቅርብ እየተንከባከቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ያስችላል፡ ፡ በተጨማሪም ሌላ ቦታ ለህጻናት ማቆያ አገልግሎት የሚያወጡትን ወጪ ይቀንሳል፡፡



**የህጻናት ማቆያ**

**ልደታ ፋና፡-** የሰራተኞች ካፌን አስመልክቶ ያለውን ጠቀሜታ ቢነግሩን?

**ወ/ሮ መቅደስ፡-** ካፌው የተቋቋመው መንግስት በሚያደርገው ድጎማ ነው፡፡ መንግስት በየቀኑ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ለምግብ የ40 ብር ድጎማ ያደርጋል፡፡ ሰራተኛውም ቢያንስ ለምግብ የሚያወጣውን ወጭ ይቀንስለታል፡፡ ይህም የሰራተኛውን የኑሮ ጫና ለመቀነስ በመንግስት የተወሰደ አንዱ እርምጃ ነው፡፡




**ካፌ ሲመረቅ የሚያሳይ**

**ልደታ ፋና፡-** ቤተ-መጽሀፍቱ ለሰራተኛው ምን አስተዋጾ ያደርጋል?
**ወ/ሮ መቅደስ፡-** ቤተ መጽሀፍቱ ሰራተኞች ከሚያነቡቸው መጽሀፍት አዳዲስ አሰራሮችን እንዲገነዘቡ እና ስራዎችን በእውቀት እንዲከናወኑ ያስችላል። በቤተ-መጽሀፍቱ ውስጥ ያሉ መጽሀፍት ከስራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ስለሆኑ አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጾ አላቸው።

**ልደታ ፋና፡-** ፕሌይ ግራውንድ መኖሩ ምን አስተዋጾ ያደርጋል?
**ወ/ሮ መቅደስ፡-** ፕሌይ ግራውንዱ ህጻናት በአካልም ሆነ በአዕምሮ የበለጸጉ ሆነው እንዲያድጉ ያስችላል። ህጻናት ላይ ኢንቨስት ማድረግ ደግሞ ነገን መገንባት በመሆኑ በትኩረት እየሰራንበት ነው።



**ጂም**

ልደታ ፋና፡- በክ/ከተማው ጅም መኖሩ ለሰራተኛው ያለው ፋይዳ ምንድን ነው?
ወ/ሮ መቅደስ፡- ጅሙ እጅግ ዘመናዊ ማሽኖች የተገጠሙበት ሲሆን ዓላማውም በአካልም ሆነ በአዕምሮ የበለጸገ አገልጋይ ለመፍጠር ነው።

**ልደታ ፋና፡-** አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ መደገፋቸው ምን ውጤት አስገኘ?
**ወ/ሮ መቅደስ፡-** አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ በመደገፋቸው ፈጣን፣ ተደራሽና ምልልስን የሚቀንስ አገልግሎት እንድንሰጥ በማስቻል የተገልጋይ እርካታ በላቀ ሁኔታ እንዲሻሻል ማድረግ ችሏል።



**ቴክኖሎጂዎችን የሚያሳይ**

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ እና ለሰጡን መረጃ እናመሰግናለን።
**ወ/ሮ መቅደስ፡-** እኔም አመሰግናለው።

## የገፅታ ግንባታ ስራ በልደታ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄርና ብሄረሰቦች ፣የባህላዊ እሴቶች፣ የጥንታዊ የቋንቋና የታሪክ እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) የተመዘገቡ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ተፈጥሯዊና ባህላዊ ቅርሶች ባለቤት መሆኗ ይታወቃል። በ2022 የባህልና ኪነጥበብ ዘርፍን በማላቅ ከቀዳሚ የክ/ከተማችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብልፅግና መሠረቶች አንዱ በማድረግ፤የክፍለ ከተማችንን ሕዝብ ባህላዊ፣ኪነ ጥበባዊ፣ታሪካዊ እና ተፈጥሮአዊ መስህቦችን በማጥናት፣ በመጠበቅ፣ በማልማት፣ በማስተዋወቅና ለማህበረሰቡ ተደራሽ በማድረግ እና የከተማችንን መልካም ገጽታ በመገንባት ዘላቂ የሆነ፣ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ እንዲቻል በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ እንገኛለን።



### አቶ ግዛዉ አለሙ
### የባህልና ኪነ-ጥበብ ጽ/ቤት ሀላፊ

ለጽ/ቤታችን የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶችም በባህል ተፅዕኖ ሳቢያ ማህበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ተግባራትን እንዲያከናውን፣ የባህል፣ የኪነጥበብ፣ የሥነ ጥበብና የፈጠራ ችሎታ በከተማው ውስጥ እንዲያዳብርና እንዲያሰፋ የማድረግ ተግባራትን ማከናወን በአዋጅ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ነው።

እንደ ልደታ ክ/ከ ባህል ኪነ ጥበብ ጽ/ቤት በ19 አገልግሎቶች የሚሰጡ ሲሆን ከነዚህም መካከል የእደ ጥበብ ማህበራት እንዲደራጁ የተለያዩ ሙያዊ ድጋፎችን መስጠት፤እደ ጥበብ ዘርፍ ሥልጠና መስጠት፤የባህል/በዕደ ጥበብ ምርቶች አውደ ርዕይ የማዘጋጀት አገልግሎት በዚህም ውስጥ በእደጥበብ የተሰማሩ በክፍለ ከተማችን የሚገኙ አምራቾችን ባህል ከማስተዋወቅ ባለፈ የገበያ ትስስር መፍጠር ተችሏል። የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት በባህልና ኪነጥበብ ዘርፎች በጠቃሚ የባህል እሴቶችን በማኅበረሰቡ ዘንድ የማስረፅ፤የአሉታዊ መጤ ባህሎች እና መከላከል ስልጠናና የግንዛቤ በባህል ተፅዕኖ ሳቢያ ማህበራዊ ዕድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሠራሮችን የመለወጥ ተግባሮችን ያከናውናል፤ የባህል ዘርፍ ልማታዊ አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያድርጋል፤ ባህል፣ ኪነጥበብ፣ ሥነ ጥበብ እና የፈጠራ ችሎታ በክፍለ ከተማው ውስጥ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ግብረ-ገባዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን የሚያራምዱና የሚያስፋፉ እንቅስቃሴዎችን በመከታተል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፤ህዝባዊና መንግስታዊ ከተማ አቀፍ የባህል ቀናትና ሁነቶች ከበራ ውስጥ ለምሳሌ የብሄር ብሄረሰቦች ቀን እና የመሳሰሉት ክብረ በኣላት፤ቅርሶችን የመመዝገብ አገልግሎት መስጠት ማለትም በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን በመለየት ጥናት እንክብካቤና ጥበቃ ማድረግ፤በቤተ መፅሀፍት የንባብ አገልግሎት እና የውሰጥ አገልግሎት፤ የኪነ-ጥበብ የዕይታዊ ጥበባት ኤግዝቢሽን ማዘጋጀት አገልግሎት፤የስነጹሁፍ ምሽት አገልግሎት፤በኪነ-ጥበብ ዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ሙያዊ ሥልጠና መስጠት በመጨረሻም ጽ/ቤት ተፈጥሮአዊ፤ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶቻችንን በማልማትና በማስተዋወቅ ከዘርፉ የሚገኘዉን ጠቀሜታ ወደ ላቀ ደረጃ በማሳደግ ለአገራችን ብልፅግና ግብዓት እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅብናል።

## “ተፈጥሮአዊ፤ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶቻችን ለብልፅግናችን!!”

## ፈጣን አገልግሎት በቴክኖሎጂ

በልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ፅ/ቤት ከሚደረጉት ሰፊ የግንባታ እንቅስቃሴ ካላቸዉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ አንጻር እንዲሁም መልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በመፍታት እየተሰጠ ካሉት የግንባታ ፈቃድ፣ የግንባታ ክትትል፣ የማስታወቂያ ፍቃድ እና የመጠቀምያ ፍቃድ አገልግሎቶችን የአገልግሎት አሰጣጣቸዉን ለማሳለጥ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። በመሆኑም በጽ/ቤቱ የተከናወኑ ተግባራት በምን አግባብ እንደተከናወኑ የልደታ ክ/ከተማ ግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ ዳዊት ጥበቡ ጋር ቆይታ አድርገናል።



## አቶ ዳዊት ጥበቡ
## የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ከማድረግ አንፃር ምን ይመስላል?

**አቶ ዳዊት፡-** አገልግሎት አሰጣጡ በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ከማድረግ አንጻር የአገልግሎት አሰጣጡን ፈጣንና ቀልጣፋ ከማድረግና የህብረተሰቡን የአገልግሎት ፍላጎት ከማርካት አንጻር በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ የኦን-ላየን አገልግሎት እና የQR Code certification አገልግሎት በመስጠት ላይ እንገኛለን፤ ከዚህ በመነሳት የኦን-ላየን አገልግሎት ከምንሰጣቸዉ ዉስጥ ዋና ዋናዎቹ የአዲስ ግንባታ ፈቃድ ፤ የማሻሻያ ፈቃድ መስጠት ሲሆኑ የተገልጋዩን ምልልስ ከመቀነስ አንጻር አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት በ **QR Code** በመጠቀም አገልግሎት እየሰጠን እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጡን የተሻለ ለማድረግ የተገልጋይ አስተያየት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላለው በ **QR Code** በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ አስተያየት መስጠት እንዲችል ተመቻችተዋል፡፡

ቴክኖሎጂን በመጠቀማችን በርካታ የሆነ ለውጥ ማምጣት የተቻለ ሲሆን ይህም የE-Service አገልግሎት በማይቋራረጥ መልኩ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ከኢኖቭሽን ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት ችግር ሲገጥም መፍታት ተሞክሯል ፡፡ እንዲሁም የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን መ/ቤቱ ባሉት የ IT department በኩል ክትትል ና ቁጥጥር በመደረጉ ሲስተም ሲቋረጥ Service በማየት በተከፈተው ቴሌግራም ፔጅ በማስታወስ እና እንዲስተካከል በማድረግ ከፍተኛ ችግር ፈቺ ለመሆን ተሞክሯል ፡፡

በቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠታችን ያስገኘው ፋይዳ ፡-የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታ የባለጉዳይ ምልልስን ለመቀነስ ተሞክሯል ፤የተሰጠዉ ግንባታ ፍቃድ ሳይት ላይ ከጽ/ቤቱ መዉጣቱን በቀላሉ በ QR Code ማረጋጋጥ መቻሉንና ህገወጥ ፍቃድ ከሆነ መለየት መቻሉ ህገወጥነትን ለመከላከል ተችሏል፤ የግንባታ ክትትል እና ቁጥጥር ሂደታችንን ዘመናዊ እና ተጠያቂነት (ባለቤት) ለመስጠት ተሞክሯል ፤አገልግሎት በተቀመጠላቸዉ ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት መስጠት ማስቻሉ፤የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ቴክኖሎጂ መደገፍ አገልግሎት ጠያቂው በቀላሉ የግል ማህደር ወጥቶለት አገልግሎት ለማግኘት ተችሏል፤የመረጃ አያያዝ ስርአታችንን በቴክኖሎጂ መተግበር መቻሉን ሁሉም ፋይሎች በሀርድ ኮፒ እና በሶፍት ኮፒ ማደራጀት ተችሏል፤የውጪ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ በቴክኖሎጂ መጠቀም መቻሉ ማስታወቂያ የሚሰቀልበት ቦታ X-Y Coordinate በማስገባት ቦታው ለተፈለገለት አላማ መዋሉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ከማስታወቂያ ፈቃድና እድሳት ጋር በተያያዘ አገልግሎት አሰጣጡ ምን ይመስላል?

**አቶ ዳዊት፡-** የማስታወቂያ ፍቃድና እድሳት አገልግሎት አሰጣጥ ቤት ለቤት በመሄድ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እየተሰራ ሲሆን ተጠቃሚዉን በመቀስቀስ ከተማው ያወጣውን ስታንዳርድ እንዲጠብቅ ከተማችን እንዲሁም ክፍለ ከተማችን ከህገ ወጥ ማስታወቂያና ደረጃውን ያልጠበቀ የውጪ ማስታወቂያ በማስወገድ ንፅሁ ሳቢ እና ተወዳዳሪ ከተማ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ይህም ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የማስታወቂየ ፈቃድ አገልግሎት ጠያቂ ሲመጣ አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ ሆኖ እንድሰጥ ሁኔታዎች እንድመቻቹ የተደረገ ሲሆን ይህም የሚሰሩትን ማስታወቂያ ስታንዳር በወረቀት በከለር ፕሪንት በማምጣት እና ሳይት ላይ በመውረድ በማረጋገጥ አገልግሎቱን ማግኘት ይቻላል፤ የማስታወቂያ ፍቃድ ለማግኘት ማሟላት ከሚገባቸው የንግድ ፍቀድ፤ንግድ ምዝገባ፤ቲን ናበር፤ቫት ሰርተፍኬት፣ ካርታ ኮፒ፣ .መልዕክትና ይዘቱን የሚያመለክት ዲዛይን ኮፒ፣ የቤት ኪራይ ውል ኮፒ፣ ብቃት ማረጋገጫ፣ የሚያሰሩት ማስታወቂያ ስታንዳርዱን የጠበቀ ዲጂታል ወይም ላይት በክስ ብቻ መሆን እንዳለበት የማሳወቅ ስራ ይሰራል፣ በዚዉ መሰረት አገልግሎት በአጭር ጊዜ ዉስጥ እንድያገኙ ይደረጋል፡፡

ማንኛውም ማስታወቂያ መስቀል የፈለገ ተገልጋይ በቅድሚያ ማስታወቂያውን ከማሰራቱ በፊት ወደ ልደታ ክ/ከ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ፅ/ቤት የማስታወቂያውን ፍቃድ አሰጣጥና ክትትል ቡድን ቀርበው ስታንዳርዱን አውቀውና በቂ መረጃ አግኝተው እንዲያሰሩ ስለሚደረግ ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረጉ አይችሉም፡፡ ያለፍቃድ ማስታወቂያ መስቀል ቅጣት እንዳለዉ ህብረተሰቡ አዉቆ አገልግሎቱን እንድያገኝ በዚዉ አጋጣሚ ለማሳወቅ እንወዳለን፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ህገ-ወጥ ግንባታ ከመከላከል አንፃር ቅንጅታዊ አሰራሩ ምን ይመስላል ?

**አቶ ዳዊት፡-** የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ፅ/ቤት በዋናነት ተቀናጅቶ አብሮ ከሚሰራባቸዉ ፅ/ቤቶች በቁጥር 6 ሲሆኑ የህገ ወጥ ግንባታን ለመከላከል በዋናነት ስራዎችን በቅንጅት መፈጸም አስፈላጊ በመሆኑ ግንባታ ፈቃድ ጽ/ቤት ህገ-ወጥ ግንባታን ለመከላከል ከደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀት እና ስራዎችን በየጊዜዉ በመገምገም ህገወጥነትን የመከላከል ስራ እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን

ማንኛዉም የግንባታ ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት በግልባጭ ለደንብ ማስከበር ጽ/ቤት እንዲደርስ ይደረጋል። ከህገ ወጥ ግንባታዎች በተጨማሪ ስታንዳርድ ያልጠበቁ ህገ ወጥ የውጪ ማስታወቂያዎችን ፈቃድ ከመቆጣጠርና ከመከላከል አንፃር ከደንብ ጽ/ቤት ጋር በመሆን እየተሰራ ይገኛል፤ በዚህም ከፍተኛ ዉጤት ተገኝቶዋል፣ በተጨማሪም ከሌሎች ጽ/ቤቶች ጋርም ቀላል የማይባል ስራ እየሰራን እንገኛለን። ከዚህም ውስጥ ከፕላን ልማት ጽ/ቤት ጋር የተለያዩ ጥናቶች (የመንገድ) በመቀበል ከተማው እንዲሁም ክፍለ ከተማው የሚመጥን ግንባታ እናከናውናለን፣ ከመሬት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት አንፃር ዲጂታል ያለ፤ሆኑ ካርታዎችን ግልጽ ያልሆኑ **X-Y co-ordinate** ጠይቀን በመቀበላችን የአገልግሎት አሰጣጡን ፈጣን ቀልጣፋ ለማድረግ ተችሏል፣ ከመሬት ምዝገባ ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት በመስራታችን ዲጂታል የሆኑ ካርታዎችን ግልጽ ያልሆኑ **X-Y coordinate** ሲያጋጥም ምላሽ በቶሎ በማግኘታችን የአገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ ተችሏል፣ ከቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት በመስራታችን የቀበሌ ቤቶችና የግል ይዞታዎች በመለየት የግንባታ ፈቃድን በመስጠታችን የመንግስት እና የህዝብ ሀብት ከህገወጦች መከላከል ተችሏል፣ ከፍትህ ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት በመስራት ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የመንግስት እና የህዝብ ሀብት ለመዝረፍ የሚሞክሩ ግለሰቦችና ድርጅቶችን ተከራክሮ ወደ ህጋዊነት ማስገባት ተችሏል።

በመሆኑም ተቋማት ተቀናጅተዉ መስራት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ዉጤታማ እየሆነ የመጣ ሲሆን በዚህ ጋር ተያይዞ ህገ ወጥ ግንባታ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የመቆጣጠር ስራ መሰራት ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ
**አቶ ዳዊት ፡-** የሚሰጡ አገልግሎቶች ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ የተጀመሩ የሪፎርም ስራዎች ተጠናክረዉ በመቀጠል ላይ ያሉ ሲሆን ዉጤቱም የሚያበረታታ ከመሆኑም በላይ የባለጉዳዩን እርካታ ለማምጣትና በመልካም አስተዳደር ዙሪያ የጽ/ቤቱን አገልግሎት ግልፅ በማድረግ ተጠያቂነት ባለው መልኩ እየተሰጠ ያለው አገልግሎት በመልካምነት የሚወሰድ ነው። በተለይም የለውጥ መሳሪያዎችን በመጠቀም ስታንዳርዱ የጠበቀ አገልግሎት ለመስጠት እየተደረገ ያለው ጥረት በቀጣይነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል። ስለሆነም ለአገልግሎት አሰጣጡ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ አሰራሮችን በማጥፋት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚደረገው ጥረት በቀጣይ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን በማወቅ ህብረተሰቡም ተሳታፊ በመሆን የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ እንጠይቃለን።

## ፅዳትን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ

ልደታ ክፍለ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ጽ/ቤት በ2018 ዓ.ም የተቋሙን ስራ ለማሳካት ብዙ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል ። ይህ ዘርፍ በጽ/ቤት ደረጃ በ**1** አስተባባሪ በ**3** ቡድን የተደራጀ ሲሆን የአሰራር ባህሉና ሁኔታው እጅግ ተመጋጋቢ የጋራ ስራና ውጤት የሚጠይቅ ዘርፍ ነው በዚህ ዘርፍ በዋናነት የክፍለ ከተማውን ማህበረሰብ ተቋማቶች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ያለውን ችግር በዘላቂነት በመፍታት የክፍለ ከተማውን ጽዳት ፣ንጽህና በትኩረት በማስጠበቅ ዘላቂ ጽዱ ክፍለ ከተማ እና ከተማ መፍጠርና የመልሶ መጠቀምና ዑደት ተግባራትን በስፋት መስራት ዋነኛ ተግባሩ ነው ። አካባቢውን ለነዋሪዎች ምቹና ፅዱ እንዲሁም ሞዴል በማድረግ ቆሻሻን ከምንጩ ለመቀነስና የደረቅ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀምና በማስወገድ ጤናው የተጠበቀ ህብረተሰብ ለመፍጠር ከባለድርሻ አካላት ጋር የተከናወኑ ስራዎች በምን አግባብ እየተከናወኑ እንደሆነ የዝግጅት ክፍላችን ከፅዳት አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊ ከአቶ አክረም መሀመድሲራጅ ጋር ቆይታ አድርገናል።



### አቶ አክረም መሀመድሲራጅ
### የፅዳት አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** ማህበረሰቡ ፅዳትን ባህሉ እንዲያደርግ ምን ተሰርቷል?
**አቶ አክረም፡-** አጠቃላይ ነዋሪውን ማህበረሰብ በበር ለበር በግንዛቤ ባለሙያዎች ተደራሽ በማድረግ ስለ ደረቅ ቆሻሻ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ማድረግ ተችሏል ::የተለያዩ በዓላትን ምክንያት በማድረግ በየወረዳው ጠዋትና ማታ በሳውንድ ሲስተም በማንታርቦ የቅስቀሳ የግንዛቤ የማነቃቃት ስራዎች ተሰርተዋል :: ህበረተሰብን ማግኘት በሚቻልባቸው በተለያዩ መድረኮች እና በሀይማኖት ተቋማቶች ስለ ፅዳት ዘመቻ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር በየሳምንቱ ቅዳሜ በበር ለበር ፅዳትና በብሎኮች ፅዳት በቋሚነት ተሳታፊ የማድረግ ስራ ተሰርቷል :: ቅዳሜ ቅዳሜ በየሳምንቱ በራስ ተነሳሽነት ለአካባቢው ፅዳት ባለቤት ለማድረግ በየብሎኩ በቡና ጠጡ ከነዋሪዎች ጋር በመወያየት በክፍለ ከተማችን በፅዳት ዙሪያ ባህሉ የሆነ ህብረተሰብ መፍጠር ተችሏል ::በክፍለ ከተማ ደረጃ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ግንዛቤ ካገኙት 40,500 ነዋሪ እማወራና አባወራዎች መካከል ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ ለመቀነስ የቤት ለቤት ቀልዝ/ ኮምፖስት/ 489 ማዘጋጀት ተችሏል ። ቅዳሜ ቅዳሜ በየሳምንቱ በራስ ተነሳሽነት ለአካባቢው ፅዳት ባለቤት በማድረግ በየብሎኩ በቡና ጠጡ ከነዋሪዎች ጋር በመወያየት በክፍለ ከተማችን በፅዳት ዙሪያ ባህሉ የሆነ ህብረተሰብ መፍጠር ተችሏል ::

**ልደታ ፋና ፡-** ሞዴል መንደር/ብሎክ/ ከመፍጠር አንፃር የተሰሩ ስራዎችና የመጣ ውጤት ቢገለፅ ?

**አቶ አክረም ፡-** በ2018 ዓ.ም በብሎክ፣ በአስተዳደር፣ በትምህርትና በሀይማኖት ተቋማት **71** ሞዴል መፍጠር ተችሏል። **1871** ሞዴል ቤተሰብ መፍጠር ተችሏል ። በሞዴል እቅድና መስፈርቱ ዙሪያ ከብሎኮቹ ነዋሪዎች፣ከብሎክ ፎካል አምባሳደሮች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይትና ስልጠና የመስጠት ስራ ተሰርቷል ። በበላይነት የሚመሩ ኮሚቴዎችን የማዋቀር ስራ ተሰርቷል ። ሞዴል በመፍጠራችን ያመጣነው ውጤት በተመለከተ በእቅድ የተያዙትን ሁሉንም ማሳካት ችለናል፣ በከተማው መመዘኛ መስፈርቱ መሰረት ብቁ ማድረግ ተችሏል። ለነዋሪ ማህበረሰቡ የማስመረቅ ስራም ተሰርቷል። ሞዴል ብሎኮቹን ፣ተቋማቶችንና ት/ት ቤቶችን በራሳቸው አደረጃጀቶች እንዲመሩ ተደርጓል።ህብረተሰቡ በየብሎኩ በባለቤትነት ፅዳት ዘመቻ ላይ እንዲሳተፍ ተደርጓል። በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ውጤታማ ስራ መሰራቱ እንዲሁም በቤት ለቤት ቀልዝ በማምረትና ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ የመቀነስ ስራ ተሰርቷል። በመሆኑም ወረዳ 6 ፅዳት አስተዳደር ጽ/ቤት ሞዴል የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

**ልደታ ፋና ፡-** የክ/ከተማውን ንፅህናና ውበት በመጠበቅ ረገድ ምን ውጤት ተገኝቷል?

**አቶ አክረም ፡-** ከአመት አመት የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ለውጥ ማምጣት ተችሏል። ነዋሪዎች ደረቅ ቆሻሻ በአይነት ከመለየት አንፃር እጅግ የተሻለ ስራ ተሰርቷል። የቤት ለቤት ቀልዝ ማምረት በከፍተኛ ሁኔታ የነዋሪው ፍላጎት መጨመሩ የደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ ለመቀነስ ትልቅ መፍትሔ እንዲሆን አድርጓል።በትምህርት ቤቶች፣ በፌደራል ተቋማትና በከተማ ተቋማቶች በየሳምንቱ የሚደረጉት ፅዳት ዘመቻዎች ለውጥ ማምጣታቸውና በትኩረት በተቋማቶቹ እንዲመራ ተደርጓል።

በየሳምንቱ ቅዳሜ ቅዳሜ በአንድ ማዕከል ለሚደረገው ፅዳት ዘመቻ የተሳታፊዎች ቁጥር መጨመሩ እና እየተለመደ መሄዱ፣ የበር ለበር ፅዳት በብዛት በየብሎኮች ነዋሪ ማህበረሰቡ ያለማንም ቀስቃሽ ራሱ በሀላፊነት ማፅዳት መቻሉና የክፍለ ከተማው ወጣቶች በፍቃደኝነት ተሳታፊ መሆናቸው የተገኘ ውጤት ነው።



**ሞዴል መንደር**

**ልደታ ፋና ፡-** ከፅዳት ባለፈ ቆሻሻ አወጋገድና መልሶ መጠቀም ሂደት ምን እየተሰራ ነው ?

**አቶ አክረም፡-** በመልሶ መጠቀምና ዉደት ማህበራቶች እና በደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዝ ማህበራት ከ92 ዜጎች በላይ የስራ ዕድል ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። በክፍለ ከተማ ደረጃ ያሉትን ከ**1ኛ-3ኛ** ደረጃ መንገዶች **180.36** ኪ.ሜ በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ በየቀኑ ከለሊቱ **10፡00** እስከ ምሽቱ **4፡00** በመንግድ ጥርጊያ በ**4** ሽፍትና በመንገድ ጽዳት ማሽነሪ ተሸከርካሪ የማስፀዳት ስራው **100%** ስኬታማ ስራ ተሰርቷል። በህብረት ሽርክና ማህበራቶች የመልሶ መጠቀምና ዑደት ዘርፍ የፕላስቲክና ጠርሙስ ፌስታል በተገቢው መንገድ ለመልሶ መጠቀምና ዑደት አገልግሎት ለማዋል **3500** ቶን ታቅዶ 4711ቶን ለመልሶ መጠቀምና ዑደት ዓላማ ማዋል ተችሏል። በመልሶ መጠቀምና ዑደት ዘርፍ ተደራጅተው ለሚሰሩ ማህበራቶች አስተማማኝ የገበያ ትስስር ለመፍጠርና **46,542,404** ብር ገቢ እንዲያገኙ ታቅዶ **65,873,514.23** ብር ገቢ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል ። በተቀመጠው የቆሻሻ ማጓጓዝ ስታንዳርድ መሰረት **10,765.96** ቶን ደረቅ ቆሻሻ ወደ ላንድ ፊል የማጓጓዝ ስራ ተሰርቷል፡፡ ይህም በየዓመቱ ደረቅ ቆሻሻ የማመንጨት አቅም መቀነሱን እና የመልሶ መጠቀምና ዑደት ተግባር ስኬታማ መሆኑን ያመላክታል፡፡ከዚህ በመነሳት ማህበረሰቡ ተገቢውን የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ ተችሏል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የመንገዶች ንጽህናን የማስጠበቅ ፣ ህገ-ወጥ ቆሻሻዎችን የማስወገድ ፣ ማህበራቶችን በገቢ ምንጭ ለከፍተኛ ደረጃ እንዲበቁ የማድረግ ስራ በስፋት ተሰርቷል።



**የመልሶ መጠቀምና ዑደት ኢግዚቢሽን**

**ልደታ ፋና ፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**አቶ አክረም፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ሪፎርም ለውጤታማ አገልግሎት

በልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር መሬት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት በቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን በመስጠት ውጤማ ስራዎችን እየሰራ የሚገኝ ተቋም ነው።የከተማዋን ገቢ በማሳደግና ለልማት ተነሺዎች የካሳ ክፍያና ምትክ ቦታ በመስጠት ከተማዋን የሚመጥን ስራ ተሰርቷል። በመሆኑም ዘመናዊ የመሬት አያያዝን በማዘመን ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ከመስጠት አንፃር የተከናወኑ ተግባራት በምን አግባብ እንደተከናወኑ የዝግጅት ክፍላችን ከመሬት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ ካሳሁን ጥላሁን ጋር ቆይታ አድርጓል አብራችሁን ቆዩ።



## አቶ ካሳሁን ጥላሁን
## የመሬት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ሀላፊ

**ልደታ ፋና፡-** የከተማዋን ገቢ ለማሳደግ ከሊዝና ከውዝፍ ሊዝ ክፍያ ገቢ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ እየተሰራ ያለው ስራ ምን እንደሚመስል ቢገልፁልን?

**አቶ ካሳሁን ጥላሁን ፡-** የልደታ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስ/ቅ/ጽ/ቤት የከተማው የገቢ አቅም ለማሳደግ ከዓመታዊ የሊዝ ክፍያ፤ውዝፍ የሊዝ ክፍያ እና የአገልግሎት ለውጥ በአጠቃላይ 301,920,875.47 ብር በመሰብሰብ ውጤታማ ስራ ሰርተናል።

**ልደታ ፋና፡-** ለልማት ተነሺዎች የካሳ ክፍያና የምትክ ቦታ አሰጣጥ አፈፃፀምና አተገባበር የተሰሩ ስራዎች ቢያብራሩልን?

**አቶ ካሳሁን ጥላሁን ፡-** በከተማዋ ፍላጎት መሠረት የመልሶ ማልማትና የወሰን ማስከበር ሥራዎችን ለማሻሻል በ1ኛ እና 2ኛ ዙር ኮሪደር ልማት ሥራዎች ካሳ የተከፈላቸው የልማት ተነሺዎች ብዛት 110 ሲሆን ብር 741,279,435.13 የካሳ ክፍያ መፈፀም ተችሏል።እንዲሁም በያዝነው በጀት ዓመትም ለልማት ተነሺዎች 143,484,835.03.23 ብር የካሳ ክፍያ በወቅቱ መፈፀም ችለናል። በክ/ከተማችን በተለያዩ ልማት ተነሺዎች ተዘጋጅቶ 37 ምትክ ቦታ እንዲሰጥ ተደርጓል።102 ለልማት ተነሺዎች ምትክ ቤት እንዲሰጣቸው ለከተማ መሬት አስተዳደር ቢሮ የመጠየቅ ስራ ተሰርቷል።

**ልደታ ፋና፡-** ዘመናዊ መሬት ዝግጅትና በመሬት ባንክ የተመዘገቡ ቦታዎች ለአልሚዎች የማስተላለፍ ሂደት በተመለከተ የተሰሩ ስራዎች ቢያብራሩልን?

**አቶ ካሳሁን ጥላሁን ፡-** በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዘመናዊ የመሬት ዝግጅት፣ ባንክና ጥበቃ አሰራርን ለማሳደግ፣ ተመዝግበው ባንክ የገቡ ለልማት የተዘጋጁ ቦታዎች በሄ/ር 6.085 ሄ/ር መሬት ተዘጋጅቷል። እነዚህ ቦታዎች ባንክ ተመዝግበው እንዲጠበቁ ለደንብ ማስከበር የተላለፉ ናቸው። በምደባ፤ በጨረታ፤ በካቢኔ ውሳኔ እና በፕሮሰስ ካውንስል ውሳኔ አግኝተው ወደ ክፍለ ከተማችን የሚመጡ አልሚዎች የተላለፉ ቦታዎች 5 ፕሎት ሲሆኑ ለሃገራዊ ፋይዳ ፕሮጀክት ሊሆኑ የሚችል ቦታዎች ከመለየት አንጻር 8.86 ሄ/ር መሬት የመለየትና የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል። ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በከተማ አስተዳደሩ ተወስኖ የተላኩ 78 ውሳኔዎች ያሉ ሲሆን እነዚህ ውሳኔዎች የተሟላ መረጃ መያዝ ተችሏል። ከተወሰኑ የካቢኔ ውሳኔዎች 56 ርክክብ የማድረግ ስራ ተሰርቷል።አፈጻጸሙም ያልተረከቡ/ቀሪ 22 ሲሆኑ፤ያልተረከቡበት ምክንያት 3 ተለዋጭ ሌላ ክ/ከተማ የወሰዱ፤ 9 በፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የተያዙ፤3 የፍርድ ቤት ክርክር ያለባቸው፤1 በፖሊስ የተያዘ ተለዋጭ ቦታ የሚፈልጉ፤6 በሂደት ላይ ያሉ በቀጣይ ርክክብ የሚደረግባቸው ናቸው።

**ልደታ ፋና ፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**አቶ ካሳሁን ጥላሁን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## የአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጤታማነት

መንግስት በሀገራችን ልዩ የትኩረት ዘርፎች ግብርና፤ ኢንዱስትሪ፤ ማዕድን፤ ቱሪዝምና ቴክኖሎጂ እንደመሆናቸው መጠን በኢንዱስተሪው የቀጣዮቹ 5ዓመታት የኢንዱስትሪ ልማት ትኩረት ከውጭ የሚገቡ የካቢታል ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካት ዘርፉን ማበረታታትና ማዘመን፤የትራንስፖርት እቃዎችን፤ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች፤ማሽን፤የሜዴካል እቃዎችን ፤ፕላስቲክ፤ብርታ ብርቶችን እና ሌሎች ወሳኝ ሸቀጦችን ማምረት፤በሀገራችን የተገነቡትን ኢንዲስተሪዎችን ማሻሻል፤ጥራትን ማርጋገጥና ተወዳዳሪነትን ማሳደግና ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰው ሀይልና የፖሊሲ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ስለሆና በከተማችን በእነዚህ ቁልፍ ግቦች ላይ ያተኮር ስራዎች እየተሰሩ ቆይተዋል በዚህ ረገድም ክፍለ ከተማችን ከሌሎች ክፍለ ከተማዎች በመሆን የበኩሉን ድርሻ እየተዋጣ ይገኛል።



### አቶ አበበ ዱላ
### የኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ሃላፊ

የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ እንደጀመረ ይታወቃል። በዚህም የአምራች ኢንዱስትሪ ልማቱን በማፋጠን ለአገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ለስራ ዕድል ፈጠራና ለኤክስፖርት ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በመረዳት የዘርፉን ልማት ለማፋጠን ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ከተማ የሚታየውን ድህነትና ስራ አጥነት ለመቀነስ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የተደራጁ አምራች ኢንዱስትሪን በመደገፍ የኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ሽግግር ማረጋገጥ፣ ገቢ ምርቶችን በሀገር ምርት በመተካትና ኤክስፖርት የማድርግ አቅም በማሳደግ ሀገራችን ኢትዮጵያ የበለፀገችና ለዜጎች የምትመች ሀገር እንድትሆን የተጠናከረ ስራ እየተሰራ ይገኛል።

በ2018 በጀት ዓመት እቅድ በማዘጋጀት ወደ ተግባር የገባን ሲሆን በክ/ከተማችን በአምራች ዘርፍ የተመቻቸ የመሰሪያ ሊዝ አቅርቦትን በኢንዱስተሪ **8** ፤ የመሳሪያ ሊዝ ብዛት **59** እንዲሁም በብር **22,558,550** ብር ለማሳካት ችለናል። በኢንዱስተሪ አክስቴንሽን የተጠናከር አምራች ኢንዱስትሪ 30 ፤ነባር አምራች በማጠናከር የተፈጠር የስራ እድል 233 ፤ የሰለጠነ የሰው ኃይል **80፤ /BDS/** ድጋፍ ያገኙ አምራቾች 19፤ ተሸጋገረ አምራች ኢንዱስትሪ **3** ፤ስትራቴጂክ ገቢ ምርት በአዲስ ኢንዱስትሪዎች **5**፤ በነባር ኢንዱስትሪዎች ኢንዱስትሪ **89** ማሳካት ተችሏል።

ወደ ውጭ የላኩ አምርቾችን በአዲስ ኢንዱስትሪዎች 1፣ በነባር ኢንዱስትሪዎች **15** ማከናወን ተችሏል። የአረንጓዴ ኢንዱስትሪ ልማትና ኢነርጂ አጠቃቀምን በተመለከተ አከባቢ ጥበቃና ኢነርጂ አጠቃቀም ዙሪያ ግንዛቤ የተፈጠረላቸው **23** የተከነወነ ሲሆን ደረጃውን የጠበቀ የፍሳሽ እቅድ **13** ፣ዘመናዊና ኃይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂ የተጠቀሙ አምራች ኢንዱስትሪ **40** ማድርስ ተችሏል ። የፋስልቴሽን እና ካይዘን ትግበራ በጥናት የተለየ የገበያ ትስስር ፍላጎት በአምራች ኢንዱስትሪ 30 ማከናወን ተችሏል። የገበያ ትስስር የተደረገላቸው አምራች ኢንዱስትሪ **32** ለማከናወን የጠቻለ ሲሆን በገቢያ ትስስር **46,910,671** ብር ለመፈፀም ተችሏል ፡፡ ለ**36** አምራች ኢንዲስትሪ ባዛር በማሳተፍ **1,070,474** ብር ለማከናወን ተችሏል ። ኤክስፖርት ያደረጉ አምራች ኢንዱስትሪ **15** ፣ የኤክስፖርት ምርት መጠን በቶን **307** ፤ ተኪ ምርት ያመረቱ ኢንዱስትሪ **89** ፤የተተካ ምርት በቶን **98,759**፤ የዳነ ምርት በዶላር **25,746,665** ፤ የግብዓት ትስስር የተደረገ የግብዓት መጠን በቶን **339** ፤የግብዓት ትስስር የተደረገላቸው አምራች ኢ/ሪ **16** ፤ ብድር ማመቻቸት አምራች ኢንዱስትሪ ብዛት **7** ፤የተሰጠ ብድር መጠን **101,090,000** ብር፤ ብድር የመለሱ አምራች ኢንዱስትሪ ብዛት 23 ፤ የተመለሰ መደበኛ ብድር መጠን **23,538,686** ብር ፤ የቆጠቡ አምራች ኢንዱስትሪ ብዛት 43 ፤ የተቆጠበ ብር መጠን **21,219,750** ብር ፤ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ድጋፍ ያገኙ አምራች ኢንዱስትሪ ብዛት **18**፤ የደረጃ እድገት እድሳት የተሰጠቻዉ አምራች ኢንዱስትሪ ብዛት **38**፤ የካይዘን ፍልስፍና ስልጠና ያገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች ብዛት **13** ሲሆን እንደ ክፍለ ከተማችን የተሻለ ስራ ስለሆነ በቀጣይም ማጠናከር ይገባል።

በመጨረሻም አምራች ኢንዱስትሪ ያለባቸውን የመሰረት ልማት ፤የገበያ ትስስርና የግብአት አቅርቦት ችግር ለመፍታት የሁሉም ትብብር ስለሚጠይቅ ሁላችንም ድጋፍና ክትትል አይለያቸው የሚል መልዕክት አስተላልፋለሁኝ።

## ህብረት ስራ ማህበራት ለውጤታማነት

የህብረት ስራ ማህበራት ተጠናክሮ መቀጠል የማህበረሰባችንን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች ከተቻለ እንዲቀረፉ ካልተቻለም እንዲቀንሱ ለማስቻል ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል። የኑሮ ውድነትን ከማረጋጋት አኳያ እንዲሁም ዘለቄታዊ መፍትሔ ለማምጣት በሚደረገው ሀገራዊ ጥረት ውስጥ የህብረት ስራ ማህበራት መኖሩ እንዴት መፍትሄ ሊሆን ይችላል ከተባለም በማህበራቱ የሚገቡ

የፍጆታ እቃዎች ጥራት ኖሮዋቸዉ የነዋሪዉን አቅም ያማከለ የዋጋ ተመን በማዉጣት ግብይት እንዲፈጽሙ በማድረግ ነዉ። የከተማ አስተዳደሩም ይህንን ተግባር አጠናክሮ በማስቀጠሉ ተጨባጭ ዉጤት ማስመዝገብ ችሏል።

የልደታ ክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽ/ቤት በከተማ ደረጃ የተያዘዉን የኑሮ ዉድነትና የገበያ ማረጋጋት ዉጤታማ እንዲሆን ለማስቻል በትኩረት እየሰራ ይገኛል። በተለይም ሸማች ማህበራት በ10ሩም ወረዳ በተለያዩ ቀጠናዎች በማመቻቸትና የፍጆታ እቃዎችን በማሟላት የክፍለ ከተማዉ ነዋሪ በአቅራቢያዉ በመሄድ ግብይት እንዲፈጸም ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። በዛሬዉ የመጽሄት አምዳችንም ከእዚሁ ጉዳይ ሳንወጣ ከጊዜ ወደ ጊዜ በማህበራቱ የሚታዩ ለዉጦችና እየተመዘገቡ ያሉ ስኬቶችን በተለይም አሁን ላይ በተደረገዉ የስራ መሻሻልና በሪፎርም ስርዓቱ መሰረት የተሰሩ ስራዎችን ለመዳሰስ ከልደታ ክ/ከተማ ህብረት ስራ ጽ/ቤት ኃላፊ ከሆኑት ከአቶ ባየ ባይሌ ጋር ቆይታ አድርገናል መልካም ቆይታ።



## አቶ ባየ ባይሌ
## የህብረት ስራ ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** በሪፎርም ስርዓቱ መሰረት አጠቃላይ የተሰሩ ስራዎች ቢገልጹልን?

**አቶ ባየ ባይሌ ፡-** በሪፎርሙ የተሰሩ ስራዎችን በሚመለከት ወደ ሪፎርሙ በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶች የህዝብን እርካታ ከማረጋገጥ አንጻር በቂ አለመሆኑ ተገምግሞ የተገባ ሲሆን በሪፎርሙ መሰረት በተቋሙ ያሉ ችግሮችን በመለየት እንዲሁም ለተቋሙ የሚያስፈልግ የሰዉ ኃይል፣የአገልግሎት ስታንዳርድ እና ሌሎችንም ጉዳዮች በጥናት በመለየት ወደ ተግባር ተገብቷል። በመሆኑም በአሁኑ ሰዓት በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ ያሉን የሰዉ ኃይልና የሸማች ማህበራት በሪፎርሙ እንዲያልፍ ተደርጎ ድልድል ተሰርቷል፡፡ ይህም ለስራችን ጥራት መኖርና በየጊዜዉ በአሰራራችን ወይም በአገልግሎት አሰጣጣችን ላይ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎችን እንዲቀንሱ ማድረግ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** ለህብረት ስራ ማህበራት የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ውጤታማነት እንዴት ይገለፃል ቢያብራሩልን?

**አቶ ባየ ባይሌ ፡-** ለህብረት ስራ ማህበራ የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ከውጤታማነት አንፃር ማህበራቱ በዕቅዳቸው መሰረት ስራቸውን እንዲሰሩ ፣ የነበራቸውን አፈፃፀም አይተው ለቀጣይ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡና የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ካሉ ድጋፍ ለሚያደርግላቸው አካል በማቅረብ ለስራው ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል። በመሆኑም የተደረገው ክትትልና ድጋፍ ውጤታማ በመሆኑ በማህበራት ላይ የተሰራው ሪፎርም የተሻሉ ውጤቶች ማስመዝገብ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር ምርትና አገልግሎታቸውን ከማስተዋወቅና በእሁድ ገበያ የተሸለ ምርት እንዲያቀርቡ ከማድረግ አንፃር የተሰራ ስራ ቢገልፁልን?

**አቶ ባየ ባይሌ ፡-** 11 መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት በማሳተፍ 11 የእሁድ ገበያ ቦታዎች ላይ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችእንዲያቀርቡ በማድረግ ምርትና አገልግሎታቸውን በባነር፣በቴሌግራም፣በብሮሸር እና በተለያዩ የኮሙኒኬሽን አግባቦች የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል።

**ልደታ ፋና፡-** የኢንስፔክሽን አገልግሎት የተሰራ ስራና የመጣው ውጤት ቢገለፅ ?

**አቶ ባየ ባይሌ ፡-** ህብረት ስራ ማህበራት በአዋጁና በመመሪያ መሰረት መስራታቸውን መደበኛ የሆነ የኢንስፔክሽን ስራ ተሰርቷል፡፡ በተሰራው ኢንስፔክሽን የአሰራር ክፍተት ያለባቸውን ማህበራት በመመሪያ መሰረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት የማስተካከል ስራ እንዲሰሩና ህጉን አክብረው እንዲሰሩ በመደረጉ ማህበራቱ ውጤታማ ሁነዋል።

**ልደታ ፋና፡-** በኦዲት አገልግሎት ምን ምን ስራዎች ተሰሩ ቢያብራሩልን?

**አቶ ባየ ባይሌ ፡-**በኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊ የህብረት ስራ ማህበራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 በክፍል 7 አንቀጽ 50 መሰረት በአመት አንድ ጊዜ ሂሳባቸውን ስልጣኝ በተሰጠው አካል ማስመርመር እንዳለባቸው በተደነገገው መሰረት ማበራ ሂሳባቸውን አዘጋጅተው ለኦዲት ብቁ ኢያደርጉ የሂሳብ ሪፓርት በማዘጋጀት የኦዲት ይደረግልን ጥያቄ ኢያቀርቡልን በአዋጁ መሰረት ገብተን ሂሳቡን በመመርመር ገለልተኛ እና ታማኝ የሆነ የሒሳብ ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል። በዚህ መሰረት አገልግሎት የምንሰጣቸው ሸማች ኃ/የተ/ህ/ስ/ማህበር፣ቁ/ብድር ኃ/የተ/ህ/ስ/ማህበር፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ኃ/የተ/ህ/ስ/ማህበር እና ሌሎች ኃ/የጠ/ህ/ስ/ ማህበራ ናቸው። በመሆኑም በአዋጁ መሰረት ለእነዚህ ህብረት ስራ ማበራት የኦዲት አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል።

**ልደታ ፋና፡-** ሸማች ማህበራት መኖራቸዉ ለኑሮ ዉድነቱ ያላቸዉ ሚና ምንድንዉ?

**አቶባየባይሌ፡-**ሸማችማህበራትመኖራቸዉለማህበረሰቡትልቅሚና አላቸዉበይብለጥደግሞበዝቅተኛየኑሮደረጃላይለሚገኙነዋሪዎቻችን በአቅማቸዉ እንዲገበያዩ ያስችላል፣ በዋጋ፣በጥራት መዳደል፣

በቂ ምርት ገብቷል አልገባምና በሌሎች ጉዳዮች ላይ በሚመለከተዉ አካል ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ምቹ ናቸዉ፣በአጠቃላይ በቂና ጥራት ያላቸዉ ምርቶችና የፍጆታ እቃዎችን በሸማች ማህበራት እንዲገቡ በማድረግ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀዉስን ለማረጋጋት ይረዳሉ።

**ልደታ ፋና፡-**የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?
**አቶ ባየ ባይሌ ፡-** አሁን ላይ በተቋማችን ትኩረት ተሰጥቶባቸዉ ከሚሰሩ ስራዎች መካከል በሸማች ማህበራት ላይ ምርቶችን ማስገባት፣ለማህበረሰቡ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ማሰራጨትና በሌሎች ጉዳዮች ላይ በተገቢዉ ሁኔታ ለዉጥ እንዲመጣ በትጋት እየሰራን ሲሆን በተለይ በዩኒየንና በብድር አቅርቦት ተመቻችቶላቸዉ ማህበረሰቡን የሚደግፉ ብሎም የኑሮ ዉድነቱን የሚያረጋጉ እንዲሆኑ ማህበራቱን ሪፎርም በመስራት እና የሚገጥማቸዉን ችግር በጊዜዉ እንዲፈታ ባለድርሻ አካላት ጋር በሚገባ ሰፊ ስራ እየሰራን እንገኛለን። ይህን ተግባራችን አጠናክረን እንቀጥላለን። ህብረተሰቡም በማይገባ የዋጋ ጭማሪና ምርትን የሚደብቁ አካላት ካስተዋለ ጥቆማ እንዲሰጥ በእዚሁ አጋጣሚ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።

## የሌማት ትሩፋት ለዜጎች ተጠቃሚነት

መንግስት ለአርሶ አደርና ለከተማ ግብርና ትኩረት በመስጠቱ ተጠቃሚዎች ከቤተሰብ ፍጆታ ማምርት አልፎ ተርፎም ለገበያ ማዋል እንደሚቻል ክቡር ጠቅላይ ሚኒሰትራችን ዶ/ር አብይ አህመድ ከገለጹ በኃላ ከተማ አስተዳደሩ ትኩረት በመስጠቱ በከተማ ደረጃ ፤ በኮሚሽን እንደ ክ/ከተማ እና ወረዳ ጽ/ቤት ሆኖ አንደ አዲስ ተቋቁሟል።

በዚህም በከተማ ግብርና በከፍተኛ ደረጃ የአመለካከት እና የተግባር ለውጥ ማምጣት ተችሎል። በከተማችን ብሎም በክ/ከተማችን አንድም ክፍት ቦታ ሳይታረስ እንዳይቀር ብለን የጀመርነው ስራ በሌማት ቱሩፋት አስደማሚ ስራዎችን እየተሰሩ ይገኛል።

ባለፉት 6 ወራት በዱሮ አትክልትና በእንስሳት እርባታ ዘርፍ በቤተሰብ ፍጆታ ፤ በስራ ዕድል አዲስ ተጠቃሚዎች ወደ ስራ የገቡ ሲሆን በእንስሳት እርባታ ዘርፍ ማለትም በወተት ከብት እርባታ ፤ በንብ ማነብ ፤ በዶሮ እርባታ 28707 ነባር ተጠቃሚዎችን እንዲሁም በእጽዋት ልማት ዘርፍ 42815 ተጠቃሚዎችን በአጠቃላይ 71522 ነባር ተጠቃሚዎችን በከተማ ግብርና በንቃት በክፍለ ከተማችን እየተሳተፉ ሲሆን ከዚህም በፊት በክፍትነት የምናውቃቸው የመንግስት እና የግል ተቋማት ወንዝ ዳርቻዎችን ጨምሮ በተቀናጀ መልኩ ምርት ለገበያ እንዲወጣ እየተሰራ ይገኛል።



## አቶ በፍቃዱ ሀይሌ
## የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ጽ/ቤት ሃላፊ

ማህበረሰባችን ቀደም ሲል ያለው ግንዛቤ ከተማ ግብርና ሲባል በመሀል ከተማ ለራሳችን መቀመጫ የሌለን እንዴት የዱሮ አትክልት ትከሉ ዶሮ አርቡ ትሉናላችሁ በሚል በጣም ይቃወሙ ነበር ነገር ግን በተደጋጋሚ ቤት ለቤት በተሰራ የግንዛቤ ማስጨበጥ እና የመድረክ ስልጠና በአሁኑ ወቅት የነበረው አመለካከት ተቀይሮ ክፍት የሆነ ቦታ እየጠቆሙ ጨምር ቢሰራበት የሚል ጥያቄ እያቀረበ ይገኛሉ ።

በአሁኑ ሰዓት እንደ ክፍለ ከተማችን በሁሉም ወረዳዎች በዱሮ አትክልት፣ በእንስሳት ዘርፍ በወተት ላም እርባታ እና በእንቁላል ጣይ ዶሮ ሞዴል የሆኑ ብዙ ናቸው። ከራሳቸው አልፈው ለገበያ እያቀረቡ ነው። በተቋማት ደረጃ የመንግስት አስተዳደር ተቋማት፤ በትምህርት ቤቶች ፤ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም በስራችን የሚገኙ የተለያዩ የግል ድርጅቶች ሞዴል የሚሆኑ ስራዎች በአሳ እርባታ ፤በእንቁላል ጣይ ዶሮ፤ በመሬትና በሽቅብ የዱሮ አትክልት ትልቅ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የከተማ ግብርና ስራችን ውጤታማ እንዲሆን እና እንዲቀጥል በየወረዳው ከቤተሰብ ፍጆታ ያለፈ ምርት የሚያመርቱ አካላትን የገበያ ችግር እንዳይገጥማቸው በወረዳው የሰንደይ ማርኬት (የእሁድ ገበያ )እንዲሳተፍ እየተደረገ ይገኛል በተጨማሪም እንቁላል በቅናሽ ዋጋ እንደ ክፍለ ከተማ ለማዕከል ጋር በመነጋገር እየቀረበ ይገኛል።

በክ/ከተማችን ተሰማርተው ለሚገኙ ግለሰቦችና እና ማህበራት የድጋፍና ክትትል አግባባችን ምን በተመለከተ የክትትልና ድጋፍ ኮሚቴ በማዋቀር ወደ ስራ የተገባ ሲሆን ለአስሩም ወረዳዎች ባለሙያዎችን በመመደብ በሳምንት ሁለት ጊዜ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በየወሩ በክትትልና ድጋፍ የተገኙ ውጤቶችን በመገምገም እስካሁን እየተሰራ ይገኛል። የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ስራችን በተጨባጭ ገበያ በማረጋጋት ውስጥ ጉልህ ሚና አለው በአሁኑ ሰዓት የከተማ ግብርና ውጤቶችን በክፍለ ከተማችን ብሎም እንደ ከተማ ገበያውን የማረጋጋት ስራ ከህብረት ስራ ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት በመስራት የእንስሳት መኖዎችን (የእንቁላል ጣይ ዶሮ፤ የስጋ ዶሮ መኖ ፤የቄብ ዶሮ መኖ ፤የወተት ላም መኖ፤ የጊደር መኖ፤የጥጃ መኖዎችን) በቅናሽ ዋጋ ማቅረብ ተችሏል።

በክ/ከተማችን ያሉ የከተማ ግብርና ተጠቃሚዎች ከቤተሰብ ፍጆታ አለፈው ገበያውን የማረጋጋት ስራ በደንብ እየተወጡ ይገኛል ይህ ተግባር እንዲቀጥል የሁላችንም ርብርብ ክትትል መጠናከር አለበት። በመጨረሻም የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ስራ ውጤቱ በተጨባጭ የሚታይ በሰዎች ኢኮኖሚ ላይ በቀጥታ ተፅኖ የሚያደርግ ነው ፡፡ ልደታ እንደ ሌሎች ማስፋፊያ ክፍለ ከተማ ሰፋፊ መሬት ባይኖርም ባሉ ክፍት በታዎች ላይ የተሰሩት ስራችዎች በቅንጅት በባለሙያ እና ከላይ እስከታች ያለው አመራር ስለሚመራው ነው ፡፡ በመሆኑም አሁንም በተለያየ ጊዜ የሚገጥሙ ችግሮችን በርብርብ በመፍታት ውጤታማነቱን ማስቀጠል ያስፈልጋል ፡፡ በሌላ በኩል የክ/ከተማችን ወጣቶች በዚህ ዘርፍ ቢሰማሩ በአጭር ጊዜ ሀብት መፍጠር ሰለሚችሉ ተደራጅተው እንዲሰሩ ጥሪየን አቀርባለሁ።

## የፕሮጀክቶች አፈፃፀም በልደታ

የልደታ ክፍለ ከለተማ ዲዛይንና ግንባታ ጽ/ቤት የህንፃና የግንባታ ፕሮጀክቶችን በብቃት፣በግልጽነት እና በከፍተኛ ጥራት እንዲከናወኑና የህብረተሰቡን የአገልግሎት ፍላጎት ያማከሉ እንዲሆኑ በማድረግ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል።በክፍለ ከተማው የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች የነዋሪዎችን የልማት ጥያቄዎች የሚመልስና የከተማ አስተዳደሩ ፕሮጀክቶች እንዲፈጸሙ የሰጠውን የማስፈጸም ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።ዲዛይንና ግንባታ ጽ/ቤት በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ውስጥ ከፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ውጤታማ ስራዎችን ሰርቷል፡ ፡በተሰሩ ስራዎችም ከከተማው ጋር በመተባበር በክፍለ ከተማችን የሚሰሩ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ወቅት ተጠናቀው ለህብረተሰቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።

የዲዛይንና ግንባታ ጽ/ቤት በ2018 በጀት ዓመት እያከናወናቸው የሚገኙ ስራዎችን በተመለከተ የጽ/ቤቱን ኃላፊ አቶ ቢኒያም ሰይፉን ጠይቀን ያገኘነውን መረጃ እንደሚከተለው አቀናብረነዋል።



### አቶ ቢኒያም ሰይፉ
### የዲዛይንና ግንባታ ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-**በ2018 በጀት ዓመት የነበራቸሁ አፈጻጸም ምን እንደሚመስል ቢገልጹልን

**አቶ ቢኒያም፡-** የዲዛይንና ግንባታ ጽ/ቤት በ2018 በጀት ዓመት ባለፉት 6 ወራት ከተማ አስተዳደሩን በመወከል የህንጻና የተለያዩ የግንባታ ሥራዎችን ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ ውል በመፈጸም ፕሮጀክቶችን ወደስራ እንዲገቡ አድርጓል።ህግና ስርዓትን ተከትሎ በደስራ እንዲገቡ ካደረጋቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ ለከተማዋም ሆነ ለክፍለ ከተማችን አገልግሎት ወሳኝ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ በትምህርት፣በጤና እና በአገልግሎት ዘርፍ ያሉ አዳዲስ ግንባታዎች ተካተውበታል።ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ በሚገቡበት ወቅት ብቃትና ጥራት ያላቸው ኮንትራክተሮችና አማካሪዎችን በማካተት ነው።

ፕሮጀክቶችን ወደ ግንባታ ከገቡ በኋላ ተከታታይ የሆነ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በማከናወን ስራዎች በወቅቱ እንዲጠናቀቁና የሚፈጠሩ የቴክኒክ ችግሮችን ፈጣን የሆነ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ውል ከተፈረመ በኋላ የፕሮጀክቶች ሥራ አፈጻጸም በየጊዜው በቅርብ እንከታተላለን።የቴክኒክ ቡድኖቻችን የሥራውን ጥራት፣የጊዜ ሰሌዳውን አጠባበቅ እና በበጀት አጠቃቀሙ ላይ ተመጣጣኝ ክትትል አድርገዋል።በስድስት ወራቱ ውስጥ በሂደት ላይ ባሉ ፕሮጀክቶች ላይ የተነሱ የቴክኒክና የአስተዳደር ችግሮች በወቅቱ መፍትሔ አግኝተው ፕሮጀክቶቹ ወደፊት እንዲራመዱ ተደርጓል።ግንባታው ሲጠናቀቅም በውሉ እና በዲዛይኑ መሰረት መከናወኑን የሚያረጋግጥ ጥብቅ የጥራት ቁጥጥርና የሙከራ ሂደት ተከናውኖ ፕሮጀክቱን ከተረከብን በኋላ ግንባታው የተጠናቀቀለት ተቋም አገልግሎቱን በአግባቡ እንዲሰጥ የሚያስችለውን የባለቤትነት ሰነድና የዕቅድ ካርታ አዘጋጅተን የርክክብ ስራዎችን ሰርተናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**ፕሮጀክቶችን በምታከናውኑበት ወቅት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያላችሁ የቅንጅት ስራ ምን ይመስላል?

**አቶ ቢኒያም፡-** አንድ ሕንፃ ተገንብቶ ለአገልግሎ ሲዘጋጅ የከተማ መሠረተ ልማቶች ውሃ፣ መብራት ፣መንገድ፣ ቴሌኮም ወዘተ ወሳኝ ናቸው ። ስለሆነም ጽ/ቤታችን ለግንባታውም ሆነ ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ ለአገልግሎት መስጫነት የሚያስፈልገውን መሠረተ-ልማት እንዲያሟላ የማድረግ ኃላፊነት አለብን፡፡ ባለፉት ስድስት ወራት በመጠናቀቅ ላይ ያሉ እና አዲስ የተረከብናቸው ሕንፃዎች በፍጥነት ሥራ እንዲጀምሩ ለማስቻል፣ለሚመለከታቸው የመሠረተ ልማት አቅራቢ አካላት በቅንጅት ስራ ተሠርቷል፡፡

በዚህ ረገድ፣ የፕሮጀክቶቹን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የተቀመጡትን መስፈርቶችና የጊዜ ገደቦችን የሚገልጽ ዝርዝር ጥያቄ ለሚመለከታቸው የመሠረተ ልማት ተቋማት ቀርቧል።ባቀረብነው ጥያቄ መሰረት የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የመሠረተ ልማት ሥራው በተቀመጠው የጥራት ደረጃና የጊዜ ገደብ የመሰረተ ልማት ስራዎች እንዲከናወኑ በማድረግ ፕሮጀክቶች ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ አድርገናልለለ፡፡ ይህን ተግባር ማከናወናችን ትላልቅ የሆኑ የመንግስት ተቋማትና ፕሮጀክቶች ወዲያውኑ አገልግሎት መስጠት እንዲጀምሩ በማድረግ ለከተማ ነዋሪዎች ምላሽ መስጠት ችለናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ስራዎች ሲሰሩ በሚፈጠሩ የውል ጥሰቶችና ጉድለቶች ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን በተመለከተ ቢያብራሩልን

**አቶቢኒያም፡-**ስራዎችበሚሰሩበትወቅትፕሮጀክቶችንበሚያከናውኑ ፕሮጀክቶች ግልጽነትን፣ጥራትንና የከተማ አስተዳደሩን ጥቅም ማስጠበቅ እንዱሁም የህብረተሰቡን የአገልግሎት ፍላጎት ያሟሉ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይህ በማይሆንበትና ስራዎች በሚሰሩበት ወቅት የሚታዩ ክፍተቶች ሲፈጠሩ ችግሩን ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶችን እናደርጋለን፡፡በ2018 በጀት ዓመት የስድስት ወራት አፈጻጸም ወቅት፣የውል ግዴታቸውን በአግባቡ ያልተወጡ ኮንትራክተሮችና አማካሪዎች ላይ ተመጣጣኝ ህጋዊ እርምጃዎችን ወስደናል፡፡ ከተወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ ጉድለቶችን በግንባታው ሂደት ወይም ሥራውን ከተረከብን በኋላ በሚታዩ ጉድለቶችና የጥራት ማነስ ላይ፣በውሉ መሠረት እርማቶች እንዲደረጉ እና ለጉድለቱ ተጠያቂ የሆኑት አካላት በፍጥነት የጥገና ሥራ እንዲያከናውኑ ጥብቅ ማስጠንቀቂያና የሥራ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

በውሉ መሰረት ባልተፈጸሙ ስራዎች፣ለምሳሌ የጊዜ መራዘም ወይም የሥራው ጥራት መጓደል ላሳዩ አካላት በኮንትራቱ መሠረት የገንዘብ ቅጣቶች ተጥለዋል።እርምጃው መወሰዱ ከባድ የሆኑ የውል ጥሰቶችና ጥፋቶች በቀጣይ እንዳይሰሩና የከተማ አስተዳደሩ የያዛቸው የፕሮጀክት አፈጻጸሞች የተሳኩ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በግንባታው ዘርፍ ክፍተቶች ሲፈጠሩ አፋጣኝ የሆነ እርምጃ መወሰዱ ሥርዓትን በማስፈንና ቀሪ ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ጥራት እንዲከናወኑ በማነሳሳት ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ፕሮጀክቶች ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር ያላቸው ሚና ቢገልፁልን?

**አቶ ቢኒያም፡-** በክፍለ ከተማው የሚገነቡት ፕሮጀክቶች የመጨረሻው ዓላማ የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻልና በተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረግ ነው።ከዚህ ጋር በተያያዘም አዲስ የተገነቡት የጤና ጣቢያዎች ለብዙ ሺህ ነዋሪዎች የጤና አገልግሎት ቅርብ በማድረግ የበሽታ መከላከልና ህክምና አገልግሎት ተጠቃሚነትን ያሳድጋሉ፡፡ የአዳዲስ ትምህርት ቤቶች ግንባታ ደግሞ የክፍል ጥበትን በመቀነስ የትምህርት ጥራት እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡ ግንባታዎች በሚካሄዱበት ወቅት የአካባቢው ነዋሪዎች በሥራ ላይ በመሰማራት የስራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በግንባታ ግብአት አቅርቦት ሂደት ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ሆነዋል።ፕሮጀክቶቹ ተጠናቀው ወደ ስራ ሲገቡ የክፍለ ከተማችንን ገጽታ በማዘመን ለነዋሪዎች ምቹ የሆነ የከተማ አካባቢ እንዲፈጠር ከማድረግ ባለፈ የሚፈልጉትን አገልግሎት በቅርበትና በጥራት እንዲያገኙ በማድረግ ኑሮን ቀላል ያደርጋሉ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች በሚፈለገው ልክ አገልግሎት እንዲሰጡ ምን መደረግ ይገባዋል ይላሉ?

**አቶ ቢኒያም፡-** የተጠናቀቁን ለህብረተሰቡ አገልግሎት ላይ የዋሉ ፕሮጀክቶች ለረጅም ዓመታት ሳይበላሹ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ለማድረግ መንግስትን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡ ዘላቂነትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ጽሕፈት ቤታችን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል።የተጠናቀቁ ሕንፃዎች ከተረከብን በኋላ በአገልግሎት ሰጪው ተቋም ዘላቂ እንክብካቤ እንዲያገኙ የሚያስችል የጥገና መመሪያና የክትትል ሥርዓት ማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድረግ ፕሮጀክቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችሉ ስራዎችን ልንሰራ ይገባል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በስተመጨረሻም መልዕክት ካለዎት

**አቶ ቢኒያም፡-** በ2018 በጀት ዓመት ባለፉት 6 ወራት በክፍለ ከተማችን በርካታ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡የፕሮጀክቶች ወደስራ መግባትም ህብረተሰቡ የሚፈልገውን አገልግሎት እንዲያገኝ ከማስቻላቸውም በላይ አካባቢያቸውን ለመኖሪያ ምቹ እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡

ይህን አፈጻጸም በቀጣዮቹ ስድስት ወራትም በማጠናከር በሂደት ላይ ያሉ የልማት ፕሮጀክቶችን በፍጥነትና በጥራት የማጠናቀቅ፣የኮንትራት አስተዳደር ስርዓታችንን በቴክኖሎጂ በመታገዝ ይበልጥ የማዘመን እና የተጠያቂነት ስርዓቱን ይበልጥ በማጠናከር ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው ወደስራ እንዲገቡ ሁላችንም ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል የሚል መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።

## መስሪያ ቦታዎች ለፍትሃዊ ተጠቃሚነት

የልደታ ክ/ከተማ የመስሪያ ቦታዎች ልማት እና አስተዳደር ጽ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 84/2016 በአዲስ መልኩ ተቋቁሞ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ይገኛል። ጽ/ቤቱ የመስሪያ ቦታዎችን በማልማት እና በማስተዳደር በዘርፉ ያለውን የመስሪያ ቦታዎች ልማት እና አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ የተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት በዋናነት የማምረቻ፣ የመሸጫ እና ማሳያ ማዕከላትን የማስገንባት፣የማስተላለፍ፣የማስተዳደር እና የቁጥጥር ስራዎችን እንዲያከናውን የተቋቋመ ነው። በ2018 በጀት አመት የተለያዩ መስሪያ ቦታዎችን በመገንባትና መሰረተ ልማት በማሟላት ለስራ ፈላጊ ዜጎች በማስተላለፍ ውጤታማ ስራ ተሰርቷል። በህገ ወጥ መልኩ የተያዙ መስሪያ ቦታዎችን በማስለቀቅ ለስራ ፈላጊዎች ዝግጁ የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

በመሆኑም መስሪያ ቦታዎችን በአሰራሩና በመመሪያው መሰረት በማስተዳደር የነዋሪዎችን የመስሪያ ቦታ ጥያቄ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለመመለስ የተከናወኑ ስራዎች በምን አግባብ እየተከናወኑ እንደሆነ የዝግጅት ክፍላችን ከመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊ ወ/ሮ ብርቱካን ባህሩ ጥያቄዎችን በማቅረብ የሰጡንን ማብራሪያ እንዲህ አቅርበነዋል መልካም ንባብ ።



### ወ/ሮ ብርቱካን ባህሩ
### የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና ፡-** የመስሪያ ቦታዎችን ከማልማትና መሰረተ ልማት ከማሟላት አንፃር የተከናወኑ ተግባራት ቢገልፁልን?

**ወ/ሮ ብርቱካን ባህሩ፡-** በባለፈው በጀት አመት የመስሪያ ቦታዎችን ከማልማት ና የዜጎችን ስራ ፈጠራን ከማሻሻልና የስራ እድል ከመፍጠር አኳያ 3 ደረጃቸውን የጠበቁ እያንዳንዳቸው 120 ካሬ ሜትር የሆኑ የመስሪያ ቦታዎችን ልዩ ስሙ ሳህሉ ጫካ ላይ የመገንባት ስራ ተሰርተዋል።

በ2018 በጀት አመት መስሪያ ቦታዎች ለማልማት 3 ሼድ ግንባታ ፤30 ኮንቲነር ሱቆችን ግንባታ እና 3 ህንጻ እድሳት ለማከናወን 57.000.000(ሃምሳ ሰባት ሚሊዬን ብር) በላይ በጀት እንዲበጀት የተደረገ ሲሆን ከዲዛይንና ግንባታ ጽ/ቤት ጋር ከዲዛይን ዝግጅትና ግንባታ ጋር ተያይዞ በጋራ እየሰራን እንገኛለን ።በተጨማሪ በአመቱ ለመስሪያ ቦታ መገንቢያ የሚያገለግል መሬት ከክፍለ ከተማው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር በመሆን 1514.88 ካሬ ቦታ የመለየት ስራ ተሰርተዋል። መሰረተ ልማት ከሟሟላት አንጻር ለ11 ኢንተርፕራዞች 7 መብራት ቆጣሪ የሟሟላት ስራ ተሰርተዋል። በዚህም 34 አንቀሳቃሾች እንዲጠቀሙ የተደረገ ሲሆን ለዚህም 155,826.85 (አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ሺ ስምንት መቶ ሃያ ስድስት ከሰማንያ አምስት ሳንቲም) በጀት ወጪ ተደርገዋል። በተጨማሪ 2 ውሃ ቆጣሪ ለ2 ተጠቃሚ ኢንተርፕራዞች የማስገባትና ተጠቃሚ የማድረግ ስራ ተሰርተዋል።



## ለተጠቃሚዎች እጣ አወጣጥ ስነ-ስርዓት

**ልደታ ፋና ፡-** የመስሪያ ቦታዎችን ለተጠቃሚዎች በፍትሃዊነት ከማስተላለፍ አንፃር የተከናወኑ ተግባራት ምንድንናቸው ?

**ወ/ሮ ብርቱካን ባህሩ፡-** በ2018 በጀት ዓመት እስከ ጥቅምት 30/2018 ዓ.ም. ድረስ ለ**53** ኢንተርፕራይዞችና ለ**128** አንቀሳቃሾች **1627.25** ካ.ሜ የመስሪያ ቦታ ማስተላለፍ የተቻለ ሲሆን በዚህም **74** ወጣቶች፡**60** ሴቶች፤**7** አካል ጉዳተኞች እንዲሁም **1** ከስደት ተመላሽ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል።

ከዚህ በተጨማሪ ለ**3** ኢንተርፕራይዞችና ለ**7** አንቀሳቃሾች **480** ካ.ሜትር የመስሪያ ቦታ ማስፋፊያ እንዲያገኙ ተደርጓል።
ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱ ተግባራትን በፍትሃዊነት ከመስራት አኳያ፡
-
አዲስ የመስሪያ ቦታ የወሰዱ ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ የሁሉንም አንቀሳቃሾች ፋይል የሚልከው የስራና ክህሎት ጽ/ቤት መረጃቸውን አጣርቶና በፕሮሰስ ካውንስል ወስኖ ሲሆን እንደ እኛ ተቋም ደግሞ ከስራና ክህሎት ጽ/ቤት ተወስኖ የመጣውን ፋይል አንድ በአንድ በባለሙያዎች ካረጋገጥን በኋላ ፋይላቸው የተሟላውን በመቀበል ፋይላቸው ክፍተት ያለባቸውን የኢንተርፕራይዝ መረጃ ለስራና ክህሎት ጽ/ቤት ተመላሽ እናደርግላን። ፋይላቸው የተሟላውን ኢንተርፕራይዞች ፋይል በፕሮሰስ ካውንስል ከወሰነ በኋላ ለመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ በደብዳቤ የኢንተርፕራይዞችን ዝርዝር፡የስራና ክህሎት ጽ/ቤት ፕሮሰስ ካውንስል ውሳኔና ደብዳቤ ከጽ/ቤታችን ፕሮሰስ ካውንስል ውሳኔ ጋር በደብዳቤ ልከን የማጸደቅ ስራ እንሰራለን።

በመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ በኩል ውሳኔ ሲሰጥበት ደግሞ ፍትሃዊነቱን በጠበቀ መልኩ ለሁሉም አንቀሳቃሾች ጥሪ ከተደረገ በኋላ በማስተላፍ ፕሮግራሙ ላይ እንዲገኙ በማድረግና የሚመለከታቸው አካላት ጥሪ በማስተላለፍ በሚዲያ ፊት እጣ እንዲያወጡ በማድረግ ፍትሃዊነቱን በጠበቀ መልኩ የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል።

አንቀሳቃሾች የመስሪያ ቦታ ዕጣ ካወጡ በኋላ በደረሳቸው የዕጣ ቁጥር መሰረት ዕጣ ካወጡበት ቀን ጀምሮ በ20 ቀናት ውስጥ ሁሉም የኢንተርፕራይዝ አባላት የደረሳቸውን የዕጣ ቁጥር በመያዝ በክፍለ ከተማው የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት በመገኘት የመስሪያ ቦታ ውል እንዲወስዱ ከተደረገ በኋላ የደሰሳቸውን የመስሪያ ቦታ በአካል የማስረከብ ስራ ይሰራል።



## ለተጠቃሚዎች ሲተላለፍ

**ልደታ ፋና ፡-** የሼዶች የውል ዕድሳትና አገልግሎት አተገባበር ዙሪያ ምን ምን ስራዎች ተሰርተዋል?

**ወ/ሮ ብርቱካን ባህሩ፡-** ለ313 ኢንተርፕራይዞች ውል የማደስ ስራ ተሰርቷል።ከዚህም ለመደበኛና ለውዝፍ 1,211,385 ብር የመስሪያ ቦታ ኪራይ ክፍያ መሰብሰብ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** ህገ- ወጥነትን ከመከላከል አንፃር የተሰራ ስራ ካለ ቢገልፅ ?

**ወ/ሮ ብርቱካን ባህሩ፡-** ህገወጥነትን መከላከል ላይ የተሰጣቸውን የመስሪያ ቦታ ላይ ወደ ስራ ባልገቡ 7 (ሰባት) ኢንተርፕራይዞች ውል በማቋረጥ እንዲታሽግባቸው ተደርጓል ።በመስሪያ ቦታ 5 ዓመትና ከዚያ በላይ የተጠቀሙ 19 ኢንተርፕራይዞች 737.13 ካሬ ሜትር ቦታ የማስለቀቅ ስራ ተሰርቷል ።

ልደታ ፋና፡- የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?
ወ/ሮ ብርቱካን ባህሩ፡- በክፍለ ከተማችን የመስሪያ ቦታ በማጣት ወደ ስራ መግባት ላልቻሉ ወጣቶች በህትመት፣ የወንዶችና የሴቶች ዉበት ስራ፣በቆዳ እና የቆዳ ዉጤቶች፣በልብስ ስፌት እና በሽመና ስራ በእነዚህ የስራ ዘርፎች በርካታ ሰዉ ማሰጠቀም የሚችል መሰረተ ልማት የተሟላለት ክፍት ቦታ ስላለን በክፍለ ከተማችን ያሉ ወጣቶች በስራ እና ክህሎት ጽ/ቤት በኩል ህጋዊ አደረጃጀታቸዉን ጨርሰው ቢመጡ ማስጠቀም የምንችል መሆኑን መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።
ልደታ ፋና ፡- ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።
ወ/ሮ ብርቱካን ባህሩ፡- ፡- እኔም አመሰግናለሁ።

## ሰላም ለሀገር ልማት

ሰላም የጦርነት አለመኖር ወይም ያለመረበሽ ነፃነት ማለት ነው። በሌላ በኩል ሰላም እርቅ፣ ፀጥታ፣ የእርጋታ ሙሉነት፣ ስኬት ቅንጅት፣ሁለንተናዊ ደህንነት፣ የሚለውን የሰውንና የማህበረሰብ አጠቃላይ ቅኝት የሚወክል ነዉ። ሰላም ለሀገር ግንባታ ያለዉ ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በየትኛዉም መልኩ ከማንኛዉም ሰላምን ሊያዉኩ ከሚችሉ ሁከትና ሌሎች ተግባራት፣ ከስጋት ሙሉ በሙሉ ነጻ ሆኖ መኖር ሲሆን ምንም እንኳን በሰላም ለመኖር ከጦርነት፣ከሁከት ጫጫት ለመዉጣት ነገሮች ከባድ ቢሆንም ከእዚህ ችግር ለመዉጣት ግን ትግል ማድረግ ግድ ይለናል።

ከሰላም ጋር የማይነጣጠለዉና ለማህበረሰቡ አስፈላጊ የሆነዉ ጸጥታ መስፈን ደግሞ ጤናማ ማህበረሰብ ለመፍጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ጉዳይ ነዉ። እንደ ልደታ ክፍለ ከተማም የማህበረሰቡን ሰላምና ጸጥታ የተጠበቀ ለማድረግ በተለያዩ ጊዜያት የሚከበሩ የአደባባይ በአላቶችም ካለምንም ስጋትና ሀሳብ ተከብረዉ እንዲያልፉ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ በመሆኑ የተሻለ አፈጻጸም ማምጣት ተችሏል። ለእዚህ ደግሞ የክፍለ ከተማዉ ሰላምና ጸጥታ ጽ/ቤት ትልቁን ሃላፊነት ወስዶ ከማህበረሰቡ ጋር በጋራ በመስራት ዉጤት ማስመዘግብ ችሏል። ልደታ ፋናም ይህንን ጉዳይ ያሳካበትን ሂደት አስመልክቶ ከጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ ቶሎሳ መርጋ ጋር አጠር ያለ ቃለ መጠይቅ አድርጓል እናንተ ዉድ አንባቢያን ደግሞ እንድትከታተሉን ጋበዝናችሁ መልካም ቆይታ

**ልደታ ፋና፡-** ዘንድሮ በተከበሩ የአደባባይ በዓላቶች ላይ ሰላምና ጸጥታቸዉ የተጠበቀ እንዲሆን ምን ምን ስራዎች ተሰርተዋል?
**አቶ ቶሎሳ መርጋ፡-** በ2018 በጀት አመት የመጀመሪያዉ 6 ወር የተከበሩ ትላልቅ የአደባባይ በአላት ያለምንም የፀጥታ ችግር በሰላም እንዲጠናቀቁ ከቅድመ ዝግጅት ጀምሮ በፀጥታ ጥምር ሀይል ዕቅዶችን በማቀድና የጋራ በማድረግ ወደ ስራ በመግባት ለበአላቱ ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን በመለየት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ ችለናል።

ሰላም ወዳድ የሆነው የህብረተሰብ ክፍላችን ደግሞ በአላቱ በሰላም እንዲጠናቀቁ ትልቁን ድርሻ የሚወጣ በመሆኑ የተለያዩ የአደባባይ በዐላት ከመድረሳቸው በፊት ከብሎክ ጀምሮ በወረዳ እና በክ/ከተማ ደረጃ መድረኮችን በማዘጋጀት ክብረ በዓላቱ በሰላም እና ጸጥታ መከበር በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ በመወያየት የፀጥታው አጋዥ እና የሰላሙ ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል። በበዓላቱ ወቅትም የፀጥታ አካሉ፣የሰላም ሰራዊቱና ሌሎች የፀጥታ አደረጃጀቶችን በማቀናጀት ስምሪት በመስጠት ጥብቅ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በመስራት በዓላቱ በሰላም ተከብረዉ እንዲጠናቀቁ ማድረግ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** ከበአላት እና ከሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ችግሮች ሲፈጠሩ የሚወሰደዉ መፍትሄ ምንድነዉ?
**አቶ ቶሎሳ መርጋ፡-** እንደ ሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት በዋናነት ከሚሰሩ ስራዎች መካከል ቅድመ መከላከል ላይ ያተኮሩ ስራዎችን መስራት አንዱ ሲሆን ይህም ችግሮች ከመፈጠራቸው በፊት ቅድመ ትንተና አዝማሚያዎች በመስራት እርምጃ መውሰድን ጨምሮ ለሰላም ሰራዊቱና ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በወቅታዊ የፀጥታ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ በማስጨበጥ ወንጀል እና ህገወጥ ድርጊቶችን ቀድሞ መከላከል ላይ ባተኮረ መልኩ ስራዎችን የሚሰራ ተቋም ነው።

ይህም በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ ወቅታዊ የፀጥታ ችግሮች ሲከሰቱ ከፀጥታ መዋቅሩ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ስራዎችን በመስራት ችግሩን የፈጠሩ ምክንያቶችን ፣ግለሰቦችን እና ተቋማትን በመለየትና በማጥናት እንደ ችግሩ አይነት በመለየት ችግሩ በውይይት የሚፈታ ከሆነ በማወያየት እንዲፈታ የማድረግ ስራ የሚሰራ ሲሆን ችግሩን በውይይት መፍታት የማይቻልና ሌሎች የፀጥታ ችግሮችን የሚፈጥር ሆኖ ሲገኝ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።



**አቶ ቶሎሳ መርጋ**
**የሰላምና ጸጥታ ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** የክፍለ ከተማዋን ነዋሪ ካለምንም ስጋት እንዲንቀሳቀስ የተሰራ ስራ አለ?
**አቶ ቶሎሳ መርጋ፡-** የክ/ከተማው ነዋሪ ያለምንም ስጋት እንዲንቀሳቀስ ከተሰሩ ስራዎች መካከል በዋናነት የህብረተሰብ ክፍሉ የሰላሙ ባለቤት እንዲሆን እና የማህበረሰብ አቀፍ የፀጥታ

አጠባበቆች ላይ እንዲሳተፍ በማድረግ ከፀጥታ አካላት ጋር ተቀራርቦ እንዲሰሩ በማድረግ ስጋት የሆኑ አካባቢዎችን እንዲለዩ እና ወንጀል ፈፃሚ ግለሰቦችንና ፀጉረ ልውጦችን እንዲያጋልጡ በማድረግ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል። በዚህም ህብረተሰቡ የሰላሙ ባለቤት እንዲሆን በመደረጉ ወንጀል በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ጭምር ማድረግ ተችሏል።

በምሽት ክፍለ ግዜ ለመንቀሳቀስ ስጋት የነበሩ ጨለማ አካባቢዎችን በመለየት ህብረተሰቡን በማስተባበር የደጅ መብራት እንዲወጣ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በዋና ዋና መንገዶች የነበሩ ጨለማ አካባቢዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በተሰሩ የቅንጅት ስራዎች መብራት እንዲገጠም በማድረግ ከስጋት ነፃ የማድረግ ስራ ተሰርቷል። ህብረተሰቡ ለመንቀሳቀስ ስጋት ከነበሩ ጉዳዮች መካከል ጫካማና ጢሻ የነበሩ አካባቢዎችን ከፀጥታ አካሉና ከሰላም ሰራዊቱ ጋር በቅንጅት የማስመንጠር ስራ በመስራት ከስጋት ነፃ የማድረግ ስራ መስራት ተችሏል።

በሌላ በኩል የንጥቂያ ወንጀል በመፈፀም በትቦ ውስጥ በመግባት ለሌቦች መሸሸጊያ የነበሩ ክፍት ትቦዎችን ባለሀብቶችን በማስተባበር የማስደፈን ስራ መስራት ተችሏል። በተደጋጋሚ ጊዜ የወንጀል ድርጊት ይፈፀምባቸው የነበሩ አካባቢዎችን በሁሉም ወረዳ በመለየት ባለሀብቶችን በማስተባበር የደህንነት ካሜራ የማስገጠም ስራ መስራት ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** ወንጀልን በጋራ ለመከላከልና ማህበረሰቡ በንቃት አካባቢዉን እንዲጠብቅ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎች ምንድናቸዉ?
**አቶ ቶሎሳ መርጋ፡-** የህብረተሰብ ክፍሉ በሰላምና በፀጥታ ዙርያ ተደጋጋሚ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እየተሰራ ሲሆን በሳምንት ሁለት ቀን በማህበረሰብ አቀፍ የምክክር መድረክ በየብሎኩ በፀጥታ ዙርያ የማወያየት ስራ እየተሰራ ይገኛል።

ህብረተሰቡ በሰላም ሰራዊት እና በተለያዩ የፀጥታ አጋዥ አደረጃጀቶች እንዲደራጅ በማድረግ እና የንድፈ ሀሳብ እና የመስክ ስልጠናዎችን በመስጠት የአካባቢያቸውን ፀጥታ እንዲያስጠብቁ በማድረግ በማህበረሰብ አቀፍ የፀጥታ አጠባበቅ ተግባራዊ እንዲደረግ በማድረግ ማህበረሰቡ በንቃት አካባቢውን እንዲጠብቅ ስራዎች ተሰርተዋል እየተሰሩም ይገኛል።

**ልደታ ፋና፡-** የሚያስተላልፉት መልዕክት አለ?
**አቶ ቶሎሳ መርጋ፡-** የሰላምና የፀጥታ ጉዳይ የአንድ ተቋም ብቻ ተግባር ባለመሆኑ የከተማችንን ብሎም የክ/ከተማችንን ሰላም በማስጠበቅ ላይ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚናን የሚጠይቅ በመሆኑ የሚሰሩ የቅንጅት ስራዎችን በማጠናከር እና እየተሰሩ ያሉ ህብረተሰቡን የሰላም ባለቤት የማድረግ ስራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በማድረግ ህብረተሰቡ ወንጀልና ህገ-ወጥ ተግባራትን እንዲያጋልጥና ከፀጥታ አካሉ ጋር በቅንጅት በመስራት የሰላም ባለቤትነቱን እንዲያረጋግጥ በማድረግ ሰላምና ፀጥታዋ የተጠበቀ ዜጎች በሰላም ወጥተው የሚገቡባት ክፍለ ከተማን መፍጠር ላይ ያተኮረ የፀጥታ ስራ በመስራት የብልፅግና ጉዞዎችንን ማረጋገጥ ላይ ትኩረት አድርገን መስራት ይኖርብናል።

**ልደታ ፋና፡-** ስለ ነበረን የቃለ መጠይቅ ጊዜ በዝግጅት ክፍሉ ስም እናመሰግናለን።
**አቶ ቶሎሳ መርጋ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# እንግልትን የቀነሰ ተቋም

በልደታ ክ/ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽ/ቤት አገልግሎቱን በተገቢው መንገድ ለማከናወንና ማስረጃው ለህጋዊ፣ ለኢኮኖሙያዊ ለአስተዳደራዊና ለማህበራዊ አገልግሎት እንዲውል ለማድረግና ህብረተሰቡን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የነዋሪነት አገልግሎት አሰጣጥና የወቅታዊ ኩነት ምዝገባ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል። የበጀት ዓመቱ እቅድ እንዲሳካም ከባለሙያ በየደረጃዉ የሚገኙ አመራሮች የራሳቸዉን ሚና እየተወጡ ነዉ። በእዚህ ተቋም የተለያዩ የመረጃ ስራዎች የሚሰሩበት ለማህበረሰቡም በፈለገዉ ሰዓት የፈለገዉን ጉዳይ አስፈጽሞ የሚሄድበት መንግስታዊ ተቋም ነዉ። በዛሬዉ አምዳችንም ከላይ የጠቀስኩት የልደታ ክፍለ ከተማ ሲቪል ምዝገባና የነዋሪዎች አገልግሎት ጽ/ቤት ያከናወናቸዉ ዉጤት ተኮር ተግባራትን ይዞላችሁ መጥቷል እናንተ ደግሞ በንባብ ተከታተሉን መልካም ቆይታ!

**ልደታ ፋና፡-**አገልግሎቱን በቴክኖሎጂ በመሰጠቱ የመጣ ለውጥ ምንድነዉ?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** የመረጃዎችን ደህንነት የማስጠበቅ፣ብልሹ አሰራርን የመከላከል፣የአገልግሎት አሰጣጡን ቅልጥፍና እና ተደራሽነት ማስፋት እንዲኖር አስችሏል።

ለአብነትም የአንድን የአገልግሎት ሂደት ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ (States Viewer) 100% መታወቂያዉ ታትሞ እስኪጠናቀቅ ድረስ ያለዉን ሂደት እና በማዕከል የሚደረገዉን የወረቀት ቅብብሎሽ ብክነት ለማስቀረት የወረቀት አልባ ሲስተምን ከክፍለ ከተማ እስከ ወረዳ ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ሙሉ ለሙሉ በቴክኖሎጂ ዲጂታላይዝድ ማድረግ፣የተለያዩ ክፍያዎችን በቴሌ ብር እንዲከፈል በማድረግ በእጅ የገንዘብ ንክኪ እንዳይኖርና አገልግሎትን በኦንላይን በመስጠት የተገልጋዮችን እንግልት መቀነስ መቻሉ ይህ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት በመስጠታችን የመጣ ለዉጥ ነዉ።

**ልደታ ፋና፡-**ብልሹ አሰራርን እና ሌብነትን ለመከላከል የተሰሩ ስራዎች ካሉ ይግለጹልን?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** በተቋማችን ብልሹ አሰራርን ለመቅረፍ ዘርፈ ብዙ ተግባራቶችን ማከናወን ተችሏል። ለምሳሌ የጥቆማ ስርዓቱን በማዘመን በነጻ የስልክ መስመር 7533 ተሰርቷል.አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ እንዲሰጡ ተደርጋል።

**ልደታ ፋና፡-** አገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ የተሰሩ ስራዎች ምንድናቸዉ?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** በ8 ጤና ጣቢያዎች እና በ4 ሆስፒታሎች ጋር በጋራ በመስራት ህጻናት በተወለዱ በ24 ሰዓት ዉስጥ የልደታ ካርድ እንዲሰጡ ተደርጓል።እስካሁንም ለ1723 አካላት የልደት ሰርተፍኬት መስጠት ችለናል።

በፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ጋር ቅንጅት በመፍጠር በበጀት ዓመቱ 147 የፍቺ ሰርተፍኬት መስጠት ችለናል

ከእድር እና የሀይማኖት ተቋማት ጋር በጋራ እየሰራን እንገኛለን።

ቢሮዎችን ለተገልጋይ ምቹ ከማድረግ አኳያ ወረዳ 2.3፣10 ማዘመን ችለናል ።

በበጀት ዓመቱ የnid ምዝገባ 43176 ተመዝግቧል



## ወ/ሮ ዘነበች እረና
## የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** የመልካም አስተዳደር ችግሮች አፈታትና ቅሬታ ከመቀነስ አንጻር አፈጻጸሙ ምን ይመስላል?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** በየወረዳዎች የመብራት መቆራረጥ ችግር ለመፍታት በየወረዳው ጄነሬተር እንዲዘጋጅ በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ተደርጎል እዲሁም ለሁለት ወረዳዎች ማለትም ወረዳ 3፣5 ለ24 ሰዓት የሚሰራ የሦላር ሲስተም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሎል።

በአካል ተገኝተው አሻራ መስጠት የማይችሉ አቅመ ደካማና ያልጋ ቁራኛ የሆኑ ለ68 ተገልጋዮች በየወረዳው የቤት ለቤት አገልግሎት እንዲሰጣቸዉ ተደርጓል።

የተለዩ ወረዳዎች መረጃ የማስተካከል ችግርን ለመፍታት በበጀት ዓመቱ በልዩ ሁኔታ ትኩረት በመስጠት ለ43 ተገልጋዮች መስራት ወይም ማስተካከል ተችሏል

የሲስተም መቆራረጥ ችግር ለመፍታት ለሊት ቀድሞ በመግባትና አምሽቶ እንዲሁም አድሮ በመስራት ችግሩ እዲቃለል ለማድረግ የተከሄደበት ጥረት የተሻለ ነው እነዚህንና መሰል የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት ወይም ለመቀነስ በተደረገዉ ጥረት በበጀት ዓመቱ 5 ቅሬታን ቀርቦ 4ቱ የተፈታ ሲሆን 1 አግባብነት የሌለው በመሆኑ ወደ ሚመለከተዉ እንዲላክ ተደርጓል።

**ልደታ ፋና፡-** በአሰራሩ ሂደት የገጠሙ ችግሮች ምንድናቸዉ?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** በአብዛኛዉ የምንሰራዉ ስራ በሲስተምና በመብራት የሚሰራ በመሆኑ አልፎ አልፎ የመቆራረጥ ይህ ችግር ይገጥማል፡ የሰዉ ሃይል እጥረት አለ ነገር ግን ይህንን ችግር ለሚመለከተዉ አካል በማሳወቅ በዉሰትም ቢሆን የሚማላት እና ስራዉ እንዳይጎዳ የሚቻለዉን ሁሉ መፍትሄ ወይም አቅም አሟጠን እየተጠቀምን ነዉ፡፡ ሌላዉ ወረፋ እንዳይኖርና ስራዉ እንዳይደራረብ በማሰብ አምሽቶ አድሮ እና ቀድሞ በመግባት እንዲሰራ እየተደረገ ነዉ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**ወ/ሮ ዘነበች፡-** የክፍለ ከተማችን ሲቪል ምዝገባና የነዋሪዎች አገልግሎት ጽ/ቤት በዉስጡ የሚያከናዉናቸዉ ተግባራቶች ቀላል ያልሆኑና ጉልህ ሚና ያላቸዉ ሰራዎችን የሚሰራ ተቋም እንደመሆኑ መጠን አፈጻጸሙንም የተሻለ ለማድረግ ይህ የማይባል ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡ በይብለጥም አሰራሩን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ ኋላቀር አሰራሮችን እያሻሻልን እንገኛለን፣የተገልጋይን እንግልት ለመቀነስም እንደእዚሁ የሚታይ ስራ መስራት ችለናል በቀጣይም ይህ ተግባር የተሳለጠ ፍሬዉም ያማረ እንዲሆን የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ትልቁን ሚና ስለሚወጣ እንዲያግዙን በእዚሁ አጋጣሚ ለማሳሰብ እወዳለሁ አመሰግናለሁ፡፡

## ትውልድን በስነ- ምግባር ተቋምን በአሰራር

ሙስና ለግል አሊያም ለቡድን ጥቅም ሲባል ስርዓቶችን፣ ህጎችን፣ ደንቦችን፣ አሰራሮችንና መርሆዎችን መጣስ ነው፡፡ሙስና አደራን አለመጠበቅ እምነትን ማጉደል በጉቦና በምልጃ ፍትህን ማዛባት እና የራስ ያልሆነን ጉዳይ ስልጣንን መከታ በማድረግ ለራስ ማድረግ የሚያካትት ነው፡፡ ሙስና ሁሉንም የሚነካ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው የሚለዋወጥና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው፡፡ ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም በርካታ ናቸው፡፡

ይህ ተለዋዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት በየጊዜው የሚሻሻል የተቀናጀ ስልት መንደፍና የግንዛቤ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና መከታተያ ክፍል ሰራተኞች ለተለያዩ ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመታገል ተቀናጅተው የሚሰሩበትን መንገድ ዕያመቻቸ ይገኛል፡፡ የልደታ ክፍለ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና መከታተያ ክፍል በ2018 በጀት ዓመት ሙስናን ለመከላከል ያከናወነውን ስራ የክፍሉን የስራ አስተባባሪ ወ/ሮ እማዋይ አበባውን ጠይቀን ያገኘነውን መረጃ እንደሚከተለው አቅርበነዋል መልካም ንባብ፡፡



## ወ/ሮ እማዋይ አበባው
## የስነ- ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪ

**ልደታ ፋና፡-** የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዋና ዓላማዎች ምንድን ናቸው?

**ወ/ሮ እማዋይ፡-** የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል ዜጎች ሙስና ላይ ያላቸው ግንዛቤ እንዲያድግና ሙስናን የሚጠየፍ ትውልድ ለመፍጠር በትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡ የስነ ምግባርና ጸረ ሙስና መከታተያ ክፍሉ በማናነት ትምህርቶችን በማስፋፋት የሞራል እሴቶችን በመገንባት የነቃ እና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ኅብረተሰብ መፍጠር፤ የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሠራርን መከላከል፤ ነዋሪው የፀረ-ሙስና ትግል ባለቤት እንዲሆን ማድረግ፤ በጸረ ሙስና ትግል ብልሹ አሰራርን ለማስቀረት ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ሥረዓት ማስፈን እና በህግ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት ነው የሚለውን ዓላማ በማንገብ የተያዘው ዓላማ ግቡን እንዲመታ የሚያስችሉ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡

የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍሉ ዋና ዓላማ ከኮሚሽኑ ዓላማ ጋር የተሳሰረ ሲሆን፣በዋናነት ሙስናና ብልሹ አሰራር ለከተማችን ልማትና ለመልካም አስተዳደር እንቅፋት እንዳይሆኑ መከላከል ነው፡፡

ሙስና የሀገርን ኢኮኖሚ ከማዳከሙ ባለፈ የዜጎችን ተስፋ የሚያጨልም የዘመናችን ድንበር ዘለል ወንጀል ነው፡፡ይህንን ተረድተን እንደልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍል ለ2018 በጀት ዓመት ያቀደውን ዕቅድ በተለይም በመጀመሪያው ስድስት ወራት ሙሉ በሙሉ በማሳካት አበረታች ውጤቶችን አስመዝግበናል፡፡

ተልዕኳችን በሁለት ዋና ዋና ምሰሶዎች ላይ የቆመ ነው፡- አንደኛው የትውልድ የሥነ ምግባር ግንባታ ስራነ ው፡-ይህ ትውልድን በስነ-ምግባር የመቅረጽ ሂደት ነው፡፡የመንግስት ሰራተኛውም ሆነ ህብረተሰቡ ሙስናን የሚጠየፍ፣ለህዝብ ጥቅም የሚቆም እና የታመነ ስብዕና እንዲኖረው ማስቻል ነው፡፡

ሁለተኛው የመከላከልና ህግ የማስከበር ስራ ሲሆን የመንግስት አሰራሮችግልጽነትናተጠያቂነትእንዲሰፍንባቸውበማድረግ፣የህዝብና የመንግስት ሀብት እንዳይባክን መታደግ እንዲሁም ሙስና ሲፈጸም ለህግ በማቅረብ ፍትህ እንዲሰፍን ማድረግ ነው። በአጠቃላይ በ2025 ሙስና ለከተማ አስተዳደሩ ልማት እና መልካም አስተዳደር እንቅፋት ከማይሆንበት ደረጃ ደርሶ ማየት ራዕያችን ነው።

**ልደታ ፋና፡-** በተቋሙ የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት ምን ምን ናቸው?

**ወ/ሮ እማዋይ፡-** በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ሙስናን ለመከላከል በተያዘው እቅድ የተሳካ እንዲሆን ነዋሪዎችን፣ ሰራተኞችን፣ አመራሮችን እንዲሆም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በማሳተፍ የግንዛቤ ስራዎችን መስራት ችለናል። በተሰራው የግንዛቤ ስራዎችም ሁሉም አካላት ራሳቸውን ከሙስና እንዲያርቁና ሙስና የሚሰሩ አካላት ሲመለከቱም የማጋለጥ ስራዎችን ለመስራት እንዲችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥረናል። ባለፉት 6 ወራት የተፈጠሩ የግንዛቤ ስራዎች በ3 አበይት ጉዳዮች የሚገለጹ ናቸው። ሰፊ የህዝብ ንቅናቄና ተፋትሮ የመጀመሪያው ክንውን ሲሆን የክፍለ ከተማው እና የወረዳ አመራሮች፣ ሠራተኞችና የክፍለ ከተማውን ነዋሪዎች እንዲሁም የፀጥታአካላትን በማሳተፍ የተከናወኑት ተግባራት ተቋማዊና ህዝባዊ መሰረታችንን ያጠናከሩ እንዲሆኑ ተደርጓል። ሙስናን ለመከላከል ከተሰሩ ስራዎች ውስጥ የፈጠራና የጥበብ አጠቃቀም ሁለተኛው ጉዳይ ሲሆን የኪነ ጥበብ ምሽትና የስፖርት ፕሮግራም በማካሄድ ክፍለ ከተማው ነዋሪዎች ስለ ሙስና አስከፊነት በመገንዘብ ችግሩን ለመከላከልና የመፍትሄ ሀሳቦችላ ለማመላከት የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል።

ሌላው የሀብት ምዝገባና የህግ ማስከበር ስራ በተመለከተ ከግንዛቤ ፈጠራው ጎን ለጎን የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ የሆኑ የመከላከል ስራዎችን ሰርተናል። የሚቀርቡ ጥቆማዎችን በማጣራት ምክረ ሃሣብ በመስጠት ተቋማት የማስተካከያ እርምጃና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲወስዱ የትግበራ ክትትልና ድጋፍ ስራ መስራት ተችሏል። በንቅናቄ መድረኩ በተለይም በመሬት አስተዳደር፣በቤቶች ልማት እና በፍትህ አካላት አካባቢ የሚስተዋሉ የሙስና ምንጮችን (ለምሳሌ፡- የመንግስት ቤቶችን ወደ ግል ማዞር፣ ህገ-ወጥ የመሬት አጥር፣ ወዘተ) ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን ለይተን የቀጣይ የትግል አቅጣጫ አስቀምጠናል።

**ልደታ ፋና፡-** የሙስና ተግባራትን ለመከላከል እየተሰሩ ያሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ምን ውጤት ተገኘ?

**ወ/ሮ እማዋይ፡-** ይህ በጣም ወሳኝ ጥያቄ ነው። በዘንድሮው ዓመት፣በተለይም የዓለም አቀፍ ፀረ-ሙስና ቀን ንቅናቄን ተከትሎ የተሰሩት የግንዛቤ ስራዎች ተጨባጭ ለውጥ እያሳዩ ነው። በቅርቡ በተካሄደው ንቅናቄ ብቻ ከ56,000 በላይ የህብረተሰብ ክፍሎች (ወጣቶች፣ ሴቶች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና ተማሪዎች) ተሳታፊ ሆነዋል። ይህ የሚያሳየው ህዝቡ "ሙስና ይብቃ" ብሎ ለመነሳት ያለውን ዝግጁነት ነው። ከዚህ ቀደም በዝምታ ይታለፉ የነበሩ ጉዳዮች አሁን ህዝቡ በድፍረት "ይሄ አሰራር ለምን ተበላሸ?፣ ይሄ መሬት ለምንታጠረ?፣ አገልግሎት ለማግኘት ለምን እንጉላለን?" ብሎ አመራሩን እስከ መጠየቅ ደርሷል። በተለይም ወጣቶች ሙስና የሀገር እድገት ካንሰር መሆኑን በመረዳት ትግሉን የራሳቸው አድርገው ወስደውታል። በግንዛቤ ስራው ምክንያት ህብረተሰቡ ጥቆማ ለመስጠት የነበረው ፍራቻ እየቀነሰ መጥቷል። አሁን ላይ ሰዎች የመልካም አስተዳደር ችግሮች ሲገጥሟቸው ዝም ከማለት ይልቅ ወደ ህግ እና ወደ እኛ ክፍል የመምጣት አዝማሚያ እያሳዩ ነው።

**ልደታ ፋና፡-** የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ተግባራትን በቀጣይ ውጤታማ ለማድረግ ምን ይጠበቃል?

**ወ/ሮ እማዋይ፡-** የጀመርነው ተልዕኮ አፈጻጸም ስኬት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ወሳኝ ናቸው። ሙስናን አንድ ተቋም ብቻውን የሚዋጋው አይደለም። አመራሩ፣ ባለሙያው፣ የፍትህ አካላት እና ህዝቡ በቅንጅት መስራት አለባቸው። በተለይም አመራሩ "እኔ ጸድቼ ተቋሜን ማፅዳት አለብኝ" በሚል ቁርጠኝነት ሊሰራ ይገባል። የሰው ለሰው ንክኪን የሚቀንሱ የቴክኖሎጂ አሰራሮችን በሁሉም ሴክተሮች ማስፋፋት ይጠበቅብናል።ተቋማት ግልጽ የአገልግሎት ስታንዳርድ ሊኖራቸው እና ያንን ተከትለው ሊሰሩ ይገባል። ህብረተሰቡ አገልግሎት በገንዘብ አልገዛም የማለት እና ወንጀልን የማጋለጥ ባህሉን አጠናክሮ መቀጠል አለበት።

**ልደታ ፋና፡-** የሚያስተላልፉት መልዕክት?

**ወ/ሮ እማዋይ፡-** በዚህ አጋጣሚ ለማስተላለፍ የምፈልገው በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ያሳየነውን ድንቅ አፈጻጸም በዓመቱ መጨረሻም ደግመን የልደታ ክፍለ ከተማን የፀረ-ሙስና ትግል ማዕከል ማድረግ አለብን።

**ልደታ ፋና፡-** ስለ ቃለ መጠይቁ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ እማዋይ ፡-** እኔም አመሰግናለሁ ።

# የዘርፈ ብዙ ተልዕኮ ባለቤት

የልደታ ክ/ከተማ የሴቶች፤ ህፃናት እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ራዕይ በ2018 ዓ.ም የሴቶች፤ የህጻናት፤ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን መብትና ደህንነት የተረጋገጠባት፤ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች የተስፋፉባት እና የስርዓተ-ፆታ እኩልነት የጎለበተባት ከተማ ሆና ማየት ነው፡፡

የሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን እና ሌሎች ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተስብ ክፍሎች ማህበራዊ ችግሮች በመከላከል፤ መብትና ደህንነት በማስከበር፤ድጋፍና ክብካቤ አገልግሎት በማስፋፋት የሴቶችን፣ የሕፃናትና አካል ጉዳተኞችን ጉዳይ አካትቶ ትግበራ በማረጋገጥ፣ ህብረተሰቡን በማሳተፍና ባለድርሻ አካላት ድጋፍ በማቀናጀት እና አደረጃጀቶችን በማጠናከር ተሳትፏቸውን በማጎልበት፣ በማብቃትና በማሸጋገር በህብረተሰቡ ዘንድ የተዛባ የስርዓተ-ፆታ አመለካከትን በመቀየር፤ በሁሉም መስክ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ልደታ ፋና መፅሔት በእነዚህና ሌሎች ጉዳዮች ከጽ/ቤቱ ሀላፊ ወ/ሮ ሔለን መሐመድ ጋር ቆይታ አድርጋለች፡፡ መልካም ንባብ!

**ልደታ ፋና፡-** በቅድሚያ ይህን ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ፈቃደኛ ስለሆኑ በመፅሔት ዝግጅት ክፍሉ ስም እናመሰግናለን፡፡
**ወ/ሮ ሔለን፡-** እኔም ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በክ/ከተማው የሴቶች ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ከማድረግ የተሰሩ ስራዎችን ቢገልፁልን?
**ወ/ሮ ሔለን፡-** በስርዓተ ፆታ የተዛባ አመለካከት ሳቢያ ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የማየት ልማድና ባህል እንዲወገድ እስከ ወረዳ ባለው መዋቅር በህብረተሰቡ ላይ ሰፊ የአመለካከከት ቀረፃ ስራ የሚሰራ ሲሆን፤ ሴቶች እራሳቸው መብትና ደህንነታቸውን በማስከበር ጥቃትን እንዲከላከሉ ለማድረግ አለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ድንጋጌዎችንና የፖሊሲ ማእቀፎች እንዲያውቁ ግንዛቤ እየተፈጠረ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከከተማ እና ከኩዊንስ ኮሌጆች ጋር በመነጋገር ሴቶች የከፍተኛ የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ 8 በማስተር እና 15 ደግሞ በዲግሪ ፕሮግራም እንዲማሩ ለሚመለከተው አካል ልከናል፡፡ ከተግባረዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመነጋግር 30 ሴቶች በተለያየ የሙያ ዘርፍ ላይ የ6 ወር ስልጠና እንዲወስዱ ልከናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በተያያዘ ሴቶችን ከጥቃት ከመከላከል አኳያ ምን ተሰርቷል?
**ወ/ሮ ሔለን፡-** በክ/ከተማና በ10ሩ ወረዳዎች ከመንግስት ጽ/ቤቶች፣ ከሲቪክ ማህበራት እና ከሐይማኖት ተቋማት የተውጣጡ በሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ ሰብሳቢነት የሚመራ 14 አባላትን ያቀፈ የፀረ-ፆታዊ ጥቃትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት አስወጋጅ ግብረ ሀይል በማቋቋም በክ/ከተማው በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን የማጋለጥ ተከታትሎ ለህግ ከማቅረብ በተጨማሪ በሀይማኖት ተቋማት፣ በእድር ስብሰባ፣ በለቅሶና ሰደቃ በታዎች ግንዛቤ በመፍጠር የጥቃትን ቅድመ መከላከል ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡



## ወ/ሮ ሄለን መሀመድ
## የሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም እንደ ክ/ከተማ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?
**ወ/ሮ ሔለን፡-** በሀገራችን ህግ መሰረት ህጻናት ተብለዉ የሚጠሩት እድሜያቸዉ ከ18 ዓመት በታች የሆኑት ሰዎች በአጠቃላይ ህጻናት ተብለዉ ይጠራሉ፡፡ ሀገራችን በዓለም ዓቀፍ ስምምነት ሰነድ፣ በአፍሪካ ቻርተር እና በሀገራችን ህገ-መንግስት መሰረት ለህጻናት ሊከበርላቸዉ የሚገቡ የህጻናት መብት በመርህ ደረጃ የተቀመጡ 4 ናቸዉ፡፡ እነሱም፡- ህጻናት የመኖርና የማደግ መብት አላቸዉ፤ ህጻናት ላይ መድሎና ማግለል ሊደርስባቸዉ አይገባም፤ ለህጻናት ጥቅም ቅድምያ መስጠት እና የህጻናት ተሳትፎ ማረጋገጥ ናቸው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የህፃናት መብቶች እንዲረጋገጡ ጽ/ቤቱ ምን አከናውኗል?
**ወ/ሮ ሔለን፡-** በክ/ከተማው በህጻናት መብት ዙሪያ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ድጋፍን በተመለከተ በሚኒስቴር መስሪያ ቤት፣ በመንግስት ሰራተኛ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ድጋፍ እየተደረገላቸዉ ያሉ ህጻናት 398 ሲሆኑ በቀጥታ ድጋፍ በየወሩ 520 ብር ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የማህበራዊ ጉዳዮች ተግባሮቻችሁ አፈፃፀም ምን ይመስላል?
**ወ/ሮ ሔለን፡-** በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ 2170 የህብረተሰብ ክፍሎችን በምገባ ማዕከላት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የልየታ፣ ኩፖን ስርጭትና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙና የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ዉስጥ መስራት የሚችሉትን መለየትና የተለያየ ድጋፍ በማድረግ እንዲቋቋሙ የማድረግ ሰራ ተሰርቷል፡፡ በክ/ከተማችን የሚገኙ 7 አካል ጉዳተኞች የሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍና የአካል ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የማህበራዊ ችግራቸው መቅረፍ የተቻለ ሲሆን ህፃናት አካል ጉዳተኞች ወደ ት/ቤት እንዲሄዱ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም አዋቂ አካል ጉዳተኞች ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፡፡

በተጨማሪም ለ22 ቤተሰቦች በቤተሰብ ፍቺ ጉዳይ የማስታረቅ፣ የህግ ድጋፍ፣ የምክር አገልግሎት የስነ-ልቦና ድጋፍ በመስጠት ጋብቻንና ቤተሰብን የማጠናከለር ፍቺን የመከላከል ስራ ተከናውኖዋል።

**ልደታ ፋና፡-** ስለነበረን ቆይታ በድጋሚ እናመሰግናለን።
**ወ/ሮ ሔለን፡-** እኔም በድጋሚ ለዚህቃለ መጠይቅ ስለጋበዛችሁኝ በጽ/ቤቱ ስም አመሰግናለሁ።

## ጤናው የተጠበቀ ትውልድ

መንግስት በቁልፍ ተግባር ከያዛቸው ጉዳዮች አንዱ ወጣቶች ያለባቸውን የስራ አጥነት ችግር መቅረፍ ሲሆን ይህንን ተግባር ለማሳካት በጥቃቅንና አነስተኛ የዕድገት ተኮር የስራ ዘርፎችና በክፍለ ከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ ተቋማት በየደረጃው በሚፈጠሩ የስራ ዕድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም የተለያዩ የድጋፍ ማዕቀፎችን በማዘጋጀትና በመተግበር የወጣቶች ቀጥተኛ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።በመሆኑም በልደታ ክፍለ ከተማ ወጣቶችን ስፖርት ጽ/ቤት የተሰሩ ስራዎችን ወደ እናንተ ለማቅረብ ከጽ/ቤቱ ኃላፊ ጋር ቆይታ አድርገናል ተከታተሉን ።

**ልደታ ፋና፡-** በመጀመርያ ለቃለ-ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆንክ እያመሰገንኩ ራስህን አስተዋውቅልን
**አቶ አንተነህ፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጠየቃችሁኝ እያመሰገንኩ አንተነህ በፍቃዱ እባላለሁ የልደታ ክፍለ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ኃላፊ ነኝ።

**ልደታ ፋና፡-** ወጣቶችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የተሰሩ የግንዛቤ ስራዎች
**አቶ አንተነህ፡-** ጽ/ቤቱ ከተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት በመነሳት ስራ ፈላጊ ለሆኑ ወጣቶች በመንግስት የድጋፍ ማዕቀፍ ወጣቶች በልዩ ሁኔታ ስልጠና እና የመስሪያ ቦታዎች እንዲያገኙ፣ በመደበኛ ብድርና ቁጠባ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ የነጻና ግማሽ ክፍያ የትምህርት እድል እንዲመቻችላቸው ስራዎችን መስራት ተችሏል። በወጣቶች በመንግስት የድጋፍ ማዕቀፍ ዙሪያ ግልፅ የሆነ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ተችሏል። በዚህም ጥሩ ውጤት በመምጣቱ የስራ ፈላጊዎች ቁጥር መቀነስ፣ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ወጣቶችም የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ሀገራችንን ከውጭ ምንዛሪ የሚያድኑ፤ለሌሎችም ዜጎች የስራ እድል የፈጠሩ፤ግብር በአግባቡ የሚከፍሉ ወጣቶች እንዲፈጠሩ ፤የስራ ባህል እንዲቀየር እና በክፍለ ከተማው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ተደርጓል።

ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀትና ግንዛቤ በመፍጠር ወጣቶች የቁጠባ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በተሰራ ቅንጅታዊ ስራ የወጣቶች የቁጠባ ተሳትፎ ማሳደግ ተችሏል። በዚህም የስራ ዕድል ለተፈጠረላቸው ወጣቶች በቁጠባ አገልግሎት ላይ በስፋት እንዲሳተፉ፤ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በብድር አወሳሰድና አመላለስ ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ግንዛቤ በመፍጠር ሲሆን በተሰራው ተከታታይ የአመለካከት ቀርጻ ተግባር ወጣቶች ቁጠባን ባህል አድርገ ከሌላ ወገን በሚገኝ የገንዘብ ምንጭ ሳይሆን በተቆጠበ የራስ ገንዘብ ህይወትን መቀየር ፣ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብሎ የሚያምኑ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ መስራት ተችሏል።



## አቶ አንተነህ በፍቃዱ
## የወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ኃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** ጤናው የተጠበቀ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ከመፍጠር አንፃር የተሰሩ ስራዎች

**አቶ አንተነህ፡-** ለስፖርት ልማት ዋነኛና አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ዉስጥ የመጀመሪያዉ በቂ የስፖርት ማዘዉተሪያ ስፍራዎችን መገንባት ነው። ስለዚህም የህብረተሰቡንና የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ በማሳደግ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በመገንባት በአግባቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ስራ ተሰርቷል። እነዚህ ማዘወተሪያ ስፍራዎችም በክፍለ ከተማ ደረጃ ሁሉንም ዜጎች በአካል እና በአእምሮ ጎልብተዉ ጤናማ እና አምራች እንዲሆኑ በማህበረሰብ አቀፍ ስፖርት እንዲሳተፉ የስፖርት ስልጠናዎችና ውድድሮች በአግባቡ እንዲካሄዱ በማድረግ ለስፖርት መስፋፋት ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ነው።

ለስፖርት ባለሙያዎች በስፖርት ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም በዳኝነት፤ በአሰልጣኝነት እና በኢንስተራክተርነት ስልጠና መስጠት ተችሏል። እነዚህ ሰልጣኞች በተለያዩ ስፖርት አይነቶች በክፍለ ከተማ ደረጃ በሚሰጡ የስፖርት ስልጠናዎችና ውድድሮችን በብቃት በመምራትና በማሰልጠን ስፖርት እንዲስፋፋ ከፍተኛ ስራዎችን የሰራን ሲሆን የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ስልጠና ፕሮግራም በ19 የስፖርት አይነቶች ታዳጊ ወጣቶች በግለሰብ ማበልጸጊያ ማዕከላት፤ በክለብ መዋቅሮች፤ በመንግስት ማበልፀጊያ ማዕከላትና በመንግስት ድጋፍ በተዘረጉ ፕሮግራሞች ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር ስራ ተሰርቷል።በዚህም የተገኘ ውጤት ተተኪ ስፖርተኞች በማፍራት በከተማ አቀፍ የውድድር መድረኮችም የወርቅ፤የብርና የነሃስ መዳሊያዎችን በማግኘት የስፖርተኞችን ተሳታፊነትና ተወዳዳሪነት ማሳድግ ተችሏል።

የኤሊት ስፖርተኞችን በየስፖርት ዓይነቱ ለማፍራት ታቅዶ በየደረጃው በተካሄዱ ወድድሮችና ስልጠናዎች 32 ኤሊት ስፖርተኞችን ማፍራት ተችሏል። በየስፖርት ዓይነቱ በተሰጥኦቸውና በችሎታቸው የተመረጡ ኤሊት ስፖርተኞችን ወደ አካዳሚ፤ ክለብ እና ብሐራዊ ቡድን እንዲገቡ በማድረግ ኤሊት ስፖርተኞችን ማፍራት ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-**ማህበረሰቡ ስፖርትን ባህሉ እንዲያደርግ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች

**አቶ አንተነህ፡-** ሁሉንም ዜጎች በአካል እና በአእምሮ ጎልብተዉ ጤናማ እና አምራች እንዲሆኑ በሚኖሩበት ፣ በሚማሩበት ፣ በሚሠሩበት እና በሚዝናኑበት በማህበረሰብ አቀፍ ስፖርት እንዲሳተፉ ማድረግ ተችሏል። ከዚህ አኳያ የተገኘ ውጤትም ዜጎችን በአካላዊ እንቅስቃሴ ውስንነት ከሚከሰቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ራሳቸውን እንዲጠብቁ እና እንዲከላከሉ በተለይም ደግሞ ወጣቶች ትርፍ ጊዜያቸውን በስፖርት እንዲያሳልፉ፤ ራሳቸውን ከሱስ እና ከጎጂ ድርጊቶች እንዲቆጠቡ ማድረግ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻ የምታስተላልፈው መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥህ

**አቶ አንተነህ፡-** ባለፉት አምስት አመታት ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ ለወጣቱ የስፖርት የማዘወተሪያ ስፍራን በመገንባት ጤናውን የጠበቀ ትውልድ ከመፍጠር አንጻር አመርቂ ስራ እንደ ሃገር እና እንደ ክፍለ ከተማም ጭምር የተሰራበትና በከፍተኛ ደረጃ እምርታ የታየበት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።በመሆኑም በ2018 ዓ.ም የልደታ ክፍለ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት በመጀመሪያ 6 ወር የተካሄዱት ተግባራት እና የተገኙ ውጤቶች በወጣቶች የስፖርት ተሳትፎ እንቅስቃሴ፡ የማህበረሰብ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት ላይ ጉልህ ተጽዕኖ ያደረጉ ሲሆን በቀጣይም የተሻለ ውጤት ለማምጣት በትጋት እንሰራለን።

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን

**አቶ አንተነህ፡-** እኔም በጽ/ቤቱ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።

# ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም

የልደታ ክ/ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት የክ/ከተማውን ሀብቶችን መምራት፤ ጥንቃቄ የተሞላበት ድልድል፤ ህጋዊ የግዢ ስርዓት እንዲኖር እና አጠቃቀምን በማረጋገጥ የነዋሪዎችን የተለያዩ ፍላጎቶች ማሟላት ተልዕኮ አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በፋይናንስ አስተዳደር አሰራር ውስጥ ግልፀኝነት፤ ተጠያቂነት እና ቅልጥፍናን ለማስፋፋት ቁርጠኛ የሆነ ተቋም ነው። በዚህም ለክ/ከተማችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እንዲሁም ደህንነት የበኩሉን አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል። ልደታ ፋና መፅሔትም በእነዚህና ሌሎች የጽ/ቤቱ የስራ እንቅስቃሴ ላይ ከጽ/ቤቱ ሀላፊ አቶ ተኽላይ አፅብሃ ጋር ቆይታ አድርጋለች። መልካም ንባብ።

**ልደታ ፋና፡-** በቅድሚያ ይህን ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ፈቃደኛ ስለሆኑ በመፅሔት ዝግጅት ክፍሉ ስም እናመሰግናለን።
**አቶ ተኽላይ፡-** እኔም ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።

**ልደታ ፋና፡-** የመንግስት በጀት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የጽ/ቤታችሁ ሚና ምንድን ነው?
**አቶ ተኽላይ፡-** የከተማ አስተዳደሩ ለክ/ከተማው የመደበውን መደበኛ እና የካፒታል በጀት ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ከክ/ከተማ እስከ ወረዳ የመደልደል ሥራ ማከናወን እንዲሁም ሴክተር ተቋማት የራሳቸውን በጀት እንዲያስተዳደሩ ተደርጓል። በሴክተር ተቋማት የበጀት አጠቃቀማቸውን በቅርበት ክትትልና ድጋፍ በማካሄድ፤ የካፒታል ፕሮጀክቶች በጀት ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን በቅርበት ክትትል በማድረግ፤ የፋይናንስ ወጪ መመሪያን ተከትለው ስለመከፈላቸው ትክክለኛነት በኦዲት በማረጋገጥ፤ ለአመራሩ እና ለባለሙያዎች በበጀት አዘገጃጀት እና አጠቃቀም ላይ የአቅም ግንባታ ግንዛቤ በመፍጠር የመንግስትን በጀት ለታለመለት አላማ እንዲውል አስችለናል።



**አቶ ተኽላይ አፅብሃ**
**የፋይናንስ ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** የባለፈው በጀት ዓመት የኦዲት ግኝት ሪፖርታችሁ ምን ያመለክታል?
**አቶ ተኽላይ፡-** የሌብነት እና ብልሹ አሰራር ታግሎ በማስተካከል ዙሪያ በተለይ የኦዲት ምርመራ ተደርጎባቸው የተገኙ ግኝቶች / የአሰራር ችግሮችን/ 1,226.022.16 ብር ሙሉ በሙሉ ገንዘቡን ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ማድረግ ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** እንደ ክ/ከተማ የግዥ ስርዓቱ መመሪያን ከማስጠበቅ አኳያ ምን ይመስላል?
**አቶ ተኽላይ፡-** 48 ሴክተር ተቋማት የ2018 በጀት ዓመት የግዥ ፍላጎት በማሰባሰብ እቅዱን በማጠቃለል በጽ/ቤት ኃላፊ ጸድቆ ለከተማው ፋይናንስ ቢሮ ተደራሽ ተደርጓል። የግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ አፈጻጸም ከፍ እንዲል ለአመራሩ እና ለባለሙያዎች፤ ለጨረታ ኮሚቴ፤ ለቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በግዥ አዋጅና መመሪያ ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ችለናል። ከክ/ከተማ እስከ ወረዳ ባለው ግዥ ፈጻሚ ሴክተር ተቋማት ወቅቱን የጠበቀ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ማድረግ ተችሏል። ሴክተር ተቋማት የሚፈጽሙት ግዥ በአመት አንድ ጊዜ አጠቃለው ቢገዙ ከሚገዛው እቃ ጥራት፤ ዋጋ እና ሌሎችም ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ግንዛቤ ተፈጥሯል። ሴክተር ተቋማት በሚፈጽሙት ግዥ አዋጅና መመሪያውን ጠብቆ ስለመከናወኑ የግዥ ኦዲት በመስራት የማረጋገጥ ሥራ ተግባራዊ ተደርጓል።

**ልደታ ፋና፡-** በዚህ በጀት ዓመት በልዩ ትኩረት ለመስራት የያዛችሁት ግብ ምንድን ነው?
**አቶ ተኽላይ፡-** በዚህ በጀት አመት የሀብት አመዳደብ እና አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሻሻል፤ ከማዘጋጃ ቤታዊ በተለያዩ የገቢ ርዕሶች ገቢ መሰብሰብ፤ የማህበራዊ ኃላፊነታቸውን የተወጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ማሳደግ፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፕሮጀክት ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ፤ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል፤ ተቋማት ወርሃዊ ሂሳባቸውን በየወሩ መዝጋታቸውን ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ፤ ጥራቱን የጠበቀ የኦዲት ሪፖርት ማድረግ፤ ከሚፈጸሙ የመንግስት ግዥዎች የግልፅ ጨረታ ድርሻ ማሳደግ ዋነኛ የበጀት አመቱ ግቦቻችን ናቸው።

**ልደታ ፋና፡-** ስለነበረን ቆይታ በድጋሚ እናመሰግናለን።
**አቶ ተኽላይ፡-** እኔም በድጋሚ ለዚህቃለ መጠይቅ ስለጋበዛችሁኝ በጽ/ቤቱ ስም አመሰግናለሁ።

# ውብ አዲስ አበባን የመፍጠር ጉዞ

የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት ራዕይ በ2022 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ በውበቷ በአረንጓዴነቷ፤ ለነዋሪዎቿና ለእንግዶቿ ማራኪና ተመራጭ የአፍሪካ ከተማ ሆና ማየት ነው፡፡ በኅብረተሰቡና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የህዝብ መናፈሻዎችን፤አረንጓዴ ቦታዎችን ልማት ማስፋፋት፤ የዘላቂ ማረፊያና የህዝብ መፀዳጃ ቤቶችን ልማትና አገልግሎት አሰጣጥን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ በማድረግ የከተማውን ውበት ማረጋገጥ ደግሞ ዋነኛ ተልዕኮው እንደሆነ ከተቋሙ ያገኘነው መረጃ ያሳያል፡፡ የከተማ ውበትን አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል የአረንጓዴ ቦታዎችን ማልማት፤ የአረንጓዴ ቦታዎችን መንከባከብ፤ የውበት ስራዎች መስራት እና የኮሪደር ልማት ስራዎች መከታተል ዋነኛ ተግባሩ ናቸው፡ ፡

በአረንጓዴ ቦታዎች ልማት የአረንጓዴ አሻራ ስራ 2017/18 አመት የችግኝ ተከላ ስራ በተመለከተ 192 ሺ በላይ ችግኞችን የተተከለ ሲሆን የተተከሉትን ችግኞች የፅድቀት መጠን ስናየው 83% የተተከሉ ችግኞች ፀድቀዋል ቀሪ 17% የጠፋ ናቸው፡፡ በሁሉም ወረዳ 20/50 ሜ/ራዲየስ የሚገኙ ቁርጥራጭ ቦታዎች 3,337 ካሬ ቁርጥራጭ ቦታዎችን በህብረተሰብ ተሳትፎ ማልማት ተችሏል፡፡ የወንዝ ዳርቻ ልማት በተመለከተ የማልማት እና 3 ኪ.ሜ ወንዝ የማጽዳት ስራ ተሰርቷል፡፡ በአጠቃላይ በልማት ዘርፉ፣ በአረንጓዴ አሻራ እና ወንዝ ጽዳት ስራ የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራዎች ወደ ገንዘብ ሲቀየር በብር 48,083,009 ብር ተሳትፎ ማድረግ ተችሏል፡፡ የህፃናት መጫወቻ በተመለከተ በየወረዳው በሚገኙ ብሎኮች ለማሳራት በእቅድ ተይዞ በያዝነው በጀት አመት 16 ቦታዎችን ለይተን እስካሁን ድረስ በመንግስትና በህብረተሰቡ በጋራ 16 የልጆች መጫዎቻዎችን በማሰራት ለተገልጋይ ክፍት ማድረግ ተችሏል፡፡



**ወ/ሮ ትዕግስት ዋለልኝ**
**የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት ሀላፊ**

የውበት ስራዎች በተመለከተ አጠቃላይ በክፍለ ከተማችን ውስጥ በኮሪደር ልማት በተሰሩት እና ባልደረሰባቸው አከባቢዎች በዋና ዋና መንገድ፣ በባቡር እና በእግረኛ መሸጋገሪያ ድልድይ የስዕል ስራዎችን በተመረጡ ቦታዎች ውበትን የሚጨምሩ፣ የሰዎችን እንቅስቃሴ የማይረብሹ የመንገድ ላይ ወንበሮች በከተማዋ በሚገኙ ዋና ዋና መንገድ ፣ህንፃወች እና ዛፎች ላይ ስፖት ላይት መብራቶች ለማስዋብ ማከናወን ተችሏል፤ያረጁ፤ የወየቡ ህገ ወጥ ማስታወቂያዎችና የከተማ ውበት የሚያበላሹ ሸራዎች በመለየት፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲስተካከሉና ቅርንጫፋቸውን እይታን የሚጋርዱ እንዲወገዱ ማድረግ ተችሏል፡፡

የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት ዋና አላማው ከተማችን አዲስ አበባ እንደ ስሟ አበባ የሆነች ሳቢ እና ማራኪ ደረጃውን የጠበቀች ከተማ እንዲሁም ለቱሪስት ምቹ  ማድረግ ነው፡፡ ክ/ከተማችን በ2ቱም ዙር የኮሪደር ልማቱ ተጠቃሚ ከሆኑ ክ/ከተሞች አንዷ ስትሆን መንገድ አካፋዩች፣ ዳርቻዎችን የአረንጓዴ ልማት ስራዎች፣ ከሳርቤት እስከ ካርል ደሳለኝ፣ ከጀጋማ ኬሎ ጤና ጣቢጣ እስከ አቦ አደባባይ፣ ከሳርቤት እስከ አረቂ ፋብሪካ ድረስ በቂ የመኪና እና የእግረኛ መንገድ፣ ብስክሌትና ሌሎች የመዝናኛና የእግር ጉዞ፣ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ በመንገድ አካፋይና ዳርቻዎች የአረንጓዴ አካባቢዎች፣ ክፍት መናፈሻዎችንና የንጽህና ቤቶችን ጠቅላላ  የለሙ መንገድ አካፋዮችና ዳርቻ በአልሚዎች እና በመንግስት 29,605.82 ካሬ እንዲለማ ተደርጓል፡፡ ፕላዛ ከማልማት አንፃር ሳር ቤት 1 ፕላዛ፣ አቦ አካባቢ ያሉ 2 ፕላዛዎች እና ሰንጋተራ አዲስ ሲኒማ ኮምፕሌክስ መዝናኛ በጥቅሉ 15,872.36 ካ.ሜ የማልማት ስራ ተሰርቷል፡፡

# ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ለህብረተሰባችን

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት ባወጣው አዋጅ ቁምር 84/2016 መሰረት ስራ አሰኪያጅ ጽ/ቤት የተለያዩ ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ማለትም የጽዳት አስተዳደር ጽ/ቤት፣ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ጽ/ቤት፣ የእሳትና አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን እንዲሁም የኤሌክትሪክ አልግሎት ተቋማትን የሚመራ፣ የሚቆጣጠር፣ የሚያስተባብርና የሚደግፍ አስፈጻሚ ተቋም ነው፡፡ የህዝብ እድገት እና የአገልግሎት ፍላጐት ሊመጥን የሚችል ዘመናዊ፤ ቀልጣፋና ውጤታማ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ለተገልጋዩ በማቅረብ የህብረተሰቡን እርካታ ለማሳደግ ከተቋማት ጋር ውጤታማ ቅንጅታዊ አሰራር የመፍጠር፣ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርድ ተግባራዊ መሆናቸውን የመከታተልና የመደገፍ፣ ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና የመስጠት፣ ክፍለ ከተማችንን ጽዱ፣ ውብና ማራኪ የመኖሪያና የስራ አካባቢ የማድረግ፣ ቀልጣፋና በቴክኖሎጂ የታገዘ የኩነትና የነዋሪነት አገልግሎት እንዲሰጥ የማድረግ በተጨማሪም የእሳትና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች እንዳይከሰቱ ቅድሚያ የመከላከል እንዲሁም አደጋዎች ሲከሰቱ የጉዳት መጠን የመቀነስ ስራዎችን እየተገበሩ ይገኛሉ፡፡

በመሆኑም የልደታ ክፍለ ከተማ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የሚያከናውናቸውን ተግባራት በተመለከተ ማብራርያ እንዲሰጡን የዝግጅት ክፍላችን ከጽ/ቤቱ ኃላፊ ጋር ቆይታ አድርጓል ተከታተሉን ፡፡



## አቶ ያየህ ከተማ
## የስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** በመጀመርያ ለቃለ- ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጀት ክፍላችን ስም ከልብ እያመሰገንኩ ስሞትን ያስተዋውቁልን

**አቶ ያየህ፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጠራችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ ያየህ አለም እባላለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ጽ/ቤቱ የሚያከናውናቸው ተግባራትን ቢገልጹልን

**አቶ ያየህ፡-** የከተማው ስራ አስኪያጅ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 84/2016 መሰረት ተጠሪነቱ ለከተማው ከንቲባ ሆኖ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈጻሚ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጁ መሰረት የሚተሉት ስልጣን፣ ኃላፊትና ተግባር ይኖሩታል፡፡ ተጠሪነታቸው ለስራ አስኪያጅ የሆኑ አስፈጻሚ አካላትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤የተቋሙ ተጠሪ የሆኑ አስፈጻሚ አካላት እንዲቋቋሙ ወይም ሌሎች የአገልግሎት መስጫ አማራጮች በስራ ላይ እንዲውሉ ለከንቲባው ሃሳብ ያቀርባል፤ ከተማ አቀፍ እና ክፍለ ከተማ ዘለል የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎትን በተመለተ ዕቅድና በጀት ለከንቲባ ጽ/ቤት ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዋ ያደርጋል፤የአገልግሎት አቅርቦት መለኪያዎች እና መመሪያዎች በማጠናቀር ለከንቲባው ያቀርባል ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤ስሉጥ፣ ግልጽና ፍትሃዊ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት መስጠቱን ያረጋግጣል፤ የማዘጋጃቤታዊ አልግሎትን የሚመለከት የፖሊስ ሃሳብ እና የህግ ረቂቅ በማመንጨት ለከንቲባ ጽ/ቤት ያቀርባል፤የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለከንቲባ ጽ/ቤት ያቀርባል፤ ለስራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከስልጣቱ በከፊል ለምክትል ስራ አስኪያጅ፣ የራሱ ተጠሪ ለሆነ ኃላፊ ወይም አስፈጻሚ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ በቻርተሩ የተሰጡትን ሌሎች ሥልጣንና ተግባራት እንዲሁም በከንቲባው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

**ልደታ ፋና፡-** በህብረተሰቡ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የተሰሩ ስራዎችን ይግለጹልኝ?

**አቶ ያየህ፡-** ከኤሌክትሪክ አገልግሎት አንጻር፡- 2ኪ.ሜ መቀየር ያለባቸው ያረጁ እና የረገቡ /ለአደጋ የተጋለጡ/የኤሌክትሪክ ገመድ መቀየር፣240 የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች መቀየር፣240 አዲስ ፖል መትከል የመቀየር፣2 የአዲስ ትራንስፎርመር የመትከል፣2 የተቃጠለ /የተበላሸ/ ትራንስፎርመር ጥገና ማድረግ ፣110 አዲስ ቆጠሪ ጥያቄ የማስገባት፣2 በተደጋጋሚ መብራት የሚጠፋባቸው ቦታዎች የማስተካከል፣1የሃይል ጭማሪ የማስተካከል፣120 የመስመር ብልሽት ጥገና፣1የትራንስፎርመርና የቆጣሪ ማንሳት ስራ፣1 የትራንስፎርመር እና ቆጣሪ ቦታ ማዘዋወር ስራ፣2 የወደቀ ፖል ማስተካከል፣1 የሃይል ማነስ ያለባቸው ቦታዎች የማስተካከል ስራ ተሰርቷል

**ልደታ ፋና፡-** በህብረተሰቡ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በአግባቡ ከመፍታት አንጻር እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ምን ይመስላሉ?

**አቶ ያየህ፡-** ከእሳት አደጋ ስጋት አንፃር የተሰሩ ስራዎች ለጐርፍ ተጋላጭ ቦታዎች ለሁለቱም ቦታዎች ላሉበት ወረዳ አስተዳደር የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው፤11 ለእሳት አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎች እና ተቋማት በመለየት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፤የቅድመ አደጋ መከላከል ስራዎች ለ1365 አባላት በአደጋ ስጋት ቅነሳ በአደጋ እና በድህረ አደጋ አገልግሎት ተሰጥቷል፤7 የደረሰ አደጋዎች ሳይስፋፋ መቆጣጠር ተችሏል፤2 ቦታዎች ለአገልግሎት ተቆፍረው በተተው ጉድጓዶች ለይቶ ምላስ በመስጠት ለሁለቱም ቦታዎች ላሉበት ወረዳ አስተዳደር የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፤ተረጅነት እና ድህነት ቅነሳ ላይ ቅድመ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል በተለይም ምግብ ነክ ምግብ ነክ ያልሆኑ መገልገያ እቃዎችንና የንጽና መጠበቂያን ከየወረዳው በማሰባሰብ ወደ መጋዘን በማስገባት በዚህ ወር ብቻ ግምታቸው ከ200,000.00 (ከሁለት መቶ ሺህ) ብር በላይ የሆነ ተሰብስቧል፡፡

ከውሃና ፍሳሽ አንፃር፡- 9 ኪ.ሜ የውሃ መስመር ዝርጋታ ማዘጋጀት ተችሏል፣በእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአይን የሚታይ የውሃ ብክነት ለመቀነስ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሆኑ የመለስተኛ መጋቢ መስመሮችን ጥገና ስራ ተሰርቷል፤62 ህጋዊ ሰነድ ለሚያቀርቡ አዲስ ደንበኞች የውሃ መስመር ቅጥያ በመፈጸም የውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤3 ጥያቂ ለሚያቀርቡ ነባር ደንበኞች የውሃ መስመር ማሻሻያ በመከናወን የአገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤120 ጥያቄ ለሚያቀርቡ ነባር ደንበኞች የውሃ መስመር ማዘዋወሪያ በመፈጸም የውሃ ተጠቃሚ ማድግ ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ
**አቶ ያየህ፡-** ተቋማችን በቅንጅታዊ አሰራር ከተጠሪ ተቋማት ጋር ሆኖ በማስከበር በተለይም ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶችን በማሳለጥ እየሰራ ይገኛል በአደጋ ቅነሳ እና ቅድመ መከላከል ጋር በተያያዘ ለጐርፍ ተጋላጭ የሆኑ በታዎች አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን ከቦታው በማንሳ እና አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል፤ከመብራት ጋር በተያያዘ ያረጁ ፖሎችን እና ገመዶችን ለመቀየር በተጨማሪም የመብራት እንዳይኖር በማስተባበር ከተቋሙ ጋር እየሰራ ይገኛል፤ ከተማችን ውብ እና ጽዱ ከማድረግ አኳያ ሞዴል ወረዳ እና ሞዴል ብሎክ ከመፍጠር ጋር ተያይዞ በመመዘኛ መስፈርት መሰረት እንዲለዩ ያደረግን ሲሆን ሞዴል ያልሆኑ ብሎኮችን ሞዴል ለማድረግ ነዋሪ ማህበረሰቡን በማሳተፍ በርብርብ ላይ እንገኛለን፤ ሲቪል ምዝገባ እና ነዋሪዎች አገልግሎት የመልካም አስተዳደር ችግሮቹን ለምቅረፍና ለመቆጣጠር ሁሉንም ነዋሪዎች በሲቪል ምዝገባ እና ነዋሪዎች አገልግሎት መታወቂያ እንዲያወጡ በብሎክ ጭምር እየተገበርን እንገኛለን፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራርያ ከልብ እናመሰግናለን ፡፡
**አቶ ያየህ ፡-** እኔም በጽ/በቱ ስም አጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፡፡

## ጥራቱን የጠበቀ ምግብና መድሃኒት....

ሀገራችን የጀመረችው የለውጥ ጉዞ ኢትዮጵያ እንደሀገር ከገባችበት ውስብስብ የፖለቲካ፣የማህበራዊ እና የኢኮኖሚ ቀውስ ተስፈንጥራ በመውጣት ወደ አስደናቂ ሁለንተናዊ ብልፅግና እየተሸጋገረች ነው፡ ፡ የሁላችን ከተማ የሆነችው አዲስ አበባ እንደስሟ አበባ የማድረግ እና የኢትዮጵያ የብሌፅግና ተምሳሌት የማድረጉ ስራም በአስደናቂ ሁኔታ በተጨባጭ ውጤት ታጅቦ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ከማህበራዊ ዘርፎች አንድ የሆነውን የጤና ዘርፍ በሽታን መከላከልና አክሞ ማዳንን ማዕከል ያደረገው የሀገራችን የጤና ፖሊሲ ሰፋፊ ለውጦችን በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፤ተደራሽነት ማስፋት ብቻ ሳይሆን ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት መስጠትንም ያለመ ነው፡፡ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ጠንካራ የቁጥጥር /regulatory/ ስርዓት መዘርጋት አስፈሊጊ ነው፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ብልም የልደታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተለያዩ የህ/ሰብ ክፍሎችና ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ የምግብ፣ጤና እና ጤና ነክ ምርቶች እና አገልግሎቶች ጥራት፣ደህንነት እና ፈዋሽነት ለማረጋገጥ የጤና ቁጥጥር ስራ በመስራት የህብረተሰቡን ጤና የማስጠበቅ ሀላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም የጤና መቆጣጠር ዙሪያ በርካታ ስራዎች እየተከናወኑ ሲሆን በተለይ ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ መድሃኒቶች ለህብረተሰቡ እንዲቀርብ እና ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ምግብና መጠጥ ለተጠቃሚው በጥራት ለማድረስ ቅ/ጽ/ቤቱ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በየተቋማቱ ጥብቅ ቁጥጥር እና ክትትል እያደረገ ይገኛል፡ ፡በዚህ መሰረትም በህብረተሰቡ የሚደርሰውን ከፍተኛ የጤና ጉዳት ሊያደርሱ የሚችል የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች ፣ ምግቦች እና መጠጦች ተከታትሎ በማስወገድ እና በመከልከል በርካታ ስራዎች እየተሰሩ የሚገኙ ሲሆን አሁንም የቁጥጥር ስራችንን በማጠናከር የህብረተሰቡን ጤና በማስጠበቅ እርካታው ከፍ ለማድረግ ተችሏል፡፡

የልደታ የምግብና መድኃኒት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብና መድኃኒት ባለስልጣን እንዴት እና መቼ ተመሰረተ የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን የተቋቋመበት ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 30/2004 (እንዱሁም የፌደራል ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን 661/2002) በተሰጠው ስልጣን እና ተግባር ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጠ የነበረ ሲሆን፣ እንደገና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 84/2016 ተሻሽል በተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መሰረት የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን በሚል የተቋቋመ መንግስታዊ ተቋም ነው፡፡ በፌደራል ደረጃ የወጣውን የምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 60/2006 መመሪያዎች ወቷል፡፡ በተጨማሪም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኃይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 121/2014 ወቷል፡፡ በመሆኑም መረጃዎችን ወደ እናንተ ለማድረስ የዝግጅት ክፍላችን ከልደታ ክፍለ ከተማ የምግብ እና መድሃኒት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** በመጀመርያ ራስዎትን ያስተዋውቁልን
**አቶ በላይነህ፡-** በላይነህ ገብሩ እባላለሁ የልደታ ክፍለ ከተማ የምግብ እና መድሃኒት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ነኝ።

**ልደታ ፋና፡-** የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ አደረጃጀት ምን ይመስላል
**አቶ በላይነህ፡-** የልደታ የምግብ እና የመዴሃኒት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አገልግሎቶችን በአራት ዳይሬክቶሬቶች በአራት ቡድን በሶስት ክላስተሮች ተደራጀቶ /regrouping/ ይገኛል፤ዳይሬክቶሬቶቹ መጠሪያዎች አደረጃጀት፡- የምግብና ጤና ነክ ተቋማት ብቃት ማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት አደረጃጀት፤የምግብና ጤና ነክ ተቋማት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት በስሩ የምግብ ተቋማት ቁጥጥር ቡድን የጤና ነክ ተቋማት ቁጥጥር ቡድን አደረጃጀት ሲሆን የጤና ተቋማትና ባለሙያዎች ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ደግሞ በስሩ የጤና ተቋምና ባለሙያዎች ቁጥጥር ቡድንና የመዴሃኒት ተቋማትና ባለሙያዎች ቁጥጥር ቡድን የመጨረሻው የጤና ተቋማትና ባለሙያዎች ብቃት ማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት ሲሆን ክሊስተሮች ክላስተር 01 (ወረዳ 01,02፣ 09 10) ክላስተር 02 (ወረዳ 03 ፤05 እና 07) ክላስተር 03 ( 04፣06፣ 08) ናቸው።

**ልደታ ፋና፡-**በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቢገልጹልኝ
**አቶ በላይነህ፡-** በተቋሙ 10 የሚሰጡ ዋና ዋና አገልግሎት ያሉን ሲሆን እነሱም፡-
ለምግብ እና ለጤና ነክ ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ መስጠትን በ62 ባለሙያዎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፤ ለጤና ባለሙያዎች ምዝገባ እና የድጋፍ ደብዳቤ መፃፍ፤የባህል መድኃኒት አዋቂዎች ምዝገባና ቁጥጥር ማካሄድ፤ጤና ተቋማትና ባለሙያዎች ላይ፤ለጤና እና ለመድኃኒት ተቋማት ፤ለምግብ ተቋማት እና ለጤና ነክ ተቋማት ቁጥጥር ማድረግ፤መረጃ ማደራጀትና የደንበኞች አገልግሎት መስጠት የህገ-ወጥ ምርት ዝውውር ላይ ቅኝት እና አሰሳ ማድረግ፤የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸውን፣የተበላሹና ህገ-ወጥ፣የምግብ፣ መድሃኒትና ጤና ነክ ምርቶችን በአግባቡ መወገዳቸውን ማረጋገጫ መስጠት ናቸው።

**ልደታ ፋና፡-** በተቋምት እየተደረገ ያለው ቁጥጥር ምን ይመስላል
**አቶ በላይነህ፡-** የምግብና ጤና-ነክ ተቋማት የኃይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ቁጥጥር የተደረገላቸው የምግብ አምራች እና የምግብ አገሌግልት ሰጪ ተቋማት

የኃይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ቁጥጥር የተደረገላቸው የምግብ መሸጫ ተቋማት ብዛት 346 ፣ የተመረመረ የምግብ ናሙና 5 ፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብዛት 98 ፣ ማከፋያና መሸጫ ተቋማት ብዛት 12 በጥቅል በ2018 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ስድስት ወራት ለ783 የምግብና ጤና-ነክ ተቋማት ቁጥጥር ለማዴረግ አቅደን ከእቅድ በላይ ለ845 ተቋማት ቁጥጥር በማድረግ መፈፀም ተችሏል፡ ፡ እንዲሁም የትንባሆ ቁጥጥር በተመለከተ 69 ትምባሆ መጠቀም/ማጨስ የተከለከለባቸው የሕዝብ መገልገያ ስፍራዎች ላይ ቁጥጥር ተደርዷል። የምግብ፣929 የጤና እና ጤና-ነክ ተቋማት ላይ የቁጥጥር ስራ መስራት ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-** በሚደረገው ቁጥጥር መሰረት እርምጃ የተወሰደባቸው አሉ
**አቶ በላይነህ፡-** አዎ አሉ ሲጋራ /ትንባሆ/ አደንዛዠ እፅ ሲያስጠቅሙ የተገኙ ተቋማት 12 ሲሆኑ እያንዳንዳቸው 5000 ብር የገንዘብ ቅጣትና የፅሁፍ /እሽጋ /ማስጠንቀቂያ እርምጃ ተወስዶባቸዋል።



## አቶ በላይነህ ገብሩ
## የልደታ ክ/ከተማ የምግብ እና መድሃኒት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** ከብቃት ማረጋገጥ ጋር ተያይዞ የተሰሩ ስራዎች ምን ይመስላል

**አቶ በላይነህ፡-** የብቃት ተግባር በተመለከተ ጤና ተቋማት የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ብቃታቸው የተረጋገጠ የጤና ተቋማት ብዛት 92፣ብቃታቸው የተረጋገጠ የመድኃኒት ችርቻሮ ተቋማት ብዛት 67፣በማስተር ፋሲሊቲ ምዝገባ መመዝገብን በተመለከተ 954 ምዝገባዎች ተደርጓል፡፡

ተገቢውን መስፈርት ያሟሉ ተቋማትን በተመለከተ የምግብና ጤና-ነክ ተቋማት ብቃታቸው የተረጋገጠ የምግብ አምራች ተቋማት 82 ፣ ብቃታቸው የተረጋገጠ የምግብ አከፋፋይ 8 ፣ ብቃታቸው የተረጋገጠ የምግብ መሸጫ/ችርቻሮ ተቋማት 148 ፣ የጤና ብቃት ማረጋገጫ የወሰደ የምግብ አገሌግልት ሰጪ ተቋማት ብዛት 384 ፣ ብቃታቸው የተረጋገጠ የጤና ነክ ምርት መሸጫና ማከፋፈያ ተቋማት 29 ነው፡ ፡ ብቃታቸው የተረጋገጠ የጤና ነክ አገሌግልት ሰጪ ተቋማት 167 ናቸው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለምን ያህል ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡

**አቶ በላይነህ ፡-** በጥቅሉ በ2018 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ስድስት ወራት ለ978 የምግብ፣ጤና እና ጤና-ነክ ተቋማት የጤና ብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅድ ለ988 ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በማደስና አዲስ መስጠት ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለጤና አደገኛ የሆኑ ምርቶችን ከማስወገድ አንፃር የተሰሩ ስራዎች ምን ይመስላል

**አቶ በላይነህ ፡-** የልደታ የምግብና መድኃኒት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቁጥጥር ወቅት የተገኙ እና ህብረተሰብ ጤና አደገኛ የሆኑ ተወገዱ ምርቶች ተ/ቁ እርምጃ የተወሰደበት ተቋማት ጥቅል የተሰደ እርምጃ አይነት ፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የማሸግ ዴምር በጤና እና መድሃኒት ተቋማቶች 5 0 5 ለምግብ ተቋም 32 4 36 ጤና ነክ ተቋም 14 2 16 የተወሰደ እርምጃ ድምር 51 6 57 ተ.ቁ የተወገደ አይነት መለኪያ ምርመራ በክብደት በኪ.ግ በአይነት ብዛት ግምታዊ ዋጋ/በገንዘብ መድሃኒት 920.6 ኪ.ግ 704 1,326,522.39 መጠቀሚያ ጊዜውን ያለፈባቸው መድኃኒቶች ፣ ምግብ በኪ.ግ 177.4 17500 የተበላሸ ምግብ ፣ መጠጥ በሊትር 317 23000 ዉሃ ለስሊሳ አምቦ ዉሃ ወዘተ ፣ጤና ነክ ምርት በኪግ/በሉትር 17 2550 የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት ፣ ቁሳቁስ በቁጥር 28 3500 ፣ ሲጋራ በፍሬ 2014 38726 ህገ-ወጥ ምርት ጠቅላላ ድምር ኪግ=1098 ሊትር=334 አይነት=732 በቁጥር/ብሬ=2014 3257.4 1,411,798.39 ብር ነው፡፡

**ልደታ ፋና ፡-** የልደታ የምግብና መድኃኒት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያጋጠሙ ችግሮች ካሉ ቢገልጹልኝ

**አቶ በላይ ነህ፡-** የምግብ ተቋማት ቀድመው ብቃት ማረጋገጫ ሳይወሰዱ ስራ መስራት፣የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የምግብና የመድኃኒቶች ይዞ መገኘት፣ያለሀኪም ትዕዛዝ መሸጥ የማይችሉ መድኃኒቶችን ያለማዘዣ ወረቀት መሸጥ፣ምንጫቸው ያልታወቀ/ ኢንቮይስ የሌላቸው መድኃኒት ይዞ መገኘት፣የሕንፃው ወይም የክፍሎች ግንባታ/premises በስታንዳርዱ መሰረት አለመሆን፣ተጠቃሚው ሕብረተሰብ ምርቶችን ሲገዛ ወይም ሲጠቀም የመጠቀሚያ ጊዜ አይቶ የመግዛት ባህለ አናሳ መሆኑ፣በህገወጥ የምግብ፣የጤና እና ጤና-ነክ ምርቶች ወይም አገልገሎት ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት መኖሩ ህብረተሰቡ መጠቆምና አጋልጦ መስጠት ላይ ክፍተት መኖሩ፣በምሽት ወቅት በባር፣በጭፈራ ቤቶች ላይ ሲጋራ/ትምባሆ/ አደንዛዥ ማጨስ ናቸው፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ችግሩን ለመፍታት የተወሰደ መፍትሔ ምን ነው

**አቶ በላይነህ፡-** በቁጥጥር ባለሙያዎች ፈልጎ ማግኘትና ብቃት እንዲወስዱ ተደርጓል፣ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆኑ የተበላሹ ምርቶችን በመሰብሰብ እንዲወገዱ ተደርጓል፣ጠንካራ የቁጥጥርና የእርምጃ ስርዓት መዘርጋት፣የተቋማት ባለቤቶችን በማወያየት እድሳት እንዲያደርጉ ዝቅተኛ የጤና መስፈርት እንዲያሟለ ተደርጓል፡ ፡ በተጨማሪም “እኔም ለጤናዬ ባለስልጣን ነኝ!” በሚል መሪ ቃል ነዋሪዎችን በየብሎኩ በጤና ቁጥጥር ፎረም በማደራጀት ግንዛቤ መፍጠርና የጤና ቁጥጥሩ ባለቤት እንዲሆን እንዲሁም ህገ-ወጦችን እንዲጠቁሙና እንዲያጋልጡ ተደርጓል፡፡ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆኑ የምሽት ቁጥጥር ተሰርቷል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን

**አቶ በላይነህ፡-** እኔም በጽ/ቤቱ ስም አመሰግናለሁ፡፡

# ይቻላል በተግባር

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ ከተጣለ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ልማት ወዳዱ የክ/ከተማችን መህበረሰብ ከህጻን እስከ አዛውንት ባደረጋችሁት ርብርብ የግድቡ ግንባታ ብዙ ፈተናዎችና ውስብስብ ችግሮች አልፎ ፕሮጀክቱ በድል ተጠናቋል።

መንግስት ታላቁ የኢትዮጲያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በመላ የኢትዮጲያ ህዝቦች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ተጠናቆ የሰላም ፣የኢኮኖሚና የብልጽግናችን ምንጭ ሆኖ ማየት የሚል ራእይ ሰንቆ ለግድቡ ግንባታ ድጋፍ የሚውል ሀብት የማሰባሰብ፣ የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችን የማስተባበርና የግድቡ ግንባታ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በማስመልከት የተለያዩ የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን የማሳለጥ ዋናዋና ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል።

በዚህ መሰረት እንደ ክ/ከተማችን ከመጋቢት 24/2003 ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ 14 ዓመታት የሀብት አሰባሰብ ዕቅድ በማቀድ በየአመቱ በአብዛኛው ዕቅዳችን ከ100% በማከናወን ለግድቡ ግንባታ የድጋፍ ሀብት በማሰባሰብ የበኩላችን አስተዋጽኦ ያደረግን ሲሆን የክ/ከተማችን ነዋሪ ማህበረሰብ፣የፋይናንስ ተቋማት፣ ባለሀብቶች፣ ዕድሮች፣ ሸማች ማህበራት እንዲሁም የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ለግድቡ መጠናቀቅ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ከልብ የመነጨ ምስጋና ከታላቅ አክብሮት ጋር ማመስገን እፈልጋለሁ።



## አቶ ኤፍሬም መገርሳ
## የህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሃላፊ

ከ86% በላይ ሃገራችን ለናይል ውሃ እያቀረበች 1□%ውሃ እንኳ ለወንዙ አስተዋጽኦ የማያበረክቱ ሃገራት ባለቤትነትን በመንፈግ ምንም በአባይ ውሃ መጠቀም እንደማንችል ከመግለጽ ባሻገር ስራውን ለማስተጓጎል በሃገር ውስጥ ጀሌዎቻቸውንና በአለም አቀፍ ደረጃ ደጋፊዎቻቸውን በማስተባበር አቅማቸው የቻለውን ሁሉ ቢያደርጉም የግድቡ ግንባታ ባለፉት አመታት ለአፍታም ሳይቆም እንሆ በጉጉትና በናፍቆት ሲጠበቅ የነበረው የኃይል ማመንጨት ተግባር መጀመሩና አጠቃላይ የግድቡ ግንባታ መጠናቀቁ የኢፌድሪ መንግስት ጳጉሜን 4/2017 ዓ.ም መግለጹ ይታወሳል።

ግድቡ የሃገራችን አለኝታና ከሃይል ማመንጨት ባሻገር ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ጠቀሜታዎች የሚሰጥ በመሆኑ ይቻላል ብለን እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን ብለንም ቃል በገባነው መሰረት በቃላችን መሰረት አጠናቀነዋል። የግድቡ መጠናቀቅ በርካታ የልማት ትሩፋቶችን ጥሎ ያለፈ፣ የይቻላል ስሜት በተግባር የታየበት፣ የአንድነትና የመተባበር መንፈስ የታየበት፣ የዲፕሎማሲ አቅማችን ተፈትሾ በአስተማማኝ ሁኔታ መክተን በድል የተሻገርንበት፣በራስ አቅም ማንኛውንም ዕምቅ ሀብታችን በመገንባት መጠቀም እንደምንችል የተማርንበት የለውጥ ትምህረትቤታችን ነው ብንል ማጋነን አይሆንም።

በመጨረሻ በአሁኑ ስዓት “አባይ ግንድ ይዞ ይዞራል ከሚለው ተረት ወጥተን የኤሌክትሪክ ኃይል ይዞ ይዞራል” ወደ ሚለው ተጨባጭ እውነታ ተሸጋግረናል። የህዳሴ ግድብ መጠናቀቅ የድል ብስራት የምርቃት ስነ-ስርዓትን ተከትሎ ይፋ የተደረጉትን የጉባ ፕሮጀክቶችን ልክ እንደ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ሁሉ ልምዳችንን በመጠቀም ከዳር እንድናደርስ ጥሪየን አስተላልፋለሁ።

# የወጣቶች ሚና ለሀገር ብልጽግና

ወጣቶች በሀገራት በሚተገበሩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ላይ ግንባር ቀደም ተሳታፊ በሚሆኑበት ወቅት ሀገሪቱ የጀመረችውን ዕድገት ወደፊት ለማስቀጠል የሚኖራቸው ሚና የጎላ ይሆናል። ይህን ከግምት በማስገባትም ዩኒቨርስቲዎች፣ኮሌጆችና የስልጠና ማዕከላት ለወጣቶች የስራ ዕድልን በማመቻቸት በአመለካከትና በክህሎት ብቁ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ስራዎች ተሰርተዋል።

ወጣቶችም በመንግስት የተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎችን ተጠቅመው ራሳቸውን ከአልባሌ ቦታዎች በመቆጠብ በሀገሪቱ የልማት ስራዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባል።

የልደታ ክፍለ ከተማ ወጣቶች ማህበር መንግስት የሰጠውን ኃላፊነት በመጠቀም ወጣቶች በተፈጠረላቸው ዕድሎች ላይ በመሳተፍ ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ እየሰራ ይገኛል።ይህን ከግምት በማስገባት የማህበሩን ሰብሳቢ ወጣት ቢኒያምን በ2018 በጀት ዓመት ባለፉት 6 ወራት ያከናወናቸውን ስራዎች በማስመልከት ቃለ መጠይቅ ሰርተን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**ልደታ ፋና፡-** በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ በመሆንዎ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን።
**ወጣት ቢኒያም፡-**እ ኔም ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ

**ልደታ ፋና፡-**ወጣቱን የስራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር የተሰሩ ስራዎችን ቢገልጹልን?
**ወጣት ቢኒያም፡-** ከተማችን በአሁኑ ወቅት በዓለም ካሉ ከተሞች ተፎካካሪና ሳቢ እንድትሆን የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡ ፡ በከተማዋ እየተከናወኑ የሚገኙ የልማት ስራዎች ወጣቶችን የስራ ዕድል ተጠቃሚ እያደረጉት ይገኛሉ። እየተሰሩ ካሉ ስራዎች ውስጥ የኮሪደር ልማት ተጠቃሽ ሲሆን በግሪነሪ እና በመጸዳጃ ቤት አገልግሎት በማደራጀት ወጣቶች የሥራ እድል ተጠቃሚ እነዲሆኑ ምቹ ሁኔታን እየፈጠረ ይገኝል። ከዚህ በተጨማሪም ከተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር በኮንስትራክሽን፣ በጨርቃጨርቅ፣ በንግድ፣ በአገልግሎት፣ በከተማ ግብርና፣ በቅጥር፣ እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች ወጣቶችን በኢንተርፐራይዞች በማደራጀት ወጣቶች የስራ ዕድል ተጠቃሚ ሆነው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን በኢኮኖሚ እየረዱ ይገኛሉ። በክፍለ ከተማው የሚገኙ ምቹ ሁኔታዎችን አሟጦ በመጠቀም የወጣቶች የስራ ዕድል ተጠቃሚነት እንዲያድግ እየተሰራ ይገኛል። ወጣቶች በመደራጀት የስራ ዕድል ተጠቃሚ በሚሆኑበት ወቅት ከአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ጋር በመተባበር የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ እየተሰራ ይገኛል።



## ወጣት ቢኒያም አሸናፊ
## የወጣት ማህበር ሰብሳቢ

**ልደታ ፋና፡-** በማህበራዊ ዘርፍ ማህበሩ ያከናወናቸው ስራዎች ምን ይመስላሉ?
**ወጣት ቢኒያም፡-** ባለፉት 6 ወራት የስራ አፈጻጸም ውስጥ በማህበራዊ ዘርፎች ተሰማርተን እየሰራን ሲሆን በዚህም በክረምት በጎ ፍቃድ ስራዎች በመደበኛ ተግባራት፣ በሰብአዊ ተግባራት እየሰራን ሲሆን እነዚህ ተግባራትም ለበርካታ አቅመ ደካሞችና ዝቅተኛ ኢኮኖሚ ላላቸው የህብረታብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ችለናል። ሌላው በማህበራዊ ዘርፍ ትኩረት ሰጥተን ከምንሰራባቸው ጉዳዮች ውስጥ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲሆን በተከናወነው ስራም የማጠናከሪያ ትምህርት እና የአይሲቲ አገልግሎት እንዲሁም የልዩ ፍላጎት ትምህርትን በማካተት ውጤታማ ስራዎችን ሰርተናል። ከአካባቢ ልማት ጋር በተያያዘ አካባቢን የሚያስውቡና ለመኖሪያ ምቹ የሚያደርጉ ስራዎችን በወጣት ማህበር ስም የተሰራ ከተሰሩ ስራዎችም የችግኝ ተከላዎችንና የአካባቢ ጽዳትን በማከናወን የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች የተሳኩ እንዲሆኑ አድርገናል።

ወጣቶችን የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በተሰራው ስራ በክፍለ ከተማችን ከሚገኙ ኮሌጆች ጋር በመተባበር በተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉና በተማሩበት ዘርፍ የስራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል። ሌላው በመማህበራዊ ዘርፍ ካከናወናቸው ተግባራት ውስጥ የሰብዓዊ አገልግሎቶች ሲሆኑ ለአረጋዊያንና ለአቅመ ደካሞች እንዲሁም በተለያዩ ሆስፒታሎች ለሚገኙ ወገኖች የማዕድ ማጋራት ፕሮግራሞችን በማዳካሄድ ለወገናችን ደራሽ መሆናችንን አሳይተናል።ከዚህ በተጨማሪ የአቅመ ደካማ ቤቶችን በማሳደስና ለቤታቸው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማሟላት ለነዋሪዎቻችን ከጎናቸው መሆናችንን ያሳየን ሲሆን የደም ልገሳ በማከናወን ደም ለሚያስፈልጋቸው አካላት መርዳት ችለናል።

**ልደታ ፋና፡-**ድንበር ተሻጋሪ የበጎ አድራጎት ስራዎችን ከማከናወን አንጻር ምን ሰራችሁ?
**ወጣት ቢኒያም፡-** ማህበሩ የበጎነት አገልግሎትን ለማከነወን ሲያስብ በልደታ ክፍለ ከተማ ብቻ እንዲወሰን አይፈልግም።

መንግስት ያመቻቸውን ድንበር የለሽ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በመጠቀም ከክፍለ ከተማው ውጭ የበጎ አድራጎት ስራዎችን ሰርቷል፡ ፡ የተወሰኑ አባሎቻችንን በመወከልና በድንበር የለሽ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን (ችግኝ ተከላ ፣ ደም ልገሳ ፣ ማእድ ማጋራት ...) ወደ አጎራባች ክልሎች በመጓዝ ተሳታፊ ሆነናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**ወጣቶች የከተማ ግብርና ስራዎችን በማከናወን የስራ ዕድል ተጠቃሚ ከመሆን አንጻር የተሰሩ ስራዎች
**ወጣት ቢኒያም፡-** ለከተማ ግብርና የተመረጡ ስራዎችን ከወረዳዎች በመረከብ በጎ ፍቃደኛ ወጣቶችን በማስተባበር የጓሮ አትልቶችን መትከልና በመንከባከብ ከጓሮ አትክልቶች ተጠቃሚነት በተጨማሪ የዶሮ ርባታን በማከናወን የገበያ ማረጋጋት ስራው ላይ ውጤታማ ስራዎችን በመስራት ኃላፊነታችንን እየተወጣን እንገኛለን፡፡

**ልደታ ፋና፡-**የትራፊክ አገልግሎትን ከማስተናበር አኳያ የሰራችሁት ስራ ምን ይመስላል?
**ወጣት ቢኒያም፡-** በጎ ፍቃደኛ ወጣቶችን በማስተባበር በተለያዩ ህዝብ በሚበዛባቸውና የትራፊክ
መጨናነቅ በሚኖርባቸው አካባቢዎች የትራፊክ አገልግሎትን በማስተባበር ህብረተሰቡ ከትራፊክ አገልግሎትን ላይ ያለምንም ችግር መንቀሳቀስ እንዲችሉ የሚያደርጉ ስራዎችን ሰርተናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ጊዜና ለሰጡን ማብራሪያ በድጋሜ እናመሰግናለን፡፡
**ወጣጥ ቢኒያም፡-** እኔም በወጣት ማህበሩ ስም አመሰግናለሁ፡፡

## የመንግስት ንብረት የጋራ ሃብት

የአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 84/2016 የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመውጣት የመንግስት ንብረት አስተዳደር ስርዓትን በማዘመን ግልፅ ምቹ፤ ቀልጣፋ እና ከብክነት የፀዳ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ከፍተኛ በጀት ፈሰባቸው የሚገዙ ንብረቶችን ለታለመላቸው አላማ ብቻ እንዲውል ለማስቻል ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ከአዲስ አበባ ከተማ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር እንዲበለፅግ ያደረገው ዘመናዊ የንብረት አስተዳደር ሶፍት ዌር የከተማችን ከንቲባ በተገኙበት ህዳር 27/2017 ዓም ተመርቆ ወደ ተግባር ምዕራፍ መሸጋገሩ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም መረጃ እንዲሰጡን ከልደታ ክፍለ ከተማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡



### ኢ/ር ቅድስት ማቲዎስ
### የመንግስት ንብረት አስተዳር ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** በመጀመርያ ለቃለ-ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እያመሰገንኩ ስምዎትን ያስተዋውቁልን
**እ/ር መቅደስ፡-** እኔም አክብራችሁ ስለጠራችሁን ከልብ እያመሰገንኩ ኢ/ር መቅደስ ማቲዎስ እባላለሁ የልደታ ክፍለ ከተማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ ነኝ፡፡

**ልደታ ፋና፡-**የመንግስት ንብረት አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት ቢገልጹ?
**እ/ር ቅድስት፡-** በመንግስት ህንጻ ንብረት አስተዳደር ላይ ለክፍለ ከተማው አስተዳደር የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል ያማክራል፡፡ የከተማው አስተዳደር ህንጻዎችና ቋሚ ንብረቶችን ይመዘግባል በበላይነት ያስተዳድራል ያድሳል ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ህንጻዎች በመለየት እንዲጠገኑ ያደርጋል፡፡ የህንጻና ንብረት አስተዳደር እና አጠቃቀም ዘመናዊ ስርዓቶችን ይዘረጋል ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል ምድረ ግቢን ውብና ማራኪ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

የመንግስት ህንጻዎች አጠቃቀም ለተጠቃሚው ያላቸው ተደራሽነት እና ከወጪ አንፃር ውጤታማ መሆቸውን ያረጋግጣል፡፡ የተቋማትን ፍላጎት የስራ ባሀሪይ እና የተገልጋይ ሁኔታን በማጥራት የተቋማትንና የስራ ከፍሎች የስራ ቦታ ይደለድላል፡፡ የክፍለ ከተማ አስተዳደሩ የመንግስት ተቋማት ለአገልግሎት አሰጣጥ የሚያስፈልጋቸው ህንጻዎች የኪራይ ደረጃ አጥንቶ ይወስናል ለመንግስት አገልግሎት የሚውሉ ህንጻዎች እንዲገነቡ ያደርጋል፡፡ በክፍለ ከተማው ውስጥ ባለቤት የሌላቸው ህንጻና ንብረቶችን አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተረክቦ ያስተዳድራል፡፡ የመንግስት ህንፃዎች ወጥ የሆነ ስታንዳርድ እና ዲዛይን እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል ያስገነባል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤የህንጻ አስተዳደር ሥራዎች የተቀላጠፉና ውጤታማ እንዲሆኑ የውስጥ አደረጃጀት እና የቢሮ ቁሳቁስ ስታንዳርድ ያዘጋጃል እንዲተገበር ያደርጋል፡፡ በመንግስት የንብረት አያያዝ ስርዓት መሰረት የመንግስት ንብረቶች በአግባቡ ስለመያዛቸው እና ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የንብረት ኦዲት ያደርጋል፡፡ የህንጻና የንብረት ኦዲት ውጤት መሰረት ተገቢው የእርምት እርምጃ ያልወሰዱ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ለይቶ ተጠሪ ለሆነለት ቢሮና ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡ አግባብ ባለው ህግ ቋሚ ንብረቶች ዋጋ እንዲወጣላቸው እና በየዓመቱ የዕልቀት ዋጋ እንዲሰላላቸው በማድረግ መንግስት የቋሚ ንብረቶች የያዙትን ዋጋ እንዲያውቅ ያደርጋል፡፡መንግሰት በሚያስተዳድራቸው ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ህገወጥ ድርጊቶችን ይከላከላል፤ ተፈጽሞም ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤የመንግስት ህንፃዎች የሚገነቡበት ቦታ ያስፈቅዳል፤ ይመዘግባል፤ ተገቢውን የይዞታ ማረጋገጫ እና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ይጠብቃል፡፡ የመንግስት ህንፃዎች የሰራተኞች ካፍቴሪያ፣ የጽዳትና ውበት፣ የጥበቃ፣ የመጀመሪያ ህክምና፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ፣ የመኪና እጥበት እና የህፃናት ማቆያ አገልግሎቶች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** የህንጻና ንብረት አስተዳደር አጠቃቀም ዘመናዊ ስርዓት ከመዘርጋት አንጻር የተሰሩ
ስራዎች ቢዘረዘሩልኝ?

እ/ር ቅድስት፡- እንደ ልደታ ክፍለ ከተማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ፅ/ቤት የተግባር ሂደቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ የሆነውን በሁሉም የአስተዳደሩ ተቋማት ውስጥ በሚሰሩ ሰራተኞች እጅ የሚገኙትን ቋሚ ንብረቶች በተዘጋጀው የኤክሴል ቅፅ የተመዘገቡ ስራዎች ተሰርተዋል ከዚህ በመቀጠል የኤክሴል ቅፅ ላይ የተመዘገቡትን ንብረቶች ወደ ኮምፒውተር ለማስገባት ከ49 ኙም ተቋማት የተውጣጡ 110 የንብረትና የህንፃ ዘርፍ ሰራተኞች ለ12 ተከታታይ ቀናት የቆየ መሰረታዊ የኮምፒውተር አጠቃቀም የመረጃ ስልጠና በመስጠት የተመዘገቡትን የቋሚ ንብረት መረጃዎችን መስራት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከህንጻ አንጻር በአጠቃላይ 447 ህንጻ ሙሉ በሙሉ መመዝገብና መለያ ቁጥር በመስጠት የዕርጅና ቅናሽ ማስላት ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**የህንጻና ንብረት ኦዲት ውጤት መሰረት በማድረግ የተሰራ ስራ ቢጠቅሱልኝ?

**እ/ር ቅድስት፡-** ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስረዓት በመዘርጋት የመንግስት ንብረት ያለአግባብ እንዳይባክን ማድረግ ተችሏል፡፡ የባከነ የመንግስት ንብረቶች በአዋጅና በመመሪያ መሰረት ወደ መንግስት ካዝና ገቢ ማድረግ ተችሏል፡፡ የመንግስት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ስርዓቶች እንዲተገበሩ ተደርጓል፡፡ በመንግስት ንብረት አጠቃቀም ዙሪያ ኦዲት በሚደረግበት ወቅት ያአቅም ግንባታ ስራ መስራት ተችሏል፡፡

**ልደታ ፋና፡-** ዘመናዊ የንብረት አስተዳደር ለመዘርጋት የበለጸጉ ሶፍት ዌሮች ከመጠቀም አንጻር የተሰሩ ስራዎች ይገለጹልኝ?

**እ/ር ቅድስት፡-** በሶፍት ዌር የአሰራር ስርዓት መስራት ተጠቃሚዎችን ከኃላፊዎች ከንብረት ቡድን መሪን ንብረት ግምጃ ቤት ኃላፊን የማስተሳሰር ስራዎችን የመስራትና ከተጠቃሚዎች በራሳቸው ፓስወርድ QR code የመንካትና የንብረት ባለቤትነታቸውን የሚያረጋግጥ አገልግሎትን በሶፍት ዌር ሲስተም ለመጠቀም አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረጉ ይገኛል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ በ48 ተቋማት ላይ የሚገኙ የስቶክ ንብረቶችን የመመዝገብ ወደ ኮምፒውተር የማስገባትና አገልግሎቱን በኦን- ላይን የማስጀመር ሂደት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**በስተመጨረሻም ማስተላለፍ የሚፈለጉት መልክት ካለ?

**እ/ር ቅድስት፡-** በአዲስ እይታ የልደታ ከፍታ በሚል ሞቶ በዘንድሮ በጀት አመት እንደ አስተዳደር የላቀ አፈጻጸም ለማስመዝገብ በርካታ ስራዎችን ለተገልጋይ እና አገልጋይ ምቹ የማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ጽ/ቤት ምቹ የሆነ የመንግስት የውጭ መስተንግዶ ሊያስቀር የሚችል የሆቴል ስታንዳርድ የሰራተኛ ክበብ ካፊቴሪያ እንዲኖር በማድረግ የመንግስትን ወጪ እንዲቆጠብ ማድረግ አና ሰራተኛ ጊዜዉን እና ገንዘቡን እንዲቆጥብ እና ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተችሎአል፡፡ በተጨማሪም ለሰራተኛ የፕሌይ ግራውንድ ግብዓት በማስገባት ሰራተኞች ስራ በሚውሉበት ጊዜ ልጆቻቸው በቂ የመጫወቻ ስፍራ እንዲያገኙ እና ጤንነታቸው እንዲጠበቅማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለተገልጋይ ንፁህ እና አረንጓዴ የስራ አካባቢ መፍጠር ችለናል፡፡ የጂሚናዚየም ፤ የላይብረሪ ፤ የሰራተኛ ሸማች ሱቅ እና ተጨማሪ ሰራዎችን ማከናወን የተቻለበት አመት ነው፡፡ የመንግስትን ንብረት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ እና ለብልሽት እንዳይዳረጉ የተበላሹትም በጊዜ እንዲጠገኑ በማድረግ ወጪ መቆጠብ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የዘመነ የንብረት አያያዝ እንዲኖር ለማስቻል እንደ ፅ/ቤትም ብሎም እንደ ክ/ከተማ አስተዳደር ትኩረት ተሰጥቶ እየሰራን እንገኛለን፡፡ በዚህ አጋጣሚ መላው የክ/ከተማችን ነዋሪዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች እና ተገልጋዮች ውስን የሆነውን የመንግስት ንብረት ከብክነት ለማዳን በተሰማራንበት ሁሉ በባለቤትነት ስሜት ጉዳት ሲደርስ እንድትከላከሉ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለፅ/ቤታችን እንድታሳውቁ መልዕክቴን አስተላልፋለው፡፡

# ንፁህ አካባቢ ለጤናማ ህይወት

አካባቢ ማለት በተወሰነ ቦታ የሚገኙ ህይወት ያላቸዉና የሌላቸዉ ነገሮች ጥምር ነዉ። በሌላ በኩል አካባቢ ሲባል ፊዚካላዊና ስነ-ሕይወታዊ እንዲሁም ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን ያካትታል።

"አካባቢ ጥበቃ " ማለት ደግሞ የሰው ልጅን ጨምሮ የማንኛውም አካል ሕይወት እና እድገት የሚወስኑ የመሬት፣ የውሃ፣ የአየር፣ የአየር ንብረት ሥርዓት የመሳሰሉት ሌሎች የአካባቢ ሀብቶች፣ ክስተቶችና ሁኔታዎች በመጠበቅ የአሁኑን ትውልድ ፍላጎት የማርካቱ ሂደት የመጪውን ትውልድ ዕድል ሳያሰናክል እንዲሟላ ማስቻል ነው። በመሆኑም የምንኖርባት ምድር ለሰዉ ልጅ ምቹና ተስማሚ እንድትሆን በተፈጥሮ የተሰጡን አረንጓዴ መስህቦችና ጤናማ አየር ናቸዉ። ነገር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ የሰዉ ልጅ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ እነዚህን መልካም ጸጋዎችን በተለያዩ ተፈጥሮአዊና በሰው ሰራሽ ብክለቶች እየተበላሹ የምድርቷን ከእዚህ ቀደም የነበራትን መልካም ገጽታ እያጎደፍ መሆኑ ግልጽ የሆነ ችግር ነዉ።

ይህንን በየምንኖርበት አካባቢ ማስተዋል እንችላለን ለአብነትም ምሽትን ተገን በማድረግ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማፍሰስ ብሎም መጣል ልምድ ተደርጎ ዕልባት የጠፋለት ተግዳሮት ሆኖ ይገኛል።

በዛሬዉ የመጽሄት አምድም ዋና ትኩረት አድርገን ለእናንተ ዉድ አንባቢያን ለንባብ ያወጣነዉ ባለንበት ልደታ ክፍለ ከተማ አካባቢን በሚበክሉና በሚወሰዱ እርምጃዎች ዙሪያ ሲሆን ለልደታ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ ለሆኑት ወ/ሮ ቅብአት ገ/ክርስቶስ ቃለ መጠይቅ በማድረግ እንደሚከተለው አቅርበነዋል መልካም ንባብ!



**ወ/ሮ ቅብአት ገ/ክርስቶስ**
**የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-** እንደ ክፍለ ከተማችን አብዛኛዉን ጊዜ አካባቢን የሚበክሉ ተግባራቶች ምንድነዉ?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** ልደታ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት በተሰጠዉ ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በአካባቢ ጉዳዮች ዙሪያ በርካታ ስራዎችን እየሰራ እገኛለሁ።እነዚህም ክ/ከተማችን መሀል ከተማ እንደመሆኗ የህብረተሰቡ አኗኗር እጅግ የተጠጋጋ እና ከአገልግሎት ሰጪ እና አምራች ተቋማት ጋር የተቀላቀለ ስለሆነ ለተለያዩ የአካባቢ ብክለት ተጋላጭ ነዉ። በዋናነትም አካባቢን ከሚበክሉ ተግባሮች ወይም አይነቶች መካከል የተለዩ አሉ እነሱም፦

- .የድምፅ ብክለት
- .የአየር መበከል/የሽታ ብክለት
- .የወንዝ/ዉሃ ብክለት
- .የደረቅ ቆሻሻ ብክለት
- .የእይታ/ጨረር ብክለት
- .የአፈር ብክለት
- .የአደገኛ ኬሚካል ብክለት
- .የሙቀት ብክለት
- .ንዝረት እና ለሎችም ናቸዉ።

እንደኛ ተቋምም ከተገለጹት ብክለቶች አንዱም እንዳይከሰት የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ እየሰራ ይገኛል።

**ልደታ ፋና፡-** ለአካባቢ ብክለት ምንጭ የሚባሉት ምንድን ናቸዉ?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** ለአካባቢ ብክለት ምክንያት ወይም ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ምክንያቶች አሉ። እኛም እንደ ባለድርሻ አካል በችግሩ ዙሪያ ጥልቅ የሆነ ጥናት በማድረግ በዋናነት የችግሩ ምክንያቶች ምንድናቸዉ ብለን መለየት ችለናል። ይህንን ስንል እንደየአካባቢያችን የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም በክፍለ ከተማችን ደረጃ የለየናቸዉ የአካባቢ ብክለት ምንጮች አሉ እነሱም

- .አገልግሎት ሰጪ ተቋማት
- .አምራች ድርጅቶች
- .ከተሸከርካሪዎች የሚለቀቅ ጭስና ድምፅ
- .ከመኖሪያ ቤቶች የሚወጣ ቆሻሻ
- .ከገበያ ስፍራዎች እና ከጤና ተቋማት የሚወጣ ብሎም የሚለቀቅ ቆሻሻ
- .ከግንባታ ስፍራዎች የሚለቀቁ ተረፈ ምርቶችና ፍሳሾች

**ልደታ ፋና፡-** አካባቢን ከብክለት ለመጠበቅ እንደ ጽ/ቤቱ የተሰሩ ስራዎች አሉ?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** ከላይ የጠቀስኳቸዉን ብክለቶች ለመከላከል በርካታ ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን። ከ300 በላይ ተቋማት ላይ ክበባዊ አየር ብክለት ፣ ወንዝ ብክለት ፤የፍሳሽ ናሙና ማስመርመር፤የአፈር ብክለት፤በደረቅ ቆሻሻ ብክለት እና ድምፅ ብክለት ዙሪያ በቼክሊስት የክትትልና የቁጥጥር ስራ መስራት ተችሏል። ተቋማት የአካባቢ ችግሮቻቸዉን እንዲያስተካክሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን እየተሰራ ይገኛል። በ45 የመንግስትና የግል ት/ቤቶች የአካባቢ እንክብካቤ ክበብ በማቋቋም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን እየተሰራ ይገኛል። የአካባቢ ጉዳይ የሁሉም አካላት ጉዳይ በመሆኑ በጋራ ርብርብ ስለሚያስፍልግ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት እና ትስስር በመፈጠር በጋራ እየተሰራ ይገኛል።

አካባቢ ጉዳዮችን በተመለከተ በአካባቢ ብክለት፤በአየር ንብረት ለዉጥ እና በስርዓተ ምህዳርና ብዝሃ ህይወት ዙሪያ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት፤ለተለያዩ የህ/ሰብ ክፍሎች፤አምራች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በገፅ ለገፅ መድረኮች፤በብሮሽር፤ ቤት ለቤት ፤ በማህበራዊ ሚዲያዎች እና የተለያዩ አደረጃጀቶች በመጠቀም ከ80ሺህ በላይ ለሚሆኑት አካላት ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-**አካባቢን ከሚበክሉና ማስተካከል ያልቻሉ አካላት ላይ ምን አይነት እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** አካባቢን ሲበክሉ የተገኙ 84 ተቋማት እና ግለሰቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ መዉሰድ ተችሏል፣50 ተቋማት የመጨረሻ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፣34 ተቋማት እና ግለሰቦች በተደጋጋሚ ግንዛቤ በመፍጠር ወንዝና ወንዝ ዳርቻዎችን በቀጥታ ሲበክሉ በመገኘታቸዉና ባለማስተካከላቸዉ እያንዳንዳቸዉን በለቀቁት የብክለት መጠን በገንዘብ በመቅጣት 7,664,000 ብር ገቢ ተደርጓል።

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በክፍለ ከተማው የሚስተዋለው የአካባቢ ብክለት ለመከላከል እና የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ለማረጋገጥ ክፍለ ከተማዋ ለኑሮ ምቹ ውብ ጽዱ ማራኪ እና በአረንጓዴ ልማት ያሸበረቀች እንድትሆንና ገጽታውን ለመቀየር የሚያስችል የህብረተሰቡን አመለካከት በመቀየርና የአካባቢ ጉዳይ የራሴ ጉዳይ ነው ብሎ ምቹ አካባቢ ለመፍጠር የሚያስችል ሥራዎች እየተሰራ ይገኛል።

በመሆኑም የተለያዩ ተግባራት ለማከናወን የተደረገ ጥረት ቢኖርም የክፍለ ከተማው ነዋሪ መሠረታዊ ፍላጐት ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ በመምጣቱ የአካባቢ ጉዳዩ ከህዝብ መሠረታዊ የህይወት የመኖር ፍላጐት ጋር የተቆራኘና በምቹ ጽዱ ውብ፣አረንጓዴ አካባቢ በመኖር ህይወቱንና የአኗኗር ሂደትን ይበልጥ ለማሳተካከል ብሎም ጤናማ ለማድረግ አረንጓዴ ልማትና ጽዱ መንደር አስፈላጊነቱ ይበልጥ የአመለካከት ለውጥ እያደገ በመምጣቱና ጽ/ቤቱም ይህንን ዘርፈ ብዙ ስራዎችን ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት በዜጎች ላይ የአመለካከት ለዉጥ እና የአካባቢ ተቋርቋሪነት እንድፍጠር ሁሉም አካላት ርብርብ ማድረግ ይጠበቃል ለማለት እወዳለሁ አመሰግናለሁ

**ልደታ ፋና፡-**ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ ሆነዉ ጊዜዎን ስለሰጡን እናመሰግናለን።

**ወ/ሮ ቅብአት፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

## የሴቶች ተሳትፎ ለዘላቂ ልማት

የልደታ ክ/ከተማ ሴቶች ማህበር ህገ መንግስታዊ የመደራጀት መብቱን በመጠቀም ከ28 አመታት በፊት የተደራጀ የጻታ ማህበር ነው።በዚህም በባለፉት በርካታ አመታት እልፍ ውጤቶችን በሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴው ማከናወን ችሏል።ማህበሩ በየአመቱ ከክፍለ ከተማ እስከ ወረዳ ያሉ አመራሮችና በጎ ፍቃደኞችን በማሳተፍ እቅድ በማዘጋጀት ዋና ዋና ስራዎችን አሳክቷል ፤በተለይ የአባላት ምልመላ፣ነባር አባላት መልሰው አባልነታቸውን እንዲያድሱ በማድረግ፤ የስራ እድል ፈጠራ፣የቁጠባና ብድር ተግባሩን፣የሰላም ሰራዊት በመሆን ከፊት ሆነው አባላቱ የሰላምና ፀጥታውን በማስከበር ለውጥ በማስመዝገብ አኩሪ ስራ መስራት ችሏል። ሌላው የትምህርት እድል ያላገኙ ሴቶችን በመለየት እንዲማሩ ከትምህርት ተቋማት ጋር በመቀናጀት ማመቻቸት ተችሎዋል፤ የጤና ተግባርን በማስመልከት ከቢሮ ጀምሮ እስከ ታች በጋራ በመሆን ለእናቶችና ህጻናት ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሎዋል። በአጠቃላይ ማህበሩ የበጎ ፍቃድ ስራን በማጎልበት ውጤታማ ስራ አከናውኖዋል ። በማህበሩ ዙርያ መረጃዎችን እንዲሰጡን የዝግጅት ክፍላችን ከክፍለ ከተማው ሴት ማህበር ሰብሳቢ ጋር ቆይታ አድርጓል ተከታተሉን

**ልደታ ፋና፡-** በቅድሚያ ለሚሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን ራስዎትን ያስተዋውቁልን

**ወ/ሮ ገነት፡-** ገነት ገ/መድህን እባላለሁ የልደታ ክፍለ ከተማ ሴት ማህበር ሰብሳቢ ነኝ።

**ልደታ ፋና፡-**የክፍለ ከተማ ሴት ማህበር አደረጃጀት ዋና አላማው ምንድን ነው?

**ወ/ሮ ገነት፡-** የማህበሩን የሰው፤ የቁሳቁስና የገንዘብ አቅም ማሳደግና ከአሰራር ስልት ጋር በማቀናጀት የማህበሩን የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፤ብዙሀን ሴቶች በማህበሩ ዙሪያ ተሰባስበውና ኃይል ፈጥረው በመደራጀት በልማቱና በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታው ጠንካራ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና የሴቶች ማህበራዊ፤ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች የሚቀረፉበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት በሀገራችን ያለውን የስርዓተ-ፆታ እኩልነት ክፍተት በማጥበብ ለሥርዓተ ፆታ እኩልነትና ለሴቶች ሰብዓዊ መብት መከበር መስራት ነው።

**ልደታ ፋና፡-** የማህበሩ አደረጃጀት ምን ይመስላል

**ወ/ሮ ገነት፡-** በ10 ወረዳዎች 500 በአንድ ወረዳ 50 የም/ቤት አባላት በአንድ ወረዳ ከቋሚ ተቀጣሪዋ ውጭ 10 የስራ አስፈጻሚ አባላት የወረዳዋን ቀጠና ማእከል ያደረገ አደረጃጀት አለው።



## ወ/ሮ ገነት ገ/መድህን
## የሴት ማህበር ሰብሳቢ

**ልደታ ፋና፡-** ማህበሩ አላማውን ለማሳካት ምን ተግባሮችን እየሰራ ነው?

**ወ/ሮ ገነት፡-** ማህበሩ የአሰራር ስርዓቱን ምቹና ተደራሽ ለማድረግ በየብሎኮች ከ110 በላይ በጎ ፈቃደኞች እስከ ቀጠና ድረስ የማህበሩን አባላትና ሴቶችን አገልግሎት መስጠት ፤ማህበሩ ስራዎችን የሚያከናውነው በተለይም የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ቤት ለቤት በር በማንኳኳት የሚሰራ አደረጃጀት ያለው ሲሆን ስራ የሌላቸው ሴቶች ለይቶ መዝግቦ በመያዝ ከሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል።በተጨማሪም የስርአተ ጾታ እኩልነትን ለማምጣትና ልዩነቱን ለማጥበብ ብሎም በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለመከላከል እንዲያመች 4200 በላይ ወንድ ተባባሪ አባላትን ያሳተፈ ነው። ከነዚህ መካከል በ10 ወረዳዎች የወንደች አጋርነት በአንድ ተደራጅተው ከማህበሩ ጋር የሴቶችን ጥቃት ለመከላከል በቅርበት አብረው እየሰሩ ይገኛሉ።

**ልደታ ፋና፡-**በእነዚህ ስራዎች ላይ ያስመዘገበው ውጤት ምንድን ነው?

**ወ/ሮ ገነት፡-** ሴቶች የተለያዩ ስልጠናዎች እንዲያገኙና በተለያየ የሥራ መስክ እንዲሰማሩ በማድረግ ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ለማላቀቅ ማሃበሩ ለራሱ ህብረት ስራ በማቋቋም ቁጠባ በማስጀመር በአነስተኛ ብድር ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሴቶች በማበደር ወደ ስራ እንዲገቡና ስራ እንዲፈጥሩ ሰፊ ስራ ተሰርቷል።ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች መብታቸውን ለማስከበር የሕግ ምክር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት በክፍለ ከተማው ጥቃት ደርሶባቸው መሄጃ የሌላቸው ሴቶች የጥቃት ማገገሚያ መጠለያ በመክፈት ሴቶች የምግብ፤ የአልባሳትና እንዲሁም የስነ ልቦና እና የህግ አገልግሎቶች ጭምር የሚያገኙበትና አገግሞ ወደ ስራ የማስገባት ስራ በሰፊው እየሰራ ይገኛል።

ማህበሩ ከተለያዩ NGO ጋር በጋራ በመሆን የተለያዩ የሙያዊ ቁሳቁሶች አገልግሎት የሚሰጡ በማመቻቸት ለምሳሌ የፀጉር ታክስ ፤ የልብስ ሰፌት ማሽን፤ የተለያዩ ቁሳቁሶች ሴቶችና ሰርተው ራሳቸው እንዲለወጡ መነሻ ካፒታል ከህብረት ስራው ብድር በማመቻቸት እራሳቸው እንዲችሉ ና ለሌሎች ስራ እንዲ ፈጥሩ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡

ጎጂ ባህላዊና ልማዳዊ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ለመለወጥ የህብረተሰቡን ግንዘቤ ማሳደግ። በተለይ በስነተዋልዶ ጤና፤ በቤተሰብ ምጣኔ፤ በኤች አይ ቪ ኤድስ፤ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና በሴቶች ጥቃት ዙሪያ ዝምታን ለመስበር ዐውደ ጥናት፤ የፓናል ውይይት፤ በሚድያና ጽሁፎችን በማሰራጨት ሰፊ ሥራ ተሰርቷል። ሴቶች የስነ ታዋልዶ ጤና መብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በተለይ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ሥራ ተሰርቷል።

የሴቶች ሰብዓዊ መብት በበለጠ እንዲዳብርና ሴቶች በሕብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚና ጎልቶ እንዲወጣና እንዲያድግ በየደረጃው ከሚገኙ የመንግስት አካላት ጋር በመመካከር ሕጎች እንዲሻሻሉና አዳዲስ ሕጎችም እንዲወጡ ሕብረተሰቡን በማነሳሳት ግፊትና ጫና በሰላማዊ ሰልፍ፤ በፓናል ውይይት፤ ወዘተ...ማድረግ

ሴቶች ተሻሽለው የወጡ ሕጎችን እንዲያውቁዋቸው በማድረግ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማድረግ ተችሏል።በተጨማሪም በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሴት ተማሪዎችን ትምህርት በማበረታትና ድጋፍ በማድረግ ሴቶች በአመራርና በውሳኔ ሰጭነት ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዲኖራቸው ሴቶች በዲሞክራሲያዊው ስርዓት ግንባታና በመልካም አስተዳደር ውስጥ ጉልህ ተሳትፎና ሚና እንዲኖራቸው የሲቪክ ኢዱኬሽን ትምህርት በሰፊው ማዳረስ በቤተሰብ ውስጥ ያለመግባባት ችግር ሲፈጠር ቤተሰብ እንዳይፈርስና ልጆች አደጋ ላይ እንዳይወድቁ የምክር አገልግሎት በመስጠት ችግሮችን መፍታት ስራ ተሰርቷል።

**ልደታ ፋና፡-** በቀጣይ የተያዘውን አላማ ለማሳካት ከመንግስት ምን አይነት እገዛዎችን ይፈልጋሉ?

**ወ/ሮ ገነት፡-** መንግስት የመደራጀት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ሴቶች በጾታቸዉ በመደራጀት ጥቅሞቻቸዉን እና መብቶቻቸዉን ለማስከበር ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አንጻር ተገንዝቦ የተለያዩ አደረጃጀቶች እንዲጠናከሩ ማህበሩ የዲሞክራሲ ስርአት መገንቢያ ተቋም እንዲሆኑ በተለይም ደግሞ ለሴቶች የተሰጠው ልዩ ድጋፍ እርምጃ ሴቶች ለጾታቸዉ ዋጋ ሰጥተዉ በሁሉም የልማት መስክ መሳተፍ የሚያስችል መነሳሳት በመፈጠሩ አልሞ በመስራት በትምህርትና በጤና ልማት ስራዎቻችን ሴቶች ግንባር ቀደም ሚናቸወን እንዲጫወቱና የአባላትን ሁሉን አቀፍ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸው ያረጋገጠ የሴቶች አደረጃጀት መሆን ችሏል። ምንም እኳን ማህበሩ አሁን ከደረሰበት ደረጃ ቢደርስም ከሚጠበቅበት አንጻር ሲታይ ገና ብዙ መስራት የሚጠበቅበት በመሆኑ በቀጣይ መንግስት የተሻለ ለውጥ ለማምጣት የምናቅዳቸዉ ግቦች ከዚህ መሰረታዊ ሁኔታዎች የሚነሱ ስለሆኑ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ድጋፍና ርብርብ ያስፈልጋል።

ልደታ ፋና፡- በመጨረሻ ማስተላለፍ የምትፈልጉት መልእክት ካለ
ወ/ሮ ገነት፡- የሴቶች ማህበራዊ፤ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች የሚቀረፉበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት በሀገራችን ያለውን የስርዓተ ፆታ እኩልነት ክፍተት በማጥበብ ለሥርዓተ ፆታ እኩልነትና ለሴቶች ሰብዓዊ መብት መከበር የሁሉም ሰው ሃላፊነት በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካል መወጣት አለበት።

**ልደታ ፋና፡-**ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ ሆነዉ ጊዜዎን ስለሰጡን እናመሰግናለን።
**ወ/ሮ ገነት፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# የህግ ተፈፃሚነትን ያረጋገጠ ተቋም

የልደታ ክፍለ ከተማ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት በአዋጅ 84/2016 ዓ/ም አንቀፅ 50 ከተማ አስተዳደሩ በተሰጠው ተግባር እና ሃላፊነት መሰረት የደንብ ጥሰቶችን መከላከልና ተላልፎ በሚገኘዉ አካል ላይ ተገቢዉን እርምጃ ይወስዳል በዚሁ መሰረት በበጀት አመቱ የደንብ መተላለፍን በ61% መቀነስ እንደተቻለ ጽ/ቤቱ ያስረዳል። ባሳለፍነው 6 ወራት እየተከናወኑ የሚገኙ ስራዎችን በማስመልከት በምን ሁኔታላይ እንዳሉ የዝግጅት ክፍላችን ከጽ/ቤቱ ሃላፊ አቶ አበራ ኢትቻ ጋር ቆይታ አድርጓል መልካም ንባብ።

**ልደታ ፋና፡-** በቅድሚያ ለቃለምልልሱ ፍቃደኛ ስለሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ
**አቶ አበራ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

**ልደታ ፋና፡-** ጽ/ቤቱ ከሌሎች አጠቃላይ የደንብ መተላለፎች አንጻር ከተለያዩ ባለድርሻ ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት የሚስተዋሉ ህገ- ወጥነቶችን በቅድመ መከላከል ስራዎች ከመቀነስ አንፃር ምንደረጃ ላይ ነዉ ያለዉ
**አቶ አበራ፡-** ጽ/ቤታችን ባሳለፍነዉ 2017 በጀት አመት በ5 ወር ከነበረው 471 የደንብ መተላለፎች ዘንድሮ በያዝነው በጀት ዓመት ወደ 183 ዝቅ ማድረግ የቻለ ሲሆን በዚህ በያዝነዉ በጀት አመት የደንብ መተላለፍን በ61% መቀነስ ችለናል።



## የአቶ አበራ ኢትቻ
## የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ሃላፊ

**ልደታ ፋና፡-** የደንብ ጥሰትን ከመቀነስ አንጻር የቅድመ መከላከል የግንዛቤ ስራዉ እንዴት እየተሰራ ይገኛል
**አቶ አበራ፡-** ባለስልጣን መስሪያ ቤታችን በአዋጅ 84/2016 ዓ/ም አንቀፅ 50 ከተማ አስተዳደሩ በተሰጠው ተግባር እና ሃላፊነት መሰረት የቅድመ መካላከል እና ስልጠና ዘርፍ እንደገና በማቋቋም ለነባር ኦፊሰሮች የንድፈ ሃሳብ እና ከፊል ወታደራዊ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ፣በጎ ፈቃደኞችን መመልመል እንዲሁም የህብረተሰብ ተኮር የግንዛቤ ማስጨበጥ ተግባራትን በማከናወን ደንብ የሚተላለፉትን

አካላት ተገቢዉን የእርምት እርምጃ እየወሰደ እየሰራ ይገኛል፡- በቡና ጡጡ እና ቤት ለቤት፣ አደረጃጀት እና ብሎክ ላይ ያሉ ነዋሪዎች በመድረክ ፣ አጠቃላይ ማህበረሰቡን የንቅናቄ መድረክ በማዘጋጀት፣ በተሽከርካሪ የታገዘ አደባባይ ላይ የሞንታርቦ ቅስቀሳ በማካሄድ፣ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ በራሪ ፅሁፎችን በማሰራጨት እየሰራን እንገኛለን በመሆኑም በእነዚህ የግንዛቤ መፍጠሪያ መንገዶች ከወረዳ እስከ ክፍለ ከተማ ደረስ ባሉን ባለሙያዎች ለ121,787 ማህበረሰብ በድግግሞሽ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡



**የግንዛቤ ስራ ሲሰራ የሚያሳይ**

**ልደታ ፋና፡-** የማህበረሰቡ ትብብር ፣ጥቆማና አስተያየት ከመስጠት አንጻር ያለዉ የስራ አጋርነት እንዴት ይገለጻል የጠቆማ የስልክ መስመርስ ስለመኖሩ ቢገልጹልኝ

**አቶ አበራ፡-** በያዝነው በጀት ዓመት 23 ጥቆማ ከማህበረሰቡ እና በጎ ፍቃደኞች የደረሰን ሲሆን ይህንን ሙሉ በሙሉ መፍታት ችለናል አልፎ አልፎ ደግሙ ከተማው በዘረገው 9995 ነፃ የስልክ መስመር በመጠቀም ላቀረቧቸው ጥቆማዎች ተገቢውን ምላሽ ሰጥተናል፡፡

**ልደታ ፋና፡-**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን በከተማ አስተዳደሩ ከተሰጡት ዋና ዋና ተግባራት በተጨማሪ በተለያዩ የፀጥታ ስራዎችና በበጎ ፍቃድ አገልግሎት አንጻር ያለዉ አስተዋጽኦ ምንድነዉ

**አቶ አበራ፡-** በጽ/ቤታችን 8 ማህበራዊ ቀውስ ያጋጠማቸው ወላጅ አልባ ህፃናትን በቋሚነት አጠቃላይ ሰራተኛው በወር ከሚያገኘው ደሞዝ 493 ሰራተኞች 0.5%ተቆራጭ በማድረግ በእየወሩ 4000ብር (አራት ሺ ብር ) ድጋፍ በማድረግ እና ወረዳ 05 ላይ የሚገኙ የአንድ አቅመ-ደካማ ቤት ሙሉ በሙሉ አፍርሰን የተሰራ ሲሆን አጠቃላይ ቤቱን ለመስራት 565,000 ብር ፈጅቷል እንዲሁም ለተረጅ ህፃናትና አቅመ ደካሞች የማዕድ ማጋራት የተደረገ ሲሆን ለ58 ማህበረሰብ የመማሪያ ቁሳቁስ ደብተር፣ ቦርሳ ፣ ዱቄት፤ዘይት፤እና ሶፍት የመደገፍ ሲሆን በብር ሲለካ 195,840 ድጋፍ ተሰርቷል፡፡



**በበጎ ፍቃድ ሲሰራ የሚያሳይ**

**ልደታ ፋና፡-**ተቋሙን በሰው ሃይል በግብዓት በማጠናከር ጠንካራና ለስራ አመቺ የሆኑ አሰራሮችን ከመዘርጋ አንጻር የተሰሩ ስራዎች ካሉ

**አቶ አበራ፡-** ሌላው ከሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት ፤ከሰላም ሰራዊት እና ከፖሊስ ጋር በመቀናጀት ኦፊሰሮችን እስከ ምሽት 4፡00 ስዓት እና የመኖርያ ቦታቸው ከክ/ከተማችንን ውጭ የሆኑትን ማደሪያ ስፍራ በማዘጋጀት አድረው ጭምር የክ/ከተማችን ሰላም ከማስከበር አንፃር ከፍተኛ ስራ እየሰራን እንገኛለን፡፡ ጽ/ቤታችን ካለው ሃይል አንፃር በ4 ቡድን ቀጥታ ለጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪ የሆኑ 1 የህግ ባለሙያ እና የንብረት ክፍል እንዲሁም 1 አስተባባሪ የተዋቀረ ሲሆን በተለይም የቁጥጥር ኢንስፔክሽን እና ግብረ-ኃይል ቡድን ላይ ያለብንን የፓራ-ሚሊተሪ ኦፊሰሮችን ከተለያዩ ወረዳዎች በውሰት በማስመጣት የሰው ሃይል ችግራችንን በጊዜዓዊነት የፈታን ሲሆን በቀጣይ ከማዕከሉ እና እዚህ ክ/ከተማ ላይ ከላው የፐብሊክ ሰርቨስ እና የሰው ሃይል ጋር በመነጋገር ዘላቂ በተለይም ከፍተኛ በሆኑ መደቦች ላይ ለቦታው ብቁ የሆኑ የሰው ሃይል የማሟላት ስራ እንሰራለን፡፡ ከግባአት አንፃር በጽ/ቤታችን ለስራ አስፈላጊ የሚባሉ ኮምፒውተር ፕሪንተር ስር እና የመሳሰሉ ግብአቶችን ባለው የሰው ኃይል ልክ ለማድረግ ጥረት ጀምረናል አገልግሎት የማይሰጡትንም ቢሆን ለይተን ላለው 3 ቦታ መረጃውን ሰጥተናል ከዚህ አናፃር ተጠግነው አገልግሎት መስጠት በጀመሩ እና በግዥ የጠየቅናቸው ችግራችን ይቀረፍልናል ብለን እናምናለን ሌላው ከምንም በላይ ለስራ እንቅፍት የሆነብን የተሽከርካሪ ጉዳይ ነው ይህም የክትትል ድጋፍ እንዲሁም ቁጥጥር ስራ በቀን በምሽት ለመስራት ያለን ተሽከርካሪ 1 ነው እንደ ኃላፊ ደግሞ የተመደበ ተሽከርካሪ ባለመኖሩ ይህ ነው ፓትሮል ስትበላሽ እና ለአገልግሎት ወደ ጋራዥ ስትገባ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ነው የምንገባው ይህን የሚመለከተው አካል በተለይም የዋና ስራ አስፈፃሚ ጽ/ቤት ጉዳዩ ላይ ትኩረት ስጥቶ ዘላቂ የሆነ መፍትሄ ቢሰጠን እላለሁ

**ልደታ ፋና፡-** በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ

**አቶ አበራ፡-** አመሰግናለሁ ባለድርሻ አካላት ከእኛ ጋር ተቀናጅተው መስራታቸው የማይተካ ሚና አላቸው ስራን በ3 ወር ከመገምገም ባለፈ በዕለት ተዕለት ዋና ስራችን ላይ አጋዥነታቸውን ቢጠናከር

የበጎ ፍቃደኛ ነዋሪዎችን አሁን በጀመሩት ድጋፍ አጠንክረው ቢሳተፉ አጠቃላይ ማህበረሰባችን የደንብ መተላለፎችን የሚፀየፍ ህገ-ወጥነትን የሚያበረታታ ሳይሆን ሞጋች ሆኖ የሰጠው መረጃ የት ደረሰ ብሎ ጭምር የሚጠይቅ እንዲሆን ስል መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡

**ልደታ ፋና፡-**ስለ ቃለ ምልልሱ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ እና መሰግናለን፡፡

**አቶ አበራ፡-** ለተደረገልኝ ቃለ-መጠየቅ በራሴ እና በጽ/ቤቱ ስም ከልብ አመሰግናለሁ!!!

ፕላንና ልማት ጽ/ቤቶች ለተቋሙ በተሰጠዉ ሀላፊነት መሰረት ሁለት ፕላኖችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን አነዚህም የስፓሻል ፕላን (ገጸ ምድር ፕላን)፤የማህበራዊ ኢኮኖሚ ልማት እቅድ፣ አፈፃፀም፣ ክትትል እና ግምገማ ናቸዉ፡፡ የልደታ ክ/ከተማ ፕላንና ልማት ጽ/ቤት መዋቅራዊ ፕላኑን ለመፈፀም በተዘጋጁ ዝርዝር የስፓሻል ፕላኖች መሰረት ለተገልጋዮች እና ባለድርሻ አካላት አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን በሌላ በኩል የማህበራዊ ኢኮኖሚ ልማት ፕላን፣ የአፈፃፀም ሪፖርት፣ የክትትል፣ ድጋፍ እና ምዘና ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል ፡፡

የክፍለ ከተማዉን ስፓሻል ፕላን ዝግጅትና አሰራር ከማሻሻል አንፃር ከመሬት ተቋማት እና ግንባታ ፈቃድ ክትትልና ቁጥጥር ጽ/ቤት ለቀረቡ የዉስጥ ለዉስጥ መንገድ ጥናቶች፣ የፕላን ማብራሪያና አስተያየት ጥያቄዎች ከመዋቅራዊ ፕላን አኳያ በማየት ለሁሉም የፕላን ማብራሪያ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ለሁሉም የፕላን ማብራሪያ ምላሽ መስጠት ተችሏል፡፡



**ወ/ሮ ወይኒቱ ሀይሉ**
**ፕላንና ልማት ጽ/ቤት ሃላፊ**

## ፕላን ለከተማ ገፅታ

በክፍለ ከተማው የሚገኙትን የመንገድ ፕላን መረጃዎች በአውቶካድ ሶፍት ዌር በአንድ ቤዝማፕ የማደራጀት ስራ ተከናውኗል፡፡ የይዞታ ካርታዎች እና የግንባታ ፈቃድ መረጃዎች በመሰብሰብ ከፕላን አንጻር ትክክለኛነታቸው በማረጋገጥ በቤዝማፕ የማደራጀት ስራ በመከናወን የግንባታ ፈቃድ መረጃዎችን በቤዝማፕ እንዲደራጅ ተደርጓል ፡፡ ሰብሳቢና የውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ አርንጓዴ ልማት፣ የወንዝ ዳርቻ መጠበቂያ አካባቢዎች የፕላን አፈፃፀም እና አጠቃቀም በቀጣይ ወደ ቁጥጥር ስራዉ ለመግባት በሚያስችል ሁኔታ የመስክ ክትትል በማድረግና ሪፖርት በማዘጋጀት ለፕላንና ልማት ቢሮ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

የማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት እቅድ እና የአፈጻፀም ሪፖርት ከማዘጋጀት አንፃር የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ በሴክተሮች የተዘጋጁ እቅዶችንና ሪፖርቶችን በማሰባሰብ የክፍለ ከተማ አስተዳደሩን መሪ እቅድ፣ የተከለሰ እቅድ እና ሪፖርቶችን በማዘጋጀ ለክፍለ ከተማ አስተዳደሩ በወቅቱ እንዲቀርብ የማድረግ ስራዎች እየተሰራ ይገኛል፡፡ የፕላን መረጃ ዝግጅት አደረጃጀትና ስርጭት በተመለከተ ተቋማችን የተለያዩ የፕላን መረጃዎችን የማደራጀትና ለፕላን ተግባር ተቋማት ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ ስራ የሚሰራ ሲሆን በዚሁም መሰረት በየበጀት አመቱ የሚዘጋጀዉን የሳተላይት ምስል መረጃ፣ ከማዕከል የተላከ ወቅታዊ የመዋቅራዊ መንገድ መረጃ፣ የህንፃ ከፍታ ማሻሻያ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል እንድደርስ ማድረግ መቻሉ፡፡

# መልካም አስተዳደርና የህዝብ ተጠቃሚነት

የልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የመልካም አስተዳደር ቅሬታና አቤቱታ ጽ/ቤት የማህበረሰቡን የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በተደራጀ መንገድ ለመፍታት በትኩረት እየሰራ ነው። ጽ/ቤቱ ማህበረሰቡ የሚያቀርባቸውን የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በመሌትና ህዝብን በማሳተፍ እየፈታ ውጤታማ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። በዚህ ጽሁፍ ጽ/ቤቱ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በመፍታት የህዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እያከናዎናቸው ያሉ ስራዎችን ዳሰናል መልካም ንባብ።

**ልደታ ፋና፡-** የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እንዴት ለያቹህ?
**አቶ ይልማ፡-** የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመለየት ከብሎክ እስከ ክፍለ ከተማ መድረክ ተፈጥሯል።በተፈጠሩ መድረኮች ማህበረሰቡ የሚያነሳቸውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለይተናል።

**ልደታ ፋና፡-** በህዝብ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር እና የቅሬታ ምንጭ የሆኑ ችግሮችን በአግባቡ በመለየት እና በመፍታት የመጣ ተጨባጭ ውጤት ቢጠቅሱልን?
**አቶ ይልማ፡-**በአንድ መአከል ተደጋግመው የሚነሱ የቤት ጥያቄዎችን ለመፍታት ከብሎክ እስከ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎችን በማወያየት 1000 ቤት ፈላጊዎች ወረፋ እንዲጠብቁ በማስቻልና በህገ-ወጥ ተይዘው የነበሩ 212 ቤቶች በማስለቀቅ የከተማችን ክብርት ከንቲባ በተገኙበት ቤት ማስተላለፍ ተችሏል።



**አቶ ይልማ ተረፈ**
**የመልካም አስተዳደር ቅሬታና አቤቱታ ጽ/ቤት ኃላፊ**

የመልካም አስተዳደር ችግሮች ከብሎክና ወረዳ የህዝብ መድረክ 36 እንዲሁም ከክፍለ ከተማ ተቋማት 57 በድምሩ 93 የመልካም አስተዳደር ችግሮች በዓመቱ ለመፍታት የታቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ6 ወሩ 47 የመልካም አስተዳደር ለመፍታት የተለዩ ሲሆን 56 በመፍታት በግማሽ አመቱ ከእቅዱ 100% በላይ መፈፀም ተችሏል።

**ልደታ ፋና፡-**የባለድርሻ አካላት የህዝብና ሲቪል ማኅበራት የግል ሴክተር ተሳትፎ መን ይመስላል?
**አቶ ይልማ፡-** በአስተዳደሩ የሚገኙ ሁሉም የመንግስት ተቋማት ባላድርሻና እገዛ የሚያደርጉላቸውን የሲቪል ማህበራት በመለየት፣ በማቀድና በማሳተፍ ሚናቸውን እንዲወጡ አስችለዋል። የተለዩ ተቋማት ዝርዝርና አሳታፊ አቅድ በማዘጋጀት የጋራ ውይይትና በሩብ አመትና በግማሽ አመት ስራን በጋራ ገምግመዋል።እነዚህን ሲቪል ተቋማት በጋራ አላማ በማሳተፍ የቅሬታ ምንጭን ለመቀነስ ተችሏል፡ ፡ በዚህም በዚህ የግማሽ አመት አፈፃፀም በፅሁፍ የቀረቡ ቅሬታዎች 23 ሲሆኑ ከዚህ ወስጥ አግባብነት ያለው 19 ሲሆን 16 ቱ ተፈተው 3 በሂደት ላይ ያሉ ናቸው(የቀረበው ቅሬታ መጠንም ካለፈው አመት ቀንሷል)

በአንድ መዓከል አገልግሎት የሚበርቡ ቅሬታዎችን ድግግሞሽ በመለየት የህዝብ መድረክ በመፍጠር ቅሬታዎችን ከምንጩ በማድረግ ባለፈው በጀት ዓመት በግማሽ አመት ከቀረበው- 780 ቅሬታ በዘንድሮው በጀት አመት ወደ 339 እንዲቀንስ ማስቻል ተችሏል።

**ልደታ ፋና ፡-** ለሰቱን ማብራሪያ እናመሰግናለን
**አቶ ይልማ፡-** እኔም አመሰግናለው

# የተቀናጀ አገልግሎት አሰጣጥ በልደታ

**ልደታ ፋና፡-**በ2018 በጀት እያከናወናችሁ ያላችሁት ስራ ምን ይመስላል?

**አቶ ጢቂ ድሪባ፡-**ጽ/ቤታችን በበጀት ዓመቱ በርካታ ተግባራትን ለማከናወን አቅዶ ስራዎችን በእቅዳቸው መሰረት እያከናወንን እንገኛለን።ዋና ስራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት በስሩ በርካታ ተቋማት ያቀፈና የተለያዩ አገልግሎቶች የሚገኙበት እንደመሆኑ መጠን ሰፊ ተልዕኮ ይዘን የክፍለ ከተማውን ነዋሪዎች ማዕከል ያደረገ አገልግሎት እንዲሰጥ ጥረቶችን በማድረግ ውጤታማ ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን።በዚህም የህብረተሰቡን የአገልግሎት ፍላጎት ከግምት በማስገባት የነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና በጾጥታና በመልካም አስተዳደር ዘርፍ ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠን እንገኛለን። ይህን አገልግሎት በመስጠታችንም የህብረተሰቡ የአገልግሎት ፍላጎት እየተሸሻለ በመምጣት ህብረተሰቡና አስተዳደሩ ይበልጥ በመቀራረብ አስተዳደሩ የህብረተሰቡን ፍላጎት ምን እንደሆነና የትኛውን ተግባር ማስቀደም እንዳለበት ግንዛቤ እንዲኖረው እያደረገ ይገኛል።

**ልደታ ፋና፡-**በ2018 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዛችሁትን አገልግሎት ከማሳካት አኳያ ስራችሁን እንዴት ገመገማችሁት?

**አቶ ጢቂ ድሪባ፡-**በበጀት ዓመቱ ለመስጠት ካቀድነው አገልግሎት አንዱ የመልካም አስተዳደር ችግርን መለየትና ችግሮቹ እንዲፈቱ ማድረግ ሲሆን ለዚህም ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የተያዙት እቅዶች የተሳኩ እንዲሆን የሚያስችሉ ስራዎች ተሰርተዋል። የህብረተሰቡን የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት የተለያዩ አማራጮችን የምንጠቀም ሲሆን አሁንም ተግባራዊ እየሆነና የሆነው ፕሮግራማችን የአንድ ማእከል አገልግሎት ሲሆን ፕሮግራሙን ረቡዕ እና አርብ በማከናወን የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች የሚፈልጉትን ጥያቄ ለሚፈልጉት መስሪያ ቤት በቀጥታ ጥያቄያቸውን ማቅረብ እንዲችሉ አድርጓቸዋል። ከዚህ በተጨማሪምበአንድ ማዕከል የቀረቡ ጥያቄዎችን በማድመጥና ችግሮችን ለመረዳት የነዋሪዎች ቤት ድረስ በመውረድ በህብረተሰቡ የተነሱ ጥያቄዎች በፍጥነት መልስ እንዲያገኙ ትረት እየተደረገ ይገኛል።

**ልደታ ፋና፡-** ሴክተር መስሪያ ቤቶችን በበጀትና በሰው ሀይል አደራጅቶ ከመምራት አንጻር ምን ምን ተግባራትን እያከናወናችሁ ትገኛላችሁ?

**አቶ ጢቂ ድሪባ፡-**ተቋማችን በርካታ ሴክተሮችን በስሩ በሰው ሃይልና በበጀት በማደራጀት በበላይነት የሚመራ ሲሆን በካሽ ፍሎው መሰረት በጀታቸውን እንዲጠቀሙ እያደረግን እንገኛለን፡ ፡በስሩ ያሉ ተቋማት በካሽ ፍሎው መሰረት ስራቸውን ሲያከናውን የፋይናንስ ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ለህብረተሰቡና ለተቋማት የምንሰጣቸውን አገልግሎት ፈጣንና ቀልጣፋ እንዲሆን አድርጓል።ተቋማት ለሚፈልጓቸው ግዥዎችና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያዎችን በመቅቱ በማከናወንና የተገዙ ዕቃዎች ለተጠቃሚው በወቅቱ እንዲደርሱ በማድረግ ስራዎቻችን በቅልጥፍና እንዲከናወኑ አስችሎናል።



**አቶ ጢቂ ድሪባ**
**የዋና ስራ አስፈፃሚ ጽ/ቤት ሃላፊ**

**ልደታ ፋና፡-**ከክፍለ ከተማው የካቢኔ ስራዎች ውስጥ የእናንተ የስራ ድርሻ እንዴት ይገልጹታል?

**አቶ ጢቂ ድሪባ፡-**እንደተቋም ሌላው ተግባራችን የካቢኔ ጉዳዮች ሲሆኑ በበጀት ዓመቱ የሴክተሮችን የበጀት እንዲሁም የግብዓት ችግርና የክፍለ ከተማው መደበኛና ወቅታዊ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በካቢኔ አጀንዳ በማስያዝ የበጀት ድጋፍ እንዲደረግ በትኩረት እየሰራን እንገኛለን።በቤቶች፣በኮሪደር ልማትና በሌሎች \የልማት ስራዎች ጋር በተያያዘ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ውሳኔዎች አጀንዳ በመቅረፅ እንዲወሰኑና አሰራር እንዲጠበቅ የማድረግ ስራዎችን ሰርተናል።

**ልደታ ፋና፡-** ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን
**አቶ ጢቂ ድሪባ-** እኔም አመሰግናለሁ